# እስልምናን ለመገንዘብ አጭር ሥዕላዊ ማስረጃ

"باللغة الأمهرية"



شبكة الألوكة
www.alukah.net

www.alukah.net
شبكة الألوكة

**በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው**

# እስልምናን ለመገንዘብ አጭር ሥዕላዊ ማስረጃ

**ደራሲ I.A. IBRAHIM (ኢብራሂም)**

| አጠቃላይ አራሚዎች | የሳይንስ አራሚዎች |
|---|---|
| ዶክተር ዊልያም / ዳውድ/ ፒቼ<br>ሚካኤል /አብዱል ሀኪም / ቶማስ<br>ቶኒ /አቡ ኽሊል / ሲልቨስተር<br>ጀማል ዛራ ቦዞ<br>አሊ አል ተሚሚ | ፕሮፌሰር ሀሮልድ ስትዋርት ኩፊ<br>ፕሮፌሰር ፊ.አ. ሰቴት<br>ፕሮፌሰር ማህጁብ አ.ጣሀ<br>ፕሮፌሰር አህመድ ዐል-ላም<br>ፕሮፌሰር ሰልማን ሱለጣን<br>ምክትል ፕሮፌሰር H.O ሲንዲ |

ትርጉም
ባህረዲን ሙሳ ኢልቦሮ
ኢዲት
አህመድ አወ ል ሀሰን

**2012**



شبكة الألوكة - قسم الكتب

Conveying Islamic message society
Site: www.islamic -message.net
email:info-en@islamic-message.net
Po.box 834-ALEX-EGYPT
TEL: 002 0106901838

## ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| **ክፍል አንድ ፡** አንዳንድ የእስልምናን እውነታነት የሚገልጹ ማስረጃዎች | 7 |
| 1- ሳይንሳዊ ተአምር በቁርአን ውስጥ | 7 |
| ሀ. ቁርአንና የፅንስ ዕድገት | 8 |
| ለ- ቁርአንና ተራራዎች | 13 |
| ሐ- የሥነ ፍጥረታት ምንጭና ቁርአን | 15 |
| መ- የሰው ልጅ አእምሮ በቁርአን ውስጥ | 17 |
| ሠ- ባህሮችና ወንዞች በቁርአን ውስጥ | 19 |
| ረ- ጥልቅ ባህርና ውስጣዊ ማዕበሎች በቁርአን ውስጥ | 21 |
| ሰ- ደመና በቁርአን ውስጥ | 23 |
| ሸ- በቁርአን ውስጥ ስለተገለፀው ሳይንሳዊ ተአምር የሳይንትስቶች አስተያየት | 27 |
| 2-እንደ ቁርአን ምዕራፎች አይነት አንድ የቁርአን ምዕራፍን እንኳ ለማዘጋጀት ታላቅ ፋክክር | 30 |
| 3-ስለ እስላሙ ነቢይ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ተልዕኮ የመጽሀፍ ቅዱስ ትንቢቶች | 32 |

| | |
|---|---|
| 4- የወደፊት ክስተቶችን የሚጠቅሱ የቁርአን አንቀጾችና ከዚያም ቆይተው የተሳኩ | 34 |
| 5- በነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እጅ የተከሰቱ ተአምራቶች | 34 |
| 6- የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ የኑሮ ህይወት ቀላልነት | 35 |
| 7-እስልምና እየተስፋፋ መምጣት | 37 |
| **ክፍል ሁለት፡** አንዳንድ የእስላም ጥቅሞች | 38 |
| 1- ዘላለማዊ የጀነት በር | 38 |
| 2- ከገሀነም እሳት መዳን | 40 |
| 3-እውነተኛ ደስታና ውስጣዊ ሰላም | 40 |
| **ርዕስ** | **ገጽ** |
| 4- ወደ አዲህ ንሰሀ በመግባት ያለፉትን ወንጀሎችን በሙሉ መማር | 42 |
| **ክፍል ሶስት፡** ስለ እስልምና አጠቃላይ ዕውቀት | 42 |
| እስላም ምንድን ነው? | 42 |
| መሠረታዊ እምነት በእስላም | 42 |

| | |
|---|---|
| 1- በአሏህ ማመን | 42 |
| 2- በመልአኮች ማመን | 44 |
| 3- ከሰማይ በወረዱ መጽሐፍቶች ማመን | 45 |
| 4- በነቢያቶችና መልዕክተኞች ማመን | 45 |
| 5- በመጨረሻው ቀን ማመን | 45 |
| 6- በቀድር ማመን | 45 |
| ለእስልምና ከቁርአን ውጭ ሌላ የተቀደሰ ምንጭ አለውን? | 46 |
| አንዳንድ የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲሶች | 46 |
| ስለ ትንሳኤው ቀን እስላም ምን ይላል? | 47 |
| አንድ ሰው እንዴት ሙስሊም መሆን ይችላል ? | 49 |
| ቁርአን የሚናገረው ስለ ምንድን ነው? | 50 |
| ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ማን ነው? | 51 |
| የእስልምና መስፋፋት የሳይንስ ሥልጣኔን እንዴት አገዘ? | 52 |
| ሙስሊሞች በኢሳ/ዐ.ሰ/ እንዴት ያምናሉ? | 53 |
| የእስልምና ሀይማኖት ስለ አሸባሪነት ምን ይላል ? | 56 |

| | |
|---|---|
| | |
| ሰብኣዊ መብትና ፍትህ በእስላም | 57 |
| ሴት ልጅ በእስላም ያላት ቦታ ምንድን ነው ? | 59 |
| **ርዕስ** | **ገጽ** |
| ቤተሰብ በእስላም | 60 |
| ሙስሊሞች የዕድሜ ባለ ፀጋዎችን እንዴት ይንከባከባሉ? | 60 |
| አምስቱ የእስልምና መሰረቶች ምንድን ናቸው ? | 61 |
| 1- ሸሃደቱ አል-ላኢላሀ ኢል-ለሏህ<br>2- ሶላት መስገድ | 61<br>61 |
| 3- ዘካ (ምጽዋት ለድሃዎች) መስ ጠት | 62 |
| 4- የረመዷንን ወር መጾም | 62 |
| 5- ወደ መካ ጉዞ | 63 |
| ስለ እስልምና የበለጠ መረጃ የፈለገ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እና በአረቢኛ ቋንቋ | 64 |




شبكة الألوكة - قسم الكتب

| | |
|---|---|
| ስለዚህ መጽሐፍ አስተያየት ያለው | *64* |
| ስለ እስልምና የበለጠ ለማንበብ | 64 |
| ዋቢ መጽሐፍት | 65 |
| ምሥጋና | 69 |




شبكة الألوكة - قسم الكتب

# መግቢያ

ይህ እስልምናን ለመገንዘብ አጭር ሥዕላዊ ማስረጃ መፅሀፍ ሶስት ክፍሎችን
አካቷል፡

ክፍል አንድ ፡አንዳንድ የእስልምናን እውነታነት የሚገልጹ ማስረጃዎች አንዳንድ ሰዎች ለጠየቋቸው አሳሳቢ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል፡

እውነት ቁርአን ከአሏህ ዘንድ የወረደ የርሱ ቃል ነውን ?
ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በእውነት ከአሏህ የተላኩ ናቸውን ?
እውነት እስልምና የአሏህ ሀይማኖት ነው?

ለነዚህ ጥያቄዎች ምላሽ ስድስት አይነት ማስረጃዎችን እናቀርባለን፡


1.አስደናቂ ሳይንስ በቁርአን ውስጥ ፡ይህኛው ክፍል ሥዕላዊ ማስረጃዎችን በማስደገፍ

ከዛሬ አስራ አራት ክፍለ ዘመን በፊት ቁርአን የገለጻቸውና በአሁኑ ሰአት የተገኙ ብዙ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ይዳስሳል፡፡

2. ከቁርአን ምዕራፎች ውስጥ አንዷን ምዕራፍ የምትመስል እንኳ ለማምጣት ትልቅ መፈታተን ፡

አሏህ /ሱ.ወ/ የሰው ልጆችን በሙሉ ከቁርአን ምዕራፎች አንድ ነጠላ ምዕራፍን የምትመስል እንዲያመጡ ይፈታተናል፡፡ቁረአን ከወረደ ጊዜ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ አንድም ሰው ይህንን ፉክክር መጋፈጥ አልቻለም ፤ ሌላው ቀርቶ ከቁርአን ምዕራፎች ትንሿን ምዕራፍ ከአስር ቃላቶች የተዋቀረችውን እንኳ እንደ አል-ከውሰር ምዕራፍ አይነት ማምጣት አልቻሉም፡፡

3. መጽሀፍ ቅዱስ መልዕክተኛው ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የእስላም ነቢይ ሆነው ስለ መላካቸው፡- ይህ ክፍል እነዚህን ትንቢቶች ያብራራል፡፡



4. የቁርአን አናቅጽ እነዚያ ወደፊት የሚከሰቱትን ነገሮች የጠቀሷቸው ከዚያም ከጊዜ በኋላ የተከሰቱ፡- ቁርአን ሮማዊያን ፋርሶችን ማሸነፋቸውን የመሳሰሉ ወደፊት የሚከሰቱ የነበሩ ነገሮችን በእርግጥ ጠቅሷል።

5. በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እጅ የተከሰቱ ተአምራቶች ፡- በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እጅ ብዙ ህዝቦች የተመለከቷቸው ተአምራቶች ተከስተዋል ።

6. የነቢዩ ሙሀመድ ቀላል ህይወት ፡- ይህም በግልጽ የሚያመለክተው ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ቁሳዊ ጥቅማቸውን ለማሳካት ወይም ለሀያልነት ወይም ለሥልጣን ብለው ነቢይነትን የሚሞግቱ ሰው አልነበሩም ማለት ነው ።

ከነዚህ ስድስት ማስረጃዎች በመነሳት የሚከተሉትን ነጥቦች መረዳት እንችላለን፡-

*በነቢያችን ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ላይ የወረደው ቁርአን ፊደል በፊደል/አንድ በአንድ/ የግድ የአሏህ ቃል መሆን አለበት።

* ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በእውነት ከአሏህ የተላኩ ናቸው።

* እስልምና በእውነቱ ከአሏህ ዘንድ ወደ ሰዎች ሁሉ የመጣ ሀይማኖት ነው።

ስለ ማንኛውም ሀይማኖት እውነታ ማወቅ ከፈለግን ስሜታችንን ወይም ባህላችንን መከተል የለብንም ።ይልቁኑ በአንጎላችንና በአስተውሏችን መሆን አለበት። አሏህ /ሱ.ወ/ነቢያቶችን

በምልክበት ጊዜ እነርሱ በእውነት ነቢያቶች መሆናቸውን የሚያረጋግጡ ተአምራትና ማስረጃዎችን ይልካል።
ሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ እስላም ለግለሰቦች የሚያቀርባቸውን አንዳንድ ትሩፋቶች ይጠቅሳል፣
እንደ፦

1. ዘላለማዊ የገነት በር
2. ከገሀነም እሳት መዳን
3. እውነተኛ ደስታና ውስጣዊ መንፈስ ሰላም መሆን
4. እውነተኛ ንሳህን በመግባት አሏህ ሙሉ ወንጀልን መማሩ ።

ሦሥተኛው ምዕራፍ ደግሞ ስለ እስላም አጠቃላይ ዕውቀት ያቀርባል እንዲሁም ስለ አንዳንድ የእስላም ግንዛቤ ስህተቶችን ያስተካክላል ፣ በተጨማሪም የተጠየቁ አጠቃላይ ጥያቄዎችን ይመልሳል፣ እንደ፦

* እስላም ስለ አሸባሪነት ምን ይላል?
* ሴት በእስላም ያላት ቦታ ምንድን ነው?
* ሰብአዊ መብትና ዕኩልነት በእስላም?
* ቤተሰብ በእስላም
* ሌሎችንም የሰው ልጆችን የሚመለከቱ ርዕሶችን ይዳስሳል።

# ክፍል አንድ

## አንዳንድ የእስልምናን እውነታነት የሚገልጹ ማስረጃዎች

አሏህ /ሱ.ወ/ የመደምደሚያውን ነቢይ ሙህመድ / ሰ.ዐ.ወ/ በእውነት ከአሏህ ዘንድ መላካቸውን የሚያረጋግጡ ብዙ ተአምራቶችና ማስረጃዎችን በማስደገፍ ረድቷል። እንዲሁም አሏህ መጨረሻ ያወረደውን ቁርአን በብዙ ተአምራቶች በማስደገፍ ይህ ቁርአን አንድ በአንድ ከአሏህ ዘንድ የወረደ ቃል መሆኑን አረጋግጧል። ስለዚህም በዚህ ቁርአን ውስጥ የማንም ሰው ቃል ሊቀላቀልበት አልቻለም ። ይህ ምዕራፍ ከነዚህ መረጃዎች ውስጥ የተወሰኑትን አንስቶ ያብራራል ፡-

### 1. ሳይንሳዊ ተአምር በቁርአን ውስጥ

ቁርአን በመልአኩ ጂብሪል /ገብሪኤል/ አማካኝነት በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ላይ የወረደ
ፍጹም ስህተት የሌለበት የአሏህ ቃል ነው። መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ በቃላቸው ሸምድደው ከዚያም ለሶሃባዎች /ለባልደረቦቻቸው/ በቃላቸው አስነበቧቸው ።እነዚህ ባልደረቦቻቸው በቃል መሸምደድ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ጻፉት ፤ ከነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ጋርም ከለሱት ። ከዚህም አልፎ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ቁርአንን ከመልአኩ ጂብሪል ጋር በአመት አንድ ጊዜ ይከልሱ ነበር ። ከህይወታቸው የመጨረሻው አመት ላይ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ከመልአኩ ጂብሪል ጋር ሁለት ጊዜ ክለሳ አድርገዋል። የቁርአን ራዕይ መውረድ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ብዙ ሙስሊሞች ሙሉ ቁርአን ቃል በቃል ሸምድደው ይገኛሉ።



شبكة الألوكة - قسم الكتب

ከዚህም አልፎ ብዙዎቹ በአሥር አመታቸው ሙሉ ቁርአን በቃላቸው ለመሸምደድ ችለዋል፡፡ ታዲያ ለረጅም ክፍለ ዘመናት አንድም የቁርአን ፊደል አልተለወጠም፡፡



ከአሥራ አራት ክፍለ ዘመናት በፊት የወረደው ቅዱስ ቁርአን በአሁኑ ጊዜ እንጂ ያልተደረሰባቸውን ሳይንሳዊ እውነታዎችን ጠቅሷል፡፡ ይህንንም እውነታ ሳይንትስቶች አረጋግጠዋል፡፡

ይህም የሚያመለክተው ያለ ምንም ጥርጣሬ በነቢያችን /ሰ.ዐ.ወ/ ላይ የወረደው ቁርአን ፍጹም ስህተት የሌለበት የአሏህ ቃል መሆን አለበት ፡፡

ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ቁርአንን አልጻፉም እንዲሁም ማንኛዉም የሰው ልጅ አልጻፈውም ልጽፈውም አይችልም፡፡

ይህ አሁንም መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ በእውነት ከአሏህ ዘንድ የተላኩ ነቢይ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ማንኛውም የሰው ልጅ ማወቅና ማስተዋል ያለበት እነዚህ እውነታዎች ከተከሰቱ አሥራ አራት ክፍለ ዘመን አለፋቸው፡፡ እነዚያም እውነታዎች በመጨረሻ በዘመናዊና
በሰለጠነ ሳይንሳዊ ዘዴ ቢሆን እንጂ አልተገኙም ወይም አልተረጋገጡም፡፡ጥቅት ምሳሌዎችን እንመልከት፡-

## ሀ. ቁርአንና የፅንስ ዕድገት ፡-

**አላህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ የሰው ልጆችን የጽንስ ሂደትን አስመልክቶ በሱረቱ አል-ሙእሚኑን ከአንቀጽ 12-14 እንዲህ ይላል፡-**

وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَـٰنَ مِن سُلَـٰلَةٍ مِّن طِينٍ ﴿١٢﴾ ثُمَّ جَعَلْنَـٰهُ نُطْفَةً
فِى قَرَارٍ مَّكِينٍ ﴿١٣﴾ ثُمَّ خَلَقْنَا ٱلنُّطْفَةَ عَلَقَةً فَخَلَقْنَا ٱلْعَلَقَةَ
مُضْغَةً فَخَلَقْنَا ٱلْمُضْغَةَ عِظَـٰمًا فَكَسَوْنَا ٱلْعِظَـٰمَ لَحْمًا ثُمَّ
أَنشَأْنَـٰهُ خَلْقًا ءَاخَرَ ۚ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحْسَنُ ٱلْخَـٰلِقِينَ ﴿١٤﴾

ትርጉሙም

***12- የሰውን ልጅ ከነጠረ ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው።***
***13-ከዚያም የፍትወት ጠብጣ (አድርገን) ምቹ ከሆነ ማረፊያ ውስጥ አስቀመጥነው።***
***14-ከዚያም የፍትወት ጠብታውን የረጋደም፤ የረጋውን ደም የተላመጠ (የሚመስል) ቁራጭ ሥጋ፤ ቁራጩን ሥጋም አጥንት አድርገን ፈጠርነው። አጥንቱንም ሥጋ አለበስነው ። ከዚያም (ነፍስ ዘርተን) ሌላ ፍጡር አደረግነው። አቻ የለሽ ፈጣሪ የሆነው ተባረከ።***

ዐለቃህ የሚለው ቃል በአረቢኛ ቋንቋ ሦሥት ትርጉሞች አሉት ፡-

1- አልቅት 2- የተንጠለጠለ ነገር 3- የረጋ ደም።

አልቅት ከፅንስ የዕድገት ደረጃ / ዐለቃህ/ ጋር ሲነፃፀር በሁለቱም መካከል መመሳሰልን እናገኛለን፤ [1] በሥዕል / 1 /ላይ እንደምንመለከተው ፅንስ ደግሞ በዚህ ሰቴጅ ምግብን ከእናት ደም ያገኛል ። ልክ አልቅት ከሌላ ደም እንደሚያገኘው ሁሉ። [2]ዐለቃህ ለሚለው ቃል ሁለተኛ ትርጉም " የተንጠለጠለ ነገር " ማለት ነው። ይህንንም በሥዕል /2/ ና /3/ ላይ በእናት ማህፀን ውስጥ በዐለቃህ የዕድገት ደረጃ ላይ የፅንስን መንጠልጠል ማየት እንችላለን።

ዐለቃህ ለሚለው ቃል ሦሥተኛው ትርጉም ፡- የረጋ ደም ማለት ነው። የጽነስ የውጪው ክፍልና የርሱ ከረጢት በፅንስ የዕድገት ደረጃ የረጋ ደምን መስሎ እናገኘዋለን ። ያም ሊሆን የቻለው በጽንስ ውስጥ ደም በከፍተኛ ደረጃ ስለሚገኝ ነው።[3] ሥዕል /4/ ላይ ተመልከት።

እንዲሁም በዚህ የዕድገት ደረጃ በፅንጽ ውስጥ የሚገኘው ደም እስከ ሦስተኛው ሳምንት አይንቀሳቀስም /አይዘዋወርም/ ።[4] ታዲያ ፅንስ በዚህ የዕድገት ደረጃ የረጋ ደም ይመስላል ማለት ነው።

---

[1] የሰው ልጅ ዕድገት ፡- Moore እና persaud አምስተኛ እትም ገጽ 8 ።


[2] የሰው ልጅ ዕድገት

ቁርአንና ሀዲስ እንደሚጠቅሰው ፡-Moore እና ሌሎችም ገፅ 36 ።

[3] የሰው ልጅ

ዕድገት ቁርአንና ሀዲስ እንደሚጠቅሰው ፡-Moore እና ሌሎችም ገፅ 37-38 ።


[4] የሰው ልጅ ዕድገት ፡- Moore እና persaud አምስተኛ እትም ገጽ 65 ።





በሥዕል ( 1 ) ላይ እንደምንመለከተው በዐለቃህ ስቴጅ በሁለቱ ቅርፆች ማለትም በአልቅትና በሰው ልጅ ጽንስ መካከል ውጫዊ ተመሳሳይነት አላቸው፡፡

የአልቅት ቅርጽ የተወሰደው Moore እና ሌሎችም ካዘጋጁት የሰው ልጅ ዕድገት ቁርአንና ሀዲስ እንደሚጠቅሰው በሚለው መጽሀፍ ከገጽ 37 ላይ ነው፣ ከዚያም አጠቃላይ መሠረታዊ የእንስሳት ሥነ ፍጥረት ጥናት ሂክማንና ሌሎችም ካዘጋጁት መጽሀፍ ተሻሻለ፡፡


የጽንሱ ቅርፅ ደግሞ Moore እና persaud ካዘጋጁት የሰው ልጅ ዕድገት ከሚለው መጽሀፍ በአምስተኛው እትም በገጽ 37 ላይ የተወሰደ ነው፡፡




በሥዕል ( 2 ) ላይ ያለውን ማብራሪያ ንድፍ እንደምንመለከተው በዐለቃህ ስቴጅ በእናት ማህፀን ውስጥ የጽንስ መንጠልጠልን እናያለን ፡፡ /የሰው ልጅ ዕድገት / ከሚለው መጽሀፍ የተወሰደ ደራሲ Moore እና persaud አምስተኛ ዕትም ገጽ 66 ፡፡




በሥዕል ( 3 ) ላይ እንደምንመለከው በፊደል /B/ ምልክት የተደረገው ትንሽ ሥዕል በዐለቃህ ስቴጅ ላይ በእናት ማህፀን ውስጥ የተንጠለጠለ ጽንስ / ዕድሜው ወደ 15 ቀን / የሆነውን እናያለን የዚህ ጽንስ መጠን ደግሞ 0.6 ሚ.ሜ ይሆናል።
/ የሰው ልጅ ዕድገት / ከሚለው መጽሀፍ የተወሰደ ፣ ደራሲ Moore ሦስተኛ እትም ገጽ 66 ።




በሥዕል ( 4 ) ላይ የምንመለከተው ንድፍ በዐለቃህ ስቴጅ ጽንስ ውስጥ የሚገኙ የደም ሥሮችና የቀድሞ የልብ ሲስተምን ይገልጻል። የጽንሱ የውጭ ክፍልና የርሱ ከረጢት በዐለቃህ ሰቴጅ ከረጋው ደም ጋር ተመሳሳይነት አላቸው፣ ይህም ሊሆን የቻለው በጽንስ ውስጥ በከፍተኛ ደረጃ የደም መገኘት ነው።

/ የሰው ልጅ ዕድገት / ከሚለው መጽሀፍ የተወሰደ ፣ ደራሲ Moore በአምስተኛ እትሙ በገጽ 65 ላይ ።በመሆኑም/ ከላይ የተመለከትናቸው/ ሦስቱ የዐለቃህ የቃላት ትርጉሞች በዐለቃህ ስቴጅ ጽንስን ይገልጻሉ።

ቀጣዩ ስቴጅ በቁርአን አንቀጽ ላይ የተጠቀሰው የሙድጋ ስቴጅ ነው። በአረቢኛ ቋንቋ ሙድጋ ማለት « የተላመጠ ነገር» ማለት ነው። አንድ ሰው ቁራጭ ማስቲካን ወስዶ በአፉ ቢያላምጥና ከዚያም በሙድጋ ስቴጅ ከጽንስ ጋር ቢያነፃጽር ጽንሱ በዚህ ስቴጅ የተላመጠ ነገር እንደሚመስል ያረጋግጣል።

እኛም በሙድጋ ስቴጅ ጽነስና የተላመጠው ነገር በቅርጽ ተመሳሳይነት እንዳላቸው እንረዳለን ። ይህንንም ለማለት የቻልንበት ምክንያት የጽንሱ አካል ጀርባው በመጠኑም ቢሆን በተላመጠው ነገር ውስጥ የጥርስ ምልክት ያለበት በመምሰሉ ነው።[5] /በሥዕል 5፥6 / ተመልከት ።


ነቢዩ ሙሀመድ / ሰ.ዐ.ወ / ከዛሬ አሥራ አራት ክፍለ ዘመን በፊት እንዴት ይህን ሁሉ ሊያውቁ ቻሉ?። ሳይነትስቶች ግን ይህንን እውነታ አሁን በመጨረሻ እንጂ ማግኘት አልቻሉም። ያውም በዘመናዊ መሳሪያና በማይክሮስኮፕ ሀይል በመጠቀም ነው። እነዚህ ዘመናዊ መሳሪያዎች ግን በዚያን ጊዜ አልነበሩምን!

---

5 የሰው ልጅ ዕድገት ፡- ደራሲ Moore እና persaud አምስተኛ እትም ገጽ 8 ።



በሥዕል ( 5 ) ላይ የምንመለከተው ፎቶ ግራፍ በሙድጋ ስቴጅ ዕድሜው 28 ቀን የሆነው ጽንስ ነው። ጽንሱ በዚህ ስቴጅ የተላመጠ የማስቲካ ቁራጭ ይመስላል። ምክንያቱም የጽንሱ አካል ጀርባ በመጠኑም ቢሆን በተላመጠው ነገር ላይ የጥርስ ምልክት ያለበት በመምሰሉ ነው። የጽንሱ መጠን 4 ሚ.ሜ ይሆናል ። /የሰው ልጅ ዕድገት/ ፣ ደራሲ Moore እና persaud አምስተኛ እትም ላይ ገጽ 82 ከፕሮፌሰር ሂዲኦ ኒሺሙራ -ኪቦቶ ዩኒቨርሲቲ -ኪቦቶ ጃፓን።




በሥዕል ( 6 ) ላይ እንደምንመለከተው በሙድጎ ስቴጅ የጽንሱ የውጭ ክፍል ከተላመጠው የማስቲካ ቁራጭ ጋር ስናነጻፅር በመካከላቸው ተመሳሳይነትን እናገኛለን ፡-

**ሀ- የጽንስ ሥዕል በሙድጎ ስቴጅ ፡-** እዚህ ላይ የጽንሱ አካል ጀርባ የጥርስ ምልክት መስሎ እናየዋለን ። /የሰው ልጅ ዕድገት ፤ ዶራሲ Moore እና persaud አምስተኛ እትም ላይ ገጽ 79 /።

**ለ- የተላመጠ የማስቲካ ቁራጭ የፎቶ ግራፍ ምስል ።**

ሀም እና ሎንሆክ / ham and Leeuwenhoek / ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ ፈሳሽን / spermatozoa / በ 1677 እ.ኤ.አ. ዘመናዊ ማይክሮስኮፕን በመጠቀም ተመለከቱ ። ይህም የሆነው /ነቢዩ ሙሀመድ / ሰ.ዐ.ወ/ ከተላኩ ከ1000 አመት በኋላ ነው/።

እነዚህ ሁለቱ ሳይንትስቶች ፡- የእስፐርም ሴል የሰው ልጅ ትንሽ ምስል ይዟል፤ያ እስፐርም በሴት የዘር ግንድ መሸከሚያ ውስጥ የተቀመጠ እንደሆነ ያድጋል የሚል የተሳሳተ አመለካከት ነበራቸው።

ፕሮፌሰር / kith L. Moore / በአናቶሚና በፅንስ ጥናት ታዋቂ ሳይንትስትና በስምንት ቋንቋዎች የተተረጎመው / የሰው ልጅ ዕድገት / የሚለው መጽሀፍ ደራሲ ነው ።ይህ መጽሀፍ ሳይንሳዊ ወሳኝ ዋቢና በተባበሩት አሜሪካ በልዩ ኮሚቴዎች እንደ ምርጥ ድርሰት የተመረጠ መጽሀፍ ነው ። ዶክተር kith Moore በካናዳ ቶሮንቶ ዩኒቨርሲቲ የአናቶሚና የባይሎጂ ሴል ጥናት ፕሮፌሰር ነው ።

እዚያ እርሱ በህክምና ኮሌጅ በመሠረታዊ ሳይንስ ረዳት ዲንና ለስምንት አመታት የአናቶሚ ዲፓርትመንት ሊቀመንበር ሆኖ አገልግሏል ። በ1984 እ.ኤ.አ. በካናዳ በአናቶሚ ፊልድ ልዩ ተሸላሚ ሆኖ ቀርቧል ። ይህም J.C.B. በካናዳዊያን የአናቶሚ ማህበር ታላቅ ሽልማት ነበር ። ብዙ የአለም አቀፍ ማህበራትን አስተዳደር ሆኖ አገልግሏል ። እንደ የካናዳና የአሜሪካ አናቶሚ ማህበርና የባይሎጂካል ሳይንስ አንድነት ምክርቤት ።

በ1981እ.ኤ.አ. በደማም ሳውዲ አረቢያ በሰባተኛው የሜዲካል ኮንፍረንስ ላይ ፕሮፌሰር Moore እንዲህ አለ ፡- በቁርአን ውስጥ ስለ ሰው ልጅ እድገት የተገለፁ ነገሮችን ለማብራራት በመታገዜ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል ። እነዚህ ንግግሮች ከአሏህ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ የመጡ ስለ መሆናቸው ለኔ በእርግጥ ግልጽ ሆኖልኛል። ምክንያቱም እነዚህ እውቀቶች ሁሉ ከብዙ ዘመን በኋላ እንጂ አልተገኙም ።

ይህም ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ መልዕክተኛ እንደነበሩ ያረጋግጣል።[6]

ከዚህም በመነሳት ለፕሮፌሰር Moore ጥያቄ ቀረበለት ፡- ይህ ማለት ቁርአን የአሏህ ቃል መሆኑን ታምናለህ ማለት ነው? እንዲህ በማለት መልስ ሰጠ፡- እኔ ይህን ለመቀበል ምንም ችግር የለብኝም …

---

6 የዚህ አባባል ምንጭ የቪዲዮ ካሴት ነው ርዕሱም “ እውነታው ይህ ነው” ይላል ። ለበለጠ መረጃ www.islamic-guide.com/truth



شبكة الألوكة - قسم الكتب

ፕሮፌሰር Moore በአንዲት ስብሰባው ላይ በሰጠው መግለጫ ፡- የሰው ልጅ ጽንስ የእድገት ደረጃ ውስብስብ ነው ። ምክንያቱም በእድገት ወቅት ቀጣይ የደረጃ ለውጥ ስላለ ነው ። በቁርአንና በሀዲስ የተጠቀሱ ቃላቶችን በመጠቀም አንድ አዲስ የድርሰት ደምብን ሊገነባ የሚችል አስተያየት ነው ። የቀረበው ሀሳብ ደምብ ቀላል፤ ሁሉን ያጠቃለለና ከአሁኑ የጽንስ ጥናት ሳይንስ ጋር የሚስማማ ነው ።

ባለፉት አራት አመታት በቁርአንና በሀዲስ ዙሪያ የተደረጉ ብዙ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከተመዘገበው ጋር ሲነጻፀር ስለ ሰው ልጅ የጽንስ ክፍፍል አስገራሚ ሥርአትን ገልጿል ። ምንም እንኳ አርስቶትል የጽንስ ጥናታዊ ሳይንስ መስራች ቢሆንም ኢሳ /ዐ.ሰ / ከመወለዳቸው በፊት በአራተኛው ክፍለ ዘመን በዶሮ እንቁላሎች ባደረገው ምርምር የጫጩት ጽንስ እድገት በእስቴጅ ነው ቢልም ለዚህ እስቴጅ አንድም ዝርዝር አላቀረበም ።

ከጽንስ ጥናት ታሪክ እንደሚታወቀው በቀርአን ውስጥ ስለ ሰው ልጅ የጽንስ እስቴጅና ክፍፍል ስለተጠቀሰው የታወቀው ጥቅት ነበር ። በዚሁ ምክንያት በቁርአን ውስጥ የተገለፀው የሰው ልጅ ጽንስ ክፍፍል በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ሳይንሳዊ እውቀትን መሠረት ያደረገ ነው ማለት አይቻልም ። ብቸኛው ምክነያታዊ መደምደሚያ እነዚህ መግለጫዎች ከአሏህ ዘንድ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ / ሰ.ዐ.ወ. / የወረዱ መሆናቸው ነበር ። እንደዚህ አይነት ዝርዝሮችን አያውቁም ነበር፣ ምክንያቱም የማያነቡና የማይጽፉ /ኡሚይ / ነበሩ። አንድም ሳይንሳዊ ልምምድ አላደረጉም ።[7]

## ለ- ቁርአንና ተራራዎች

አንድ ርዕሱ (ምድር) የሚል መጽሀፍ አለ ፥ ይህ መጽሀፍ በብዙ የአለም ዩኒቨርሲቲዎች መሰረታዊ ዋቢ ሆኖ ይጠቀሳል ። ፕሮፌሰር ፍራንክ ፕሬስ የመጽሀፉ አንዱ ደራሲ ነው ።

---

[7] የቪዲዮ ካሴት‹‹ እውነታው ይህ ነው ።››

ለቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ጂሚ ካርተር የሳይንስ አማካሪ ሆኖ አገልግሏል ። ከዚያም ለ12 አመት ዋሽንተን ውስጥ የብሄራዊ ሳይንስ አካዳሚ ሊቀመንበር ሆኗል ።


ይህ መጽሀፍ እነዲህ ይላል ፦ ከተራራዎች በታች ሥሮች /መሠረቶች / አሉ ። እነዚህ ሥሮች በምድር ውስጥ በጥልቅ ተቀብረዋል ። በዚህ ሁኔታ ተራራዎች ማንጠልጠያ የሚመስል ቅርፅ አላቸው ። ( በሥዕል 7-8-9 ተመልከት ) ። ቁርአን ተራራዎችን ልክ እንደዚህ ነበር የገለፃቸው ። አኢህ / ሱ.ወ / በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል -ነበእ በአንቀጽ 6 እና 7 ላይ እንዲህ ይላል ፦

أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ مِهَٰدٗا ۝٦ وَٱلۡجِبَالَ أَوۡتَادٗا ۝٧


ትርጉሙ፦

***6. ምድርን ምንጣፍ አላደረግናትምን?***


***7. ጋራዎችን ችካሎች አላደረግንም?***




በሥዕል ( 7 ) ላይ እንደምንመለከተው ተራራዎች ከምድር በታች በጥልቀት የተቀበሩ ሥሮች / መሰረቶች / አኢቸው ። (የምድር ፕሬስና ሲቨር ገጽ 413)




በሥዕል ( 8 ) ላይ እንደምንመለከተው የሥራ እቅድ ክፍል ፦ ተራራዎቹ እንደ ችካል በምድር ውስጥ በጥልቅ የተቀበረ መሠረቶች / ሥሮች / አሏቸው ። (የምድር አካል ገጽ 220) ((Anatomy of the earth, cailleux p. 220))




በሥዕል ( 9 ) ላይ ያለውን እንደምንመለከው የተራሮች ቅርፅ እንዴት ችካል እነደሚመስል ነው ። ለዚህም ምክንያቱ ምድር ውስጥ ጥልቅ መሰረት ስላለ ነው ። (የመሬት ሳይንስ ገፅ 158) (Earth science, Tar buck and Lutgens)

ዘመናዊ የምድር ሳይንስ እንደሚያረጋግጠው ተራራዎች ከምድር በታች ጥልቅ መሰረት አሏቸው ። (ሥዕል 9 ተመልከት) እነዚህ ሥሮች / መሰረቶች/ ከምድር በላይ የተራራዎቹን ከፍታ ብዙ እጥፍ

ሊደርሱ ይችላሉ ፡፡[8] ስለዚህ በነዚህ ኢንፎርሜሽኖች መሰረት ተራራ ለሚለው ቃል የበለጠ ተስማሚ ገለፃ ሊሆን የሚችለው ችካል የሚለው ቃል ነው ፡፡ ምክንያቱም አብላጫው የችካል አካል ከምድር በታች ድብቅ ስለሆነ ነው ፡፡



የሳይንስ ታሪክ እንደሚያስረዳው ስለ ተራራዎች ሥር የሚናገረው አስተያየት በ1865 እንጂ አይታወቁም ነበር ፡፡ ይህም በሥነ ምህዋር ሳይንትስቱ Sir George Airy አማካኝነት ነበር ፡፡ [9]ተራራዎች የምድርን ቅርፊት የላይኛውን አካል በማደላደል ትልቅ ሚና ይጫወታሉ ፡፡[10] ምክንያቱም (እነዚህ ተራራዎች) ምድር እንዳይንቀጠቀጥ ይከለክላሉ ፡፡ አላህ /ሱ.ወ / በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል- ናህል በአንቀጽ 15 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(وَأَلْقَىٰ فِي ٱلْأَرْضِ رَوَٰسِيَ أَن تَمِيدَ بِكُمْ وَأَنْهَٰرًا وَسُبُلًا لَّعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ ﴿١٥﴾)

[8] ጂኦሎጂካላዊ የተራራዎች ኮንሴፕት በቁርአን ውስጥ ገጽ 5

[9] ምድር ፣ ፕሬስና ሲቨር ገጽ435 ፡፡ እንዲሁም ጂኦሎጂካላዊ የተራራዎች ኮንሴፕት በቁርአን ውስጥ ገጽ 5 ተመልከት ፡፡

[10] ጂኦሎጂካላዊ የተራራዎች ኮንሴፕት በቁርአን ውስጥ ገጽ 44-45

ትርጉሙ

## ‹‹ም ድርም እንዳታረገርግባችሁ ከበላይዋ ጋራዎችን ተከለ ፡፡ ትመሩባቸው ዘንድም (ከበላይዋ) ወንዞች (እንዲፈሱ አደረገ)፤ መንገዶችንም (ዘረጋ)‹‹

በተጨማሪም ዘመናዊ የቴክቶኒክ ፕሌቶች ኮንሴፕት እንደሚወስነው ተራራዎች ምድር እንድትፀና ያደርጋሉ ፡፡ የዚህ ኢንፎረሜሽን ግንዛቤ የተጀመረው ከ1960ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ በቴክቶኒክ ፕሌት ፍሬም ወርክ ነበር ፡፡[11]ማንኛውም ሰው በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ./ ዘመን የተራራን እውነተኛ ቅርፅ ሊያውቅ ይችል ነበርን? ማንኛውም ሰው ይህን ፊትለፊቱ የሚያየውን በጣም ትልቅና ከባድ ተራራ በእውነቱ ጥልቀቱ ምድር ውስጥ የሚደርስና በአሁኑ ጊዜ ሳይንትስቶች እንደሚያረጋግጡት መሰረት ያለው ነው ብሎ የሚገምት ሰው ነበር ን? ዘመናዊው የጂኦሎጂ ሳይንስ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሰውን እውነታ በእርግጠኝነት አረጋግጧል፡፡

## ሐ-ቁርአንና የሥነ ፍጥረታት ምንጭ ፡-

በአንድ ወቅት ዘመናዊ ሳይንስ በተጨባጭና በቲኦሪ የሥነ ፍጥረታት ጥናትና በቲኦሪ ፤ሥነ ፍጥረታት ሁሉ የደመና ጥስ በስተቀር ሌላ እንዳልነበር በግልጽ ያመለክት ነበር ፡፡ (ያ ማለት በጣም ጥቅጥቅ ያለና የሞቃት ጋዝ ድርሰት ነው) ፡፡[12]

---

11 ጂኦሎጂካላዊ የተራራዎች ኮንሴፕት በቁርአን ውስጥ ገጽ 5

12 የመጀመሪያዎቹ ሦስት ደቂቃዎች ፡- ዘመናዊ የሥነ ፍጥረታት ምንጭ እይታ ፤ ዊንበርግ ገጽ 94-105

ይህ አንዱ የማያከራክር መሠረታዊ የሥነ ፍጥረታት ዘመናዊ ሳይንስ መለኪያ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ሳይንትስቶች ከዚህ ጥስ ቅሪት ውጭ የተዋቀሩትን አዳዲስ ኮከቦችን ማየት ችለዋል ። (ሥዕል 10 እና 11 ተመልከት) ። ሌሊት ላይ አብርቶ የምናየው ኮከብ በአጠቃላይ ሥነ ፍጥረታት ሁሉ ልክ በዚህ ጢሳማ ቁስ ውስጥ እንደነበር ነው የሚያመለክተው ። አላህ(ሱ.ወ) በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ፉሲለት በአንቀጽ 11 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰٓ إِلَى ٱلسَّمَآءِ وَهِيَ دُخَانٌ)

<u>ትርጉሙም</u>

11- *<<ከዚያም ወደ ሰማይ አሰበ ። ጭስ ነበረች>>*

(ፀሐይ፣ጨረቃ፣ኮከብ፣ጋላክሲ...) ከሰማይና ምድር በላይ በመሆናቸው ምክንያት ከዚሁ ጭስ ነበር የተፈጠሩት ። ስለዚህም ሰማይና ምድር አንድ ላይ የተጣበቀ አንድ አካል ነበሩ ከዚያም ተዋቀሩና ከዚህ ተመሳሳይ ከሆነው ጭስ ውጭ ከፊሉ ከከፊሉ ተለያየ ማለትን እንረዳለን ። አሏህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-አንቢያእ በአንቀፅ 30 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(أَوَلَمۡ يَرَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَنَّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ كَانَتَا رَتۡقٗا فَفَتَقۡنَٰهُمَا)

<u>ትርጉሙ</u>

30-*<<እነዚያ የካዱት ፣ሰማያትና ምድር የተጣበቁ እንደነበሩና እኛ እንደነጣጠልናቸው አያዩምን >>*

ዶክተር (Alfered Kroner) በአለም ላይ በጂኦሎጂ ከሚታወቁ ሳይንስቶች አንዱ ነው ። እንዲሁም በጀርመን ማይንዝ ውስጥ በጆሀንስ ጎተንበርግ ዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰርና የጂኦሎጂ ትምህርት ዲፓርትመንት ሊቀመንበር ነው ። እንዲህም አለ፡- <<ስናስበው ነቢዩ ሙሀመድ እነዚህን እንፎርሜሽኖች ከየት አመጧቸው? እኔ እንደሚመስለኝ እነዚህን ነገሮች እንደ የሥነ ፍጥረታት የጋራ ምንጭ የመሳሰሉትን በፍጹም ሊያውቁ አይችሉም ። ምክንያቱም ሳይንትስቶች ያገኙት ባለፉት ጥቅት አመታቶች ነው ። ይሀውም በጣም ውስብስብና በዘመናዊ የቴክኖሎጂ ዘዴዎችን በመጠቀም ነው>> ።

በተጨማሪም እንዲህ ይላል፡- <<አንድ ከአሥራ አራት መቶ አመት በፊት ስለ ፊዚክስ ኒዩክሌር ምንም የማያውቅ ሰው ለምሳሌ ፡- ሰማይና ምድር ከአንድ ምንጭ ናቸው ብሎ በርሱ አእምሮ ብቻ መርምሮ ማግኘት ይችላል ብዬ አላምንም ።[13]



ሥዕል ( 10 ) ፡- አዲሱ ኮከብ ከአቧራና ከጋዝ ደመና የተዋቀረ ነው (nebula) ። ይህም የሥነ ፍጥረታት ሁሉ ምንጭ የነበረው አንዱ የጭስ ቅሪት ነው ። (The space Atlas, Heather and Henbest, p.50)

---

13 የቪዲዮ ካሴት <<እውነታው ይህ ነው>> ።



شبكة الألوكة - قسم الكتب



ሥዕል( 11 ):- የሚያመለክተው የደመና ሀይቅ ነው (The Lagoon nebula) ይህ የጋዝና የአቧራ ደመና ነው ። በዲያሜትር ወደ 60 የብርሃን አመት ይሆናል ።ሀይቁን በአዲስ መልክ የተዋቀረው ከፍተኛ ሙቀትን ያዘለው ኮከብ በአልትራ ቫዮሌት ስርጭት ላይ ያለው ጨረር ማራኪ አድርጎታል ። (አድማስ የሥነ ፍጥረታት ምርምር)

## መ- ቁርአንና የሰው ልጅ አዕምሮ

የተባረከው አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ዐለቅ ከአንቀጽ 15-16 ከሙሽሪኮች ስለ አንዱ ተንኮለኛ ሙሽሪክ ያ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ/ወ/ በካእባ ሶላት እንዳይሰግዱ የከለከላቸውን የሚናገር ነው።-

(كَلَّا لَئِن لَّمْ يَنتَهِ لَنَسْفَعًا بِٱلنَّاصِيَةِ ﴿١٥﴾ نَاصِيَةٍ كَٰذِبَةٍ خَاطِئَةٍ ﴿١٦﴾)

<u>ትርጉሙ</u>

*15- « (ከአድራጎቱ) ይታቀብ፤ (አንተን ከማወክ) ባይቆጠብ አናቱን ይዘን (ወደ ገሀነም) እንጎትተዋለን » ።*
*16- «ሀሰተኛና ስህተተኛ የሆነች አናቱን» ።*

ለምን አሏህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ የራስን አናት ሀሰተኛና ስህተተኛ በማለት ጠቀሰ? ለምን ግለሰቡን ራሱ ሀሰተኛና ስህተተኛ ነው አላለም? በራስ አናት፥ በሀሰተኝነትና ስህተተኛነት ያለው ግኑኝነት ምንድን ነው?


በራስ አናት ላይ የሚገኘውን የራስ ቅል ያየን እንደሆነ ወደፊት አካባቢ የሚገኘውን አንጎል እናገኛለን ። (ሥዕል 12 ተመልከት) ። ስለዚህ አካባቢ ተግባር ፊዚዮሎጂ ምን ይላል? ርዕሱ የአናቶሚና የፊዚዮሎጂ አስፈላጊነት በሚለው መጽሐፍ ላይ እንዲህ ይላል፦

<<መገፋፋትና ፥እቅድ ለማውጣት እንቅስቃሴዎችን በመጀመር አስቀድሞ ማሰብ ፥የሚከሰተው በፊትለፊት በኩል የሚገኘው ነው ። ይህም ፊትለፊት አካባቢ ያለው ግንባርና ኮርቴክስን የሚያሳስረው አካባቢ ነው>> ።[14] መጽሐፉ አስከትሎም <<የመገፋፋትን ተሳትፎ በተመለከተ ፊትለፊት አካባቢ ያለው ግንባር ዋና የጠላትነት ተግባሮች አሉት >> ። ታዲያ ይህ የአእምሮ አካባቢ ስለ እቅድ አወጣጥ፥አነሳሽና እንዲሁም ጥሩና መጥፎ ሐሳብን የሚያፈልቅና እውነትና ሀሰትን በመናገር ድርሻ ያለው ነው ። ስለዚህ አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ <<ሀሰተኛና ስህተተኛ የሆነች አናቱን>> እንዳለው የሰው ልጅ ሲዋሽና ወንጀል ሲሰራ አናትን በእውነትና ሀሰት መሰየም ተገቢ ነው ።[15]

---

[14] የናቶሚና የፊዚዮሎጂ አስፈላጊነት ፡- ሲሊና ሌሎችም ገጽ 211 እንዲሁም የሰው ልጅ ነርቭ ሲስተም በሚለው ላይ ተመልከት ፣ ኖባክና ሌሎችም ገጽ 410-411

[15] የአናቶሚና የፊዚዮሎጂ አስፈላጊነት ፡ ሲሊና ሌሎችም ገጽ 211




ሥዕል ( 12 ) እንደሚያመለክተው ፡ የበስተግራ አካባቢ ተግባሮች የአንጎል ኮርቴክስ የክብ አጋማሽ ናቸው ። የግንባር አካባቢ የአንጎል ኮርቴክስ ፊትለፊት ይገኛል ። የአናቶሚና የፊዚዮሎጂ አስፈላጊነት፡ ሲሊና ሌሎችም ገጽ210 ።

እነዚህ የግንባር አካባቢ ተግባሮች የተገኙት ባለፉት ስልሳዎቹ አመታቶች ነበር ። ይህንንም ያለው ፕሮፌሰር Keith L.Moore ነው።[16]


## ሠ- ባህሮችና ወንዞች በቁርአን ውስጥ

ዘመናዊ ሳይንስ ሁለቱ የተለያዩ ባህሮች የሚገናኙበትን ቦታና በሁለቱም መካከል ማገጃ እንዳለ አግኝቷል ። ይህ ማገጃ ሁለቱን ባህሮች ይከፍላል ። ሆኖም እያንዳንዱ ባህር የራሱ የሆነ

---

16 አል-ኢዕጃዝ አል-ዒልሚ ፊ አል-ናሲያህ (ሳይንሳዊ ተአምሮች በአናት ላይ) ፡ Moore እና ሌሎችም ገጽ 41

የሙቀት፣ የጨዋማነትና የውፍረት መጠን አለው ።[17] ለምሳሌ የሜድትራኒያን ባህር ውሃ በጣሪቅ(Gibraltar) ተራራ አማካኝነት ወደ አትላንቲክ ውቅያኖስ ይገባል ይህም በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮችን በመጓዝ ነው ። በአትላንቲክ ውቅያኖስ ውስጥ ወደ አንድ ሺህ ሜትር ጥልቀት ከነ ሙቀቱ ፣ ጨዋማነቱና ከአነስተኛ ውፍረቱ ጋር ይጓዛል[18] (ሥዕል 13 ተመልከት) ።




ሥዕል ( 13 ) ላይ እንደተመለከትነው የሜድትራኒያን ባህር ውሃ በጣሪቅ (Gibraltar) ተራራ አማካኝነት ከነ ሙቀቱ ፣ጨዋማነቱና ከአነስተኛ ውፍረት ባህሪው ጋር ወደ አትላንቲክ ውቅያኖስ ይገባል ። ምክንያቱም በሁለቱ መካከል የሚለያቸው ማገጃ ስላለ ነው ። የሙቀቱ መጠን በዲግሪ ሴልሽስ (c°) ይለካል ።

ምንም እንኳ ከፍተኛ ማእበልና ጠንካራ ጎርፍ በባህሩ ውስጥ ቢኖርም አይደባለቅም ወይም ይህንን ማገጃ አይጥስም ። አሏህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ረህማን ከአንቀጽ 19-20 ስለዚህ ስለ ሁለቱ ባህሮች መካከል ስላለው ማገጃና ተገናኝተው ያለ መደባለቃቸውን ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

---

17 principles of oceanography, Davis, p 92-93
18 principles of oceanography, Davis, p 93

مَرَجَ ٱلْبَحْرَيْنِ يَلْتَقِيَانِ ﴿١٩﴾ بَيْنَهُمَا بَرْزَخٌ لَّا يَبْغِيَانِ ﴿٢٠﴾

ትርጉሙ

***19-<<ሁለቱን ባህሮች ይገናኙ ዘንድ ለቀቃቸው>> ፡፡***
***20-<<በመካከላቸው ጋራጅ አለ፤ አንዱ በሌላው ላይ ወሰንን አያልፍም፤ (አይዋሀዱም) >>፡፡***

ነገር ግን ቅዱስ ቁረአን በጣፋጭና ጨዋማ ውሃ መካከል ያለውን መለያ ሲናገር ከመለያው የሚከለክል ግርዶሽ መኖሩን መግለጹ ነው ፡፡ ይህንንም በማስመልከት አሏህ/ሱ.ወ/ በሱረቱ አል-ፉርቃን በአንቀጽ (53) ላይ እንዲህ ይላል፡-

۞ وَهُوَ ٱلَّذِى مَرَجَ ٱلْبَحْرَيْنِ هَٰذَا عَذْبٌ فُرَاتٌ وَهَٰذَا مِلْحٌ أُجَاجٌ وَجَعَلَ بَيْنَهُمَا بَرْزَخًا وَحِجْرًا مَّحْجُورًا ﴿٥٣﴾


ትርጉሙም

***53-<<እርሱ ያ፤ አንዱ ጣፋጭና ጥምን ቆራጭ፤ሌላኛው ጨዋማና መርጋጋ የሆኑ ሁለት ባህሮችን አጎራብቶ የለቀቀ፤እነዳይቀላቀሉም በመካከላቸው ግርዶና አቃቢ ክልል ያበጀ (አምላክ) ነው>> ፡፡***

ምናልባት አንድ ሰው ጥያቄ ልጠይቅ ይችላል፡- አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በጣፋጭና ጨዋማ መካከል ያለውን መለያ ሲናገር ለምን ግርዶሽን ገለጸ ነገር ግን በሁለቱ ባህሮች ያለውን መለያ ሲናገር አልጠቀሰውም?

ዘመናዊ ሳይንስ የወንዞችን መፍሰሻ ቦታ መርምሮ በማግኘት ጣፋጭና ጨዋማ ውሃ የሚገናኙበትን ቦታ አውቋል ፡፡ ሁኔታው ከሁለቱ ባህሮች የመገናኛ ቦታ በጥቅቱም ቢሆን ይለያል ፡፡ ከወንዞች ፍሳሽ ጣፋጭ ውሃ ከጨዋማ ውሃ የሚለይበት መንስኤ

ዝቅተኛ አካባቢ (pycnocline) ላይ መሆኖ ተጠንቷል ፡፡ በደንሲቲውና በአቋራጭነቱ የሚለይና በሁለቱ መስመሮች መካከል መለያ ያለው ነው ፡፡ ይህ መክፈያ (የመለያ ክልል) ከጣፋጭና ከጨዋማ ውሃ የሆነ የተለያየ የጨዋማነት ደረጃ አለው[19] ሥዕል 14 ላይ ተመልከት ፡፡




ሥዕል 14 ፡ ከላይ በሥዕሉ ላይ እንደተመለከትነው ጨዋማን የሚያሳይ ረጅም ክፍል ነው ፡፡ (የአንድ ሺህ ክፍል %) በወንዝ ውስጥ ይፈሳል ፡፡ እዚህ ላይ በጣፋጭና በጨዋማ ውሃ መካከል ያለውን መክፈያ (መለያ ክፍል) ማየት እንችላለን ፡፡ (Introductory oceanography, Thurman P 301).

እነዚህ ኢንፎርሜሽኖች አሁን ቢሆን እንጂ ከዚህ በፊት አይታወቁም (አልተገኙም ) ነበር ፡፡ ይህውም የሙቀት፣የጣፋጭና የጨዋማነት መለኪያ እንዲሁም የደንሲቲንና ኦክሲጅን የሚሟማበትን ደረጃ ለይቶ የሚያሳዩ መሳሪያዎችንና ዘመናዊ መመሪያዎችን በመጠቀም ነው ፡፡

የሰው ልጅ አይን በሁለቱ ባህሮች መካከል ያለውን መገናኛ መስመር ለይቶ ማወቅ አይችልም ፡፡ ይልቁንም ሁለቱ ባህሮች እንደ አንድ ባህር ሆኖ ይታዩናል ፡፡ እንዲሁም የሰው ልጅ አይን በወንዞች የሚፈሰውን የውሃ ክፍፍል ሦሥት አይነት እንደሆነ ለይቶ ማወቅ አይችልም ፣ ይህም ጣፋጭ ውሃ ፥ ጨዋማና መክፈያ(መለያ ክልል) ነው፡፡

[19] oceanography.Gross.P.242 and Introductory oceanography, Thurman p. 300-301

## ረ- ጥልቅ ባህሮችና ውስጣዊ ማዕበሎች በቁርአን ውስጥ

አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አን-ኑር በአንቀጽ( 40) ላይ እንዲህ ይላል፡-


(أَوْ كَظُلُمَـٰتٍ فِى بَحْرٍ لُّجِّىٍّ يَغْشَىٰهُ مَوْجٌ مِّن فَوْقِهِۦ مَوْجٌ مِّن فَوْقِهِۦ سَحَابٌ ۚ ظُلُمَـٰتٌۢ بَعْضُهَا فَوْقَ بَعْضٍ إِذَآ أَخْرَجَ يَدَهُۥ لَمْ يَكَدْ يَرَىٰهَا ۗ وَمَن لَّمْ يَجْعَلِ ٱللَّهُ لَهُۥ نُورًا فَمَا لَهُۥ مِن نُّورٍ ﴿٤٠﴾ )

ትርጉሙም

***40-<<ወይም ከበላዩ ማዕበልንከዚህም በላይ (ሌላ) ማዕበል፣ከርሱ በላይ ደግሞ ዳመና የሸፈነው በሆነ ጥልቅ ውቅያኖስ ውስጥ እንዳሉ ጨለማዎች ነው ፡፡ አንዱ በአንዱ ላይ የተነባበረ ጨለማዎች ፡፡ (ከነኝህ ማዕበሎች ውስጥ ያለ) ሰው እጆቹን ቢዘረጋ ፈጽሞ ሊያየው አይችልም ፡፡ አሏህ ብርሃን ያላደረገለት ብርሃን የለውም፡፡***

አሏህ/ሱ.ወ/ በነዚህ የቁርአን አንቀጾች በባህሮችና በውቅያኖሶች ውስጥ የሚገኙትን ጨለማዎች የጠቀሰው አንድ ሰው እጁን በጥልቅ ባህር ውስጥ ፊትለፊቱ እጁን ቢዘረጋ ሊያየው እንደማይችል ነው ፡፡ ጭለማው በጥልቅ ባህሮችና ውቅያኖሶች ውስጥ ወደ 200ሜትር አካባቢ ይገኛል ፡፡ ከዚህ ጥልቀት በታች ምንም ብርሃን የለም ፡፡ (ሥዕል 15 ተመልከት) ከ1000 ሜትር ጥልቀት በታች በፍጹም ብርሃን የለም ፡፡ የሰው ልጅ በባህር ሰርጓጅ መርከብ ወይም ልዩ መሣሪያዎችን በመጠቀም ካልሆነ በስተቀር ከአርባ ሜትር በላይ

መጥለቅ አይችልም ። የሰው ልጅ በጥልቅ ጨለማ ውቅያኖስ ውስጥ 200 ሜትር ጠልቆ መቋቋም አይችልም ።




ከላይ የምንመለከተው ሥዕል 15 እንደሚያሳየን በ3 እና በ30 ፐርሰንት መካከል በሀገር ላይ የሚገኝ የፀሐይ ብርሃን ነጸብራቅ ነው ። ታዲያ የሰመያዊ ብርሃን ሲቀር በመጀመሪያዎቹ 200 ሜትሮች ሁሉም ሰባቱ የብርሃን ቀለሞች አንዱ በሌላ ላይ ይመጠጣል። (ውቅያኖሶች ፣ ኢልደርና ፐርነታ ገጽ 27)

ሳይንትስቶች ይህንን ጨለማ ያገኙት አሁን ነው ። ይሀውም በልዩ አስፈላጊ መሳሪያዎችና በባህር ሰርጓጅ መርከብ አማካኝነት ነው ። እንዲሁም በሚቀጥለው የቁርአን አንቀጾች ውስጥ የተጠቀሱትን መረዳት እንችላለን ፡-

{ فِي بَحْرٍ لُّجِّيٍّ يَغْشَاهُ مَوْجٌ مِّن فَوْقِهِ مَوْجٌ مِّن فَوْقِهِ سَحَابٌ ۚ }


ትርጉሙ

***40-<<ከበላዩ ማዕበልን ከዚህም በላይ (ሌላ) ማዕበል፣ ከርሱ በላይ ደግሞ ዳመና የሸፈነው በሆነ ጥልቅ ውቅያኖስ ውስጥ >>***

በባህርና ውቅያኖስ ውስጥ የሚገኘው ስምጥ ውሃ በማዕበል ላይ ማዕበል የተሸፈነ ውሃ ነው ። ያ የምንመለከተው ሁለተኛው የማዕበል ስብስብ የባህሩ የላይኛው ክፍል ማዕበል መሆኑ ግልጽ ነው


شبكة الألوكة - قسم الكتب

። ምክንያቱም የቁርአኑ አንቀጽ በሁለተኛው ማዕበል ላይ ዳመና መኖሩን ይጠቅሳል ።ነገር ግን ስለ መጀመሪያው ማዕበልስ? ከጥቂት ጊዜ በፊት ሳይንትስቶች ውስጣዊ ማዕበል እንደሚገኝ አጥንተው ማረጋገጥ ችለዋል ። ይህ ማዕበል የሚከሰተው በተለያዩ የውፍረት መጠን ባላቸው እርከኖች መካከል በሚኖረው የመሐል ክፍተት መጠን ምክንያት ነው ። (ሥዕል 16 ተመልከት)




ይህ ከላይ የምንመለከተው ሥዕል/16/ በሁለቱ የተለያዩ የውፍረት እርከኖች መካከል የሚከሰት ውሃ የውስጣዊ ማዕበል ነው ። አንደኛው (ከታች በኩል ያለው) በጣም ወፍራም ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ (ከላይ በኩል ያለው) በመጠኑ ወፍራም ነው ። [20]ውስጣዊ ማዕበሎች በባህሮችና በውቅያኖሶች ውስጥ ጥልቅ ውሃ ተሸፍነውታል፣ ምክንያቱም ጥልቁ የውሃ ክፍል ከበላዩ ካለው የውሃ ውፍረት መጠን የበለጠና ውስጣዊ ማዕበልን የሚፈጥር በመሆኑ ነው ። ውስጣዊው ማዕበል እንደላይኛው የማዕበል ክፍል ይሰራል፣ እንዲሁም ይህ ማዕበል እንደላይኛው የማዕበል ክፍል ሊሰባበር ይችላል። ነገር ግን ውስጣዊ ማዕበል በሰው አይን ሊታይ አይችልም። ይልቁኑም በተወሰነ ቦታ የሙቀትና የጨዋማነትን መጠን ለውጦች ጥናት በማድረግ ማግኘት ይቻላል ።[21]

[20] Oceanography, Gross. P205


[21] Oceanography, Gross. P205

## ሰ፡- ደመና በቁርአን ውስጥ

ሳይንትስቶች የተለያዩ ደመና አይነቶችን አጥንተዋል፤ብሎም የዝናብ ደመና በተወሰኑ ደንቦችና ስቴፖች መሰረት እንደሚዋቀርና ከንፋስና ዳመናዎች ጋር ትስስር እንዳላቸው ተገንዝበዋል ።

አንዱ የዝናብ ደመና አይነት የደመና ክምር (cumulonimbus) ነው። ሜትሮሎጂስቶች የደመና ክምር እንዴት እንደሚዋቀርና እንዴት ዝናብ ፣በረዶና መብረቅ ሊያመነጭ እንደሚችል ጥናት አካሄደዋል ። በተጨማሪም የደመና ክምር ዝናብን ለማመንጨት የሚከተሉትን ስቴፖች እንደሚከተል አሳስበዋል ፡-

1-ደመናዎች በንፋስ ይገፋሉ፡- የደመና ክምሮች መዋቀር የሚጀምሩት ንፋሶች አንዳንድ ጥቃቅን የደመና ቁራጮችን ወደ ደመና መሰባሰቢያ አካባቢ በሚገፉት ጊዜ ነው ። (የደመና ክምር cumulus) (ሥዕል 17እና 18ተመልከት) ።





በሥዕል 17 ላይ የምንመለከተው የሳተላይት ፎቶ ግራፍ ደመና ወደ B,C, እና D የሚገናኝበት አካባቢ መንቀሳቀሱን የሚያሳይ ነው። ቀስቶቹ የንፋስን አቅጣጫ ያመለክታሉ ። (በአየር ትንተናና ትንበያ የሳተላይት ሥዕል መገልገያ ፤ አንደርሶንና ሌሎችም ገጽ 188) ።



በሥዕል 18 ላይ የምንመለከተው ትናንሽ የደመና ቁርጭራጭ (cumulus clouds) ወደ መገጣጠሚያ አካባቢ አድማስ አጠገብ ይንቀሳቀሳሉ ። ይህንንም ትልቅ የደመና ክምር ማየት እንችላለን (ደመናና አውሎ ንፋስ ፡ Ludlum, plate 7.4) ።

(2) መገጣጠም፡- የዚህን ጊዜ ትናንሽ ደመናዎች እርስበርሳቸው ይገጣጠማሉ ከነርሱም ትልቁ ደመና ይዋቀራል ። (ሥዕል 18 እና 19 ተመልከት)[22]

22 the Atmosphere, Anthes and others p. 268-269 and Elements of Metrology, Miller and Thompson p.141




ከላይ በሥዕል 19 ላይ የምንመለከተው ፡-

(A) ተለይቶ የኖረ ትንሽ የደመና ቁራጭ (cumulus clouds) ነው ።

(B) ትንሹ ደመና አንድ ላይ ሲደባለቅ ፣ በትልቁ የተነደፈው የደመና መጨመር ሲሆን የውሃ መጣልን የሚያሳይ በምልክት ተለይቷል * ። (the Atmosphere, Anthes and others p. 269)


(3) መከመር ፡- ትናንሽ የደመና ማዕበሎች እርስበርሳቸው ሲገናኙ የአየር ሞገዶች ደመና በትልቁ እንዲጨምር የደርጋሉ ። ከደመና ማዕከል አጠገብ ያሉት የአየር ሞገዶች ከነዚያ ዳርቻ ካሉት ይጠነክራሉ ።[23] እነዚህ የአየር ሞገዶች የደመና አካል በቀጥታ (vertically) እንዲያድግ የደርጋሉ ። ስለዚህ ደመናው ይከመራል ። (ሥዕል19 (B), 20 እና 21 ተመልከት) ። ይህ የቀጥታ ዕድገት (vertical growth) የደመናው አካል ተዘርግቶ አትሞስፈር ቀዝቃዛ የአየር ክልሎች እንዲገባ ያደርጋል ። ያም የውሃ ጠብታና በረዶ የሚዋቀርበትና ማደግ የሚጀምርበት እንዲሁም እየተለቀ የሚሄድበት አካባቢ ነው ።

እነዚህ የውሃ ጠብታዎችና በረዶች ክብደታቸው በጣም ከፍ ሲል የአየር ሞገዶቹን ክብደት መሸከም አይችሉም ። እነዚህም በዝናብና በበረዶ መልክ ከደመና መውረድ ይጀምራሉ ።[24]

---

23 ከደመና ማዕከል አጠገብ ያሉት የአየር ሞገዶች ጠንካራ ናቸው ። ምክንያቱም በነርሱ አካባቢ ያሉት ደመናዎች ከቅዝቃዜ ይከላከላሉ ። ይህም በውጭ በኩል ባለው የደመና ድርሻ ውጤት ነው ።

24 the Atmosphere, Anthes and others p. 269 and Elements of Metrology, Miller and Thompson p.141-142




ከላይ በሥዕል 20 ላይ የምንመለከተው የደመና መነባበር ነው ። ደመናው ተከምሮና ዝናቡም ተጨፍልቆ ከውስጡ መውጣት ሲጀምር ። (weather and climate, Bodine, p 123)

ይህን አስመልክቶ አሏህ/ሱ.ወ/በሱረቱ አል-ኑር በአንቀጽ 43 ላይ እንዲህ ይላል፡-

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يُزْجِى سَحَابًا ثُمَّ يُؤَلِّفُ بَيْنَهُۥ ثُمَّ يَجْعَلُهُۥ رُكَامًا فَتَرَى ٱلْوَدْقَ يَخْرُجُ مِنْ خِلَـٰلِهِۦ

ትርጉሙ

***43-<<አሏህ ዳመናን እንደሚነዳ፤ከዚያም እርስበርስ እንደሚያገናኘው ከዚያም የተነባበረ እንደሚያደርገው አላየህምን? ዝናቡም ከውስጡ (እየተጨፈለቀ) ሲወጣ ታያለህ>> ።***

***ሜትሮሎጂስቶች የዚህን የደመና መዋቅር ፤እስትራክቸርና ተግባር ዝርዝር ሊያውቁ የቻሉት በአሁን ጊዜ ነው ።***

***ያውም እንደ ፕሌኖችን፣ሳይተላይቶችን፣ኮምፒዩተሮችን፣ባሎኖችንና ሌሎችንም ዘመናዊ መሳሪያዎችን በመጠቀም ነው ። ኀፋስና አቅጣጫውን ለማጥናት፣የእርጥበት ለውጦችን በመለካት፣ ደረጃዎችን (ሌቭሎችን)ና የአየር ግፊት ለውጦችን በመወሰን ነው ።[25] ቀደም ብሎ የተጠቀሰው የቁርአን አንቀጽ ስለ ዳመናና ዝናብ ከገለጸ በኋላ (አሁን ደግሞ) ስለ በረዶና መብረቅ በሱረቱ አል-ኑር በአንቀጽ 43 ላይ እንዲህ ሲል ይናገራል፥-***

وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن جِبَالٍ فِيهَا مِنۢ بَرَدٍ فَيُصِيبُ بِهِۦ مَن يَشَآءُ وَيَصۡرِفُهُۥ عَن مَّن يَشَآءُۖ يَكَادُ سَنَا بَرۡقِهِۦ يَذۡهَبُ بِٱلۡأَبۡصَٰرِ ﴿٤٣﴾

ትርጉሙም

***43-<<ከሰማይ ውስጥ ካሉ (የደመና) ቁልሎች በረዶን ያወርዳል ። በርሱም የሚሻውን (ክፍል) ይመታል ። ከሚሻውም (አካባቢ) ያስወግደዋል ። የብልጭታውም ብርሃን አይኖችን ሊያጠፋ ይቀርባል>> ።***

***ሜትሮሎጂስቶች እነዚህ ከደመና ክምሮች የሚወርዱ የበረዶ ዝናቦች ከፍታቸው ከ25000 እስከ 30000 ጫማ (ከ4.7 እስከ 5.7 ማይል) እንደሚደርስ ተመራምረው አግኝተዋል ።***[26]አኒህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ እንደገለጸው የደመናውን ቁልሎች እንደ ተራራ ናቸው፤

(وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن جِبَالٍ)

( ሥዕል 21 ላይ ተመልከት)…

---

25 ***ኢእጃዝ አል-ቁርአን አል-ከሪም ፊ ወስፍ አንወኡ አል-ሪያህ አል-ሶሀብ፣አል-መጠር ፤ ማኪ እና ሌሎችም ገጽ 55***


26 **Elements of Metrology, Miller and Thompson p.141**



እዚህ ሥዕል 21 ላይ የምንመለከተው የደመና ቁልል ነው ።

ምናልባት ይህ የቁርአን አንቀጽ ጥያቄን ሊያስነሳ ይችላል፡- አንቀጹ በረዶን መጠቀም ፈልጎ ለምን «የብልጭታ ብርሃን»አለ? ያ ማለት በረዶ መብረቅን ለማመንጨት ዋናው ምክንያት ነው? እስኪ ስለዚህ ነገር የሜትሮሎጂ መጽሐፍ ርዕሱ (Metrology Today) የሚለውን እንመልከት ።

ደመና ውስጥ ካለ አካባቢ በረዶ በሚወርድበት ጊዜ ደመናው ወደ ኤሌክትሪክነት ይለወጣል ። እንዲሁም የፈሳሽ ጠብታዎች የተጋገረ በረዶ (hailstone) ጋረ በመነካካታቸው ብቻ ወደ በረዶነት ይለወጣሉ ። የታመቀ ሙቀትም ይለቃሉ ይላል ።



ይህ የተጋገረ የበረዶ (hailstone) የላይኛው ክፍል ከውቅያኖስ የላይኛው ክፍል ውህደት ከተፈጠረው በረዶ የበለጠ ሞቃትነት አለው ። የተጋገረው በረዶ (hailstone) ከበረዶ ውህደት (crystal) ጋር ሲገናኙ አስፈሪ የሆነ ገጽታ ይፈጥራል ።

ኤሌክትሮኖች የሚጓዙት በጣም ቀዝቃዛ ከሆኑ ነገሮች ወደ በጣም ሞቃት ወደ ሆኑ ነገሮች ነው ፡፡ ስለዚህ የተጋገረው በረዶ ነገቲቭ ቻርጅ የሆናል ፡፡ በተመሳሳይ ሀይለኛ ቅዝቃዜ ከተጋገረው በረዶ (hailstone) ጋር ሲገናኝ በጣም ትናንሽ ስንጣሪዎች ከበረዶ የፖዘቲቭ ቻርጅ ተሰባብሮ ይወጣል ፡፡ እነዚህ ቀላል ክብደት ያላቸውና ፖዘቲቭ ቻርጅ የተደረጉ ትናንሽ ስብርባሪዎች በአየር ሞገድ አማካኝነት ወደ ላይኛው የደመና ክፍሎች ይወጣሉ ፡፡ በነገቲቭ ቻርጅ ላይ የሚቀረው በረዶ በታችኛው ደመና በኩል ይወድቃል ፡፡ በዚህ ሁኔታ በታችኛው በኩል የሚገኘው ደመና ነገቲቭ ቻርጅ ይሆናል ፡፡ እነዚህ ነገቲቭ ቻረጆች እንደ መብረቅ ቻርጅ አልተደረጉም ፡፡[27] ከዚህም በመነሳት በረዶ መብረቅን ለማመንጨት በጣም አስፈላጊ ነው በማለት እንቋጫለን ፡፡

እነዚህ የመብረቅ ኢንፎርሜሽኖች የተገኙት በአሁን ጊዜ ነው ፡፡ እስከ 1600AD የአርስቶትል ሜትሮሎጂ ገዢ ሀሳብ ነበር ፡፡ ከጠቀሳቸው ውስጥ ለምሳሌ ፡- አትሞስፈር ሁለት አይነት መተንፈሻ ይዟል ይል ነበር፣ እርጥብና ደረቅ ፡፡ ደግሞም ነጎድጓድ በጎረቤት ደመና የደረቅ መተንፈሻ ድምጽ ግጭት ነው ፡፡ መብረቅ የደረቅ ትንፋሽ ቃጠሎና ቀጭንና ደካማ እሳት መሰል ነው ፡፡ [28]እነዚህ አንዳንድ የሜትሮሎጂ ሀሳቦች ከአስራ አራት ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቁርአን ወህይ (ተአምር) እስከ ወረደበት ጊዜ ድረስ የነገሱ ነበሩ ፡፡

---

[27] Meteorology Today, Ahrens, p 437

[28] የአርስቶትል ሥራ ወደ እንግሊዘኛ የተተረጎመ ፡- ሜትሮሎጂ ቮልዩም 3 ፣ ሮስና ሌሎችም ገጽ 369a- 369b



شبكة الألوكة - قسم الكتب

## ሸ- በቁርአን ውስጥ ስለተገለፀው ሳይንሳዊ ተአምር የሳይንትስቶች አስተያየት

የሚከተሉት አንዳንድ ስለ ሳይንሳዊ የቁርአን ተአምሮች የተሰጡ የሳይንትስቶች አስተያየት ነው ፡፡ እነዚህ አስተያየቶች ሁሉ ርዕሱ «እውነታው ይህ ነው» ተብሎ ከተሰየመው የቪዲዮ ካሴት የተወሰዱ ናቸው ፡፡ በዚህ የቪዲዮ ካሴት ውስጥ እነዚያ ሳይንትስቶች የሚከተለውን አስተያየታቸውን ሲሰጡ ማየትና ማዳመጥ ትችላለህ፡-(የዚህን ቪዲዮ ኮፒበቀጥታም ሆነ በቪዲዮቴፕ ማየት የፈለገ የሚከተለውን ዌብሳይት በመጎብኘት አስተያየታቸውን መከታተል ይቻላል) ፡፡

www.islam-guide.com/truth

1-ዶክተር T.V.N Persaud; - በማኒቶባ ዩኒቨርሲቲ -ዊንግ-ማኒቶባ - ካናዳ (ይህ ሰው) የሴቶች በሽታና አወላለድ (obstetrics and Gynecology) ፣ የህፃናት በሽታና ህክምና እንዲሁም የአናቶሚክ ሳይንስ ፕሮፌሰር ነው ፡፡ ለ16 አመት የአናቶሚ ዲፓርትመንት ሊቀመንበር ሆኖ አገልግሏል ፡፡ በዚህ ዘርፍ በጣም ታዋቂና የ22 መጽሐፍት ደራሲና ኢዲተር ነው ፡፡ እንዲሁም 181 ሳይንሳዊ ጥናቶችን አስነብቧል ፡፡ በ1991 ካናዳ ውስጥ በአናቶሚ ፊልድ የቀረበለትን ልዩ ሽልማት ተቀብሏል ፡፡ ይህ የJ.C.B. ከካናዳዊያን የናቶሚ እስፔሻሊስት ማህበር የተሰጠ ትልቅ ሽልማት ነበር ፡፡ ዶክተር Persaud ስላደረገው ሳይንሳዊ የቁርአን ተአምራቶች ጥናት በተጠየቀ ጊዜ ፡-

ለኔ የተገለጸልኝ መንገድ ያ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በጣም ተራ ሰው ነበር ማንበብ መጻፍ አይችልም ነበር ፡፡ በእውነቱ መሀይም ነበር ፡፡ እኛ አሁን የምንናገረው ወደ አሥራ ሁለት ክፍለ ዘመን ገደማ ( በአሁን ጊዜ አሥራ አራት ክፍለ ዘመን ያለፈውን ነው) ፡፡ አንድ መሀይም ሰው ጥልቅ ሀሳብን የሚያፈልቅና መግለጫን የሚሰጥ፣ ያንንም አስገራሚ የሚያደርገው በተፈጥሮ ሳይንስ ትክክል መሆኑ ነው ፡፡ እኔ ራሴ ይህ ቀላል ገጠመኝ እንዴት ሊሆን እንደሚችል ማመን አልችልም ፡፡ እዚያ በጣም ብዙ እውነታዎች አሉ ፡፡

እኔ እንደ ዶክተር Moore እነዚህ መግለጫዎች ከጌታ ዘንድ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ የመጡ ራዕዮች ስለ መሆናቸው ለመቀበል ችግር የለብኝም ፡፡ በርግጥ ዶክተር Persaud ብዙ የቁርአን አናቅጽና ሐዲሶችን (ነቢዩ ሙሀመድ የተናገሩትን) በአንዳንድ መጽሐፍቶች ውስጥ ጠቅሶታል ፡፡ እንዲሁም እነዚህን የቁርአን አናቅጽና ሐዲሶችን በብዙ ኮንፍረንሶች አቅርቦታል ፡፡

2. ዶክተር Joe Leigh Simpson; - የሴት ልጅ በሽታና አወላለድ (obstetrics and Gynecology) ክፍል ሊቀመንበርና ፕሮፌሰር እንዲሁም በተባበሩት አሜሪካ -ቴክሳስ-ሆስተን ውስጥ በባይሎር የሜዲሲን ኮሌጅ ውስጥ የቀድሞ የሰው ፍጥረታት ሳይንስ (human Genetics) ፕሮፌሰር ነው ፡፡ ባለፈው ጊዜ በተባበሩት አሜሪካ ተነሲ- መምፊስ (Tennesse, Memphis) በተነሲ (Tennesse) ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሴት ልጅ በሽታና አወላለድ (Ob-Gyn) ዲፓርትመንት ሊቀመንበርና ፕሮፌሰር ሆኖ አገልግሎ ነበር ፡፡ እንዲሁም በአሜሪካ ውስጥ የመሬት ልማት ማህበር ውስጥ ሊቀመንበር ሆኖ አገልግሏል ፡፡ ዶክተር Joe Leigh Simpson ብዙ ሽልማቶችን ተቀዳጅቷል ፡፡ ከነዚህ ሽልማቶች ውስጥ የሴት ልጅ በሽታና አወላለድ (Ob-Gyn) ፕሮፌሰሮች ማህበር በ1992 ተሸልሟል ፡፡ ፕሮፌሰር Simpson የሚከተሉትን የነቢዩ ሙሀመድን/ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲሶች ተምሯል ፡-

**** ከናንተ አንዳችሁ ፍጥሩ (ጽንሱ) በእናቱ ሆድ ውስጥ አርባ ቀን ይሰበሰባል ፡፡*[29]**

**** ጽንሱ አርባ ሁለት ሌሊት ካለፈው በኋላ አሏህ መልአክትን ይልካል ፡፡ (እንዲሁም ጽንሱን) ይቀርፀውና መስመያ፣ማያ፣ቆዳ፣ሥጋና አጥንትን ይፈጥርለታል፡፡ [30]እነዚህን ሁለት የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲሶችን በሰፊው***

---

[29] ሀዲሱን ቡኻርና ሙስሊም ዘግበውታል ፡፡

[30] *ሐዲሱን ቡኻርና ሙስሊም ዘግበውታል ፡፡*

ባደረጉት ጥናታቸው ። ያ የመጀመሪያዎቹ አርባ ቀናቶች የጽንስ - ፍጥረትን ለማቀናበር ልዩ እስቴጅ እንደሆነም አስተውሏል ። በነዚህ ሁለት የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲሶች ምን ያህል እውነትና ትክክል እንደሆነ በጣም ተማርኳል ። ከዚህም በላይ በአንድ ኮንፍረንስ ላይ ይህንን የነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲስ በተመለከተ እንዲህ በማለት ተናግረዋል ፦

እነዚህ የነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሁለት ሐዲሶች ከአርባ ቀናት በፊት የጽንስ ዕድገትን ልዩ የጊዜ ገደብ አስቀምጠውልናል። በተወሰነ የጊዜ ገደብ እንደሆነም ያስተምረናል ። (እንድንዘጋጅ ያስታውሰናል) ።

እንዲሁም ይህን ነጥብ ዛሬ ጠዋት ሁለት ሌላ ተናጋሪዎች በተመሳሳይ ጠቅሰውታል ።እነዚህ ሁለት ሐዲሶች በዚያ በሚጻፉበት ጊዜ በሳይንሳዊ ዕውቀት መሠረት የመነጩ ሊሆኑ አይችሉም ። ያ ማለት በጀነቲክስና ሀይማኖት መካከል ጥል የለም ማለት ነው ። በተጨማሪም ሀይማኖት በአንዳንድ የሳይንሳዊ ነጥቦች ዙሪያ ራዕይን በመጨመር ሳይንስን ሊመራ ይችላል ማለትን እንገነዘባለን ። ካለፉት ብዙ ዘመናት ጀምሮ በቁርአን ውስጥ የተጠቀሱ ዕውቀቶች በአሁን ጊዜ ትክክል መሆናቸው የፀና ነው ። ይህ የሚያረጋግጠው ቁርአን ከአሏህ/ሱ.ወ/ ዘንድ የወረደ መሆኑ ነው ።

3. ዶክተር E.Marshal Johnson; - በተባበሩት አሜሪካ በቶማስ ዩኒቨርሲቲ ጄፈርሰን- ፊላደልፊያ-ፐንሲቫኒያ ፤ የአናቶሚና የባይሎጂ ዕድገት ፕሮፌሰር ነው ። ለ22 አመታት ፕሮፌሰርና የአናቶሚ ዲፓርትመንት ሊቀመንበር ሆኖ አገልግሏል ። የDaniel Baugh የትምህርት ኢኒስቲትዩሽን ዳይሬክተር ሆኖም አገልግሏል ። በተጨማሪም የአስደናቂ ፍጡራን ማህበር ሊቀመንበር ነበር ። ዶክተር ጆንሰን (Johnson) ከ200 እትሞች በላይ ደርሷል ። በ1981 እ.ኤ.አ በደማም ሳውዲ አረቢያ ሰባተኛው የሜዲካል ኮንፍረንስ በሚደረግበት ወቅት ዶክተር ጆንሰን የጥናት ጽሑፉን በሚየቀርብበት ጊዜ እንዲህ አለ፦ (ማጠቃለያ ቁርአን የሚገልጸው የጽንስን ዕድገት ውጫዊ ቅርጽ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን

ለውስጣዊ እስቴጆችም የበለጠ ዋጋ ይሰጣል ። የማህፀን ውስጥ እስቴጆች ፦ አፈጣጠሩን ዕድገቱንና ሌሎችም አጠቃላይ ዘመናዊ ሳይንስ ያወቃቸውን ክስተቶች ሁሉ ያካትታል) ።

በተጨማሪም እንዲህ ይላል፦ <<ሳይንትስት እንደመሆኔ መጠን ማየት የምችላቸውን ነገሮች ብቻ ነው የምወስደው ። የፅንስ ትምህርት (Embryology) ና የባይሎጂ ዕድገትን መረዳት እችላለሁ ። እናም ከቁርአን ውስጥ ለኔ የሚተረጎሙልኝን ቃላቶች መረዳት እችላለሁ ። ከዚህ በፊት ምሳሌ እንደሰጠሁት ወደዚያኛው ዘመን ብንዝ ኖሮ ዛሬ የማውቀውን ያህል አውቅ ነበር እንዲሁም ነገሮችን መግለጽ እችል ነበር ። በቁርአን ውስጥ እንደተገለጸው ነገሮችን መግለጽ አልችልም ። ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እነዚህን ኢንፎረሜሽኖች ያገኟቸው ከሆነ ቦታ ነው የሚለውን ሀሳብ ላለመቀበል አንድም የሚያግድ ምክንያት ያለ አይመስለኝም ። ደግሞም ያ ነቢዩ ሙሀመድን እንዲጽፍ ያስቻለው መለኮታዊ ጣልቃ ገብ ሀሳብ ጋር የሚቃወም ነገር አይመስለኝም) ።[31]

4. ዶክተር William W.Hay በባህር ሳይንትስትነቱ በጣም ታዋቂ ነው ። እርሱ በተባበሩት አሜሪካ በኮሎራዶ ዩኒቨርሲቲ ቦለር (Boulder) ኮሎራዶ ውስጥ የጂኦሎጂካል ሳይንስ ፕሮፌሰር ነው ። ከዚህ ቀደም በተባበሩት አሜሪካ በሚያሚ ዩኒቨርሲቲ -ሚያሚ- ፍሎሪዳ ውስጥ በሮዘንሺያል ትምህርተ ቤት የባህርና የአትሞስፈሪክ ሳይንስ ዲን ሆኖ አገልግሏል ። ቁርአን ስለ ባህር የገለፃቸው እርግጠኛ ነገሮችን በአሁን ጊዜ በባህር ውስጥ ስለ ተገኙ ነገሮች ከዶክተር Hay ጋር ውይይት ከተደረገ በኋላ እንዲህ ይላል፦

<<እንዲህ አይነት ኢንፎርሜሽኖችን እንደ ቅዱስ ቁርአን አይነት በቀደምት መጽሐፍ ውስጥ ተጽፎ መገኘቱ የሚገርም ነው ። የነዚህ ኢንፎርሜሽኖች ምንጭ ከየት እንደሆነ የማውቅበት መንገድ የለኝም ። ነገር ግን እዚህ ላይ እነዚህ ኢንፎርሜሽኖችና ይህን ጥናት ተፈላስፎ ለማግኘትና አንዳንድ የቁርአን አናቅጽን

---

31 ነቢዩ ሙሀመድ/ሲ.ዐ.ወ/ መሀይም ነበረ መጻፍም ሆነ ማንበብ አይችልም ነበር ። ነገር ግን ባልደረቦቹን ቁርአንን እንዲጽፉ ያዛቸው ነበር ።

ለማወቅ መሆኑ በጣም ያስደስተኛል›› ፡፡ ዶክተር Hay ስለ ቁርአን ምንጭ ሲጠየቅ እንዲህ በማለት መለሰ፤
‹‹ጥሩ የግድ መልካም መሆን ያለበት ይመስለኛል›› ፡፡

5. ዶክተር Gerald C. Georinger; በተባበሩት አሜሪካ ዋሽንተን በጆርጅ ታውን ዩኒቨርሲቲ የሜድስን ትምህርት ቤት የኮርስ ዳይሬክተርና በሴል ባይሎጂ ዲፓርትመንት የሜዲካል ኢምቢርዮሎጂ ተባባሪ ፕሮፌሰር ነው ፡፡ በሳውዲ አረቢያ -ሪያድ ስምንተኛው የሳውዲ ሜዲካል ኮንፍረንስ ሲደረግ ፕሮፌሰር Georinger የጥናት ጽሁፉን ሲያቀርብ እንዲህ በማለት ገለጸ፡-
‹‹ጥቅት የቁርአን አናቅጽ የሰው ልጅን ሙሉ ዕድገት የሚገልፁ የውሁድ ሴሎች ከተደባለቁበት ጊዜ ጀምሮ በማህፀን(organogenesis) አማካኝነት እስከሚወለድ ድረስ ያለውን አካቷል ፡፡ ከዚህ ቀደም እንዲህ አይነቱ ልዩ ምዝገባ እንደ ክፍፍልና ሙሉ መግለጫ በግልጽና በተሟላ መልኩ አልተገኘም ፡፡ ሁሉም ባይሆንም በአብዛኛው ይህ ሙሉ መግለጫ ለብዙ ዘመናት ስለ ተለያየ የሰው ልጅ የጽንስ እስቴጅና የጽንስ ዕድገት በቀድሞ ሳይንሳዊ ሥነ ጽሁፍ ውስጥ ተጽፎ ተቀምጧል›› ፡፡

6. ዶክተር ዮሺሂድ ኮዝ፡- በጃፓን - ቶክዮ - ሆንጎ ውስጥ የቶክዮ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰርና በጃፓን - ቶክዮ - ሚታካ ውስጥ የብሔራዊ ፈለክ ጥናት ዳይሬክተር ነው ፡፡ እንዲህም ይላል፡-
‹‹በቁርአን ውስጥ እውነተኛ የፈለክ ጥናት በማግኘቴ በጣም ተደንቅያለሁ ፡፡ በኛ በኩል ዘመናዊ የፈለክ ሳይንትስቶች በጣም ትናንሽ የዩኒቨርስ ቁርጭራጮችን አጥንተዋል ፡፡ በጣም ትንሽ ክፍልን ለመገንዘብ ብዙ ትግል አድርገናል ፡፡ ምክንያቱም ቴሌስኮፖችን በመጠቀም የሰማይን በጣም ጥቅት ፓርቶችን እንጂ ማየት አንችልም ፡፡ (ይህም) ሁሉንም ዩኒቨርስ(አለም) ለማየት ሳናስብ ነው ፡፡ ስለዚህ ቁርአንን ካነበብኩና ጥያቄዎችን ከመለስኩ በሗላ ወደፊት ዩኒቨርስን መርምሬ ማግኘት የምችልበት መንገድ ይመስለኛል›› ፡፡

7. ፕሮፌሰር Tejatat Tejasan;-በታይላንድ - ችያንግ ማይ ውስጥ በችያንግ ማይ ዩኒቨርሲቲ የአናቶሚ ዲፓርትመንት ሊቀመንበር ነው ፡፡

ከዚህ ቀደም ብሎ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ የሜድስን የኮሌጁ ዲን ነበር ። በሳውዲ አረቢያ - ሪያድ ስምንተኛው የሳውዲ ሜዲካል ኮንፍረንስ ሲደረግ ፕሮፌሰር Tejatat ብድግ ብሎ ተነሳና እንዲህም አለ፡- <<በመጨረሻዎቹ ሦስት አመታቶች ውስጥ ለቁርአን ትኩረት መስጠት ጀመርኩ ። ከጥናቴና ከዚህ ኮንፍረንስ ከቀሰምኩት ዕውቀት  በመነሳት ካለፉት አሥራአራት ክፍለ ዘመናት ጀምሮ በቁርአን ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙ ነገሮች ሁሉ የግድ እውነት መሆን አለባቸው ። ያም በሳይንሳዊ አባባል ማስረጃ ሊሆን ይችላል ። ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ማንበብና መጻፍ የማይችል ከመሆኑም ጋር እነዚህን እውነታዎች  ይዞልን የመጣ መልዕክተኛ መሆን አለበት ። ያም እንደ ብርሃን የተገለፀለት በዚያ በፈጣሪ በኩል ነው ። ይህ ፈጣሪ አሏህ መሆን አለበት ። ስለዚህ ላ ኢላሀ ኢል-ሏህ ሙሀመደር-ረሱለል-ሏህ << ከአንድ አሏህ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም ሙሀመድ የአሏህ መልዕክተኛ>> ነው ። የምልበት ወቅት ይመስለኛል ። በመጨረሻም ስለዚህ ልዩና ከፍተኛ የኮንፍረንስ ሥርአት የምሥራች ማለት እወዳለሁ ። (እዚህ ኮንፍረንስ ላይ ብዙ ጥቅሞችን) ቀስሚያለሁ ። በሳይንሳዊና ሀይማኖታዊ ነጥብ ብቻ ሳየሆን ነገር ግን ታዋቂ ሳይንትስቶችን መገናኘቴና በኮንፍረንሱ ከተሳተፉትመካከል አዳዲስ ጓደኞችን መተዋወቄ ለኔ ትልቅ ዕድል ነው ። እዚህ ቦታ በመምጣት ትልቁ የቀሰምኩት ነገር ( ላኢላሀ ኢል-ሏህ ሙሀመደር-ረሱሉል-ሏህ) እና ሙስሊም መሆኤ>> ነው ።  ከነዚህ በቁርአን ውስጥ ካየናቸው ሳይንሳዊ ተአምሮች ምሳሌ በኋላና ከነዚህ ከሳይንትስቶች በኩል ከተሰጡ አስተያየቶች በኋላ እነዚህን ጥያቄዎች ራሳችንን  እንጠይቅ ፡-

* እነዚህ በተለያዩ ዘርፎች አሁን የተገኙ ሳይንሳዊ ኢንፎርሜሽኖች ካለፉት አሥራ አራት ክፍለ ዘመን ጀምሮ በቁርአን ውስጥ የተገለፁት ሁሉ ድንገት የተጠቀሱ ናቸውን ?

* ይህንን ቁርአን ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ወይም ማንም ሰው መድረስ / ማዘጋጀት/ ይችላልን ?

*ሊሆን የሚችለው ብቸኛው መልስ ይህ ቁርአን ከተባረከው አሏህ አንድ በአንድ/ ፊደል በፊደል/ የወረደ ቃል ነው ።*

*(ለተጨማሪ መረጃ ስለ ሳይንሳዊ የቁርአን ተአምሮች በኢንተርኔት ፥ጽሁፎች፥መጽሐፍቶችና ቪዲዮ ካሴት የሚከተለውን ዌብ ሳይት ይጎብኙ ፦www.islam-guide.com/science ወይም በመጽሐፉ መጨረሻ በስተጀርባ በኩል በሚገለጹት አንዱ ድርጅት ይገናኙን) ።*

## 2-እንደ ቁርአን ምዕራፎች አይነት አንድ የቁርአን ምዕራፍን እንኳ ለማዘጋጀት ትልቅ ፉክክር(ፈተና)

ይህን አስመልክቶ አሏህ/ሱ.ወ/ በሱረቱ አልበቀራህ ከአንቀጽ 23-25 ድረስ እንዲህ ይላል፡-

(وَإِن كُنتُمْ فِي رَيْبٍ مِّمَّا نَزَّلْنَا عَلَىٰ عَبْدِنَا فَأْتُوا بِسُورَةٍ مِّن مِّثْلِهِ وَادْعُوا شُهَدَاءَكُم مِّن دُونِ اللَّهِ إِن كُنتُمْ صَادِقِينَ ﴿٢٣﴾ فَإِن لَّمْ تَفْعَلُوا وَلَن تَفْعَلُوا فَاتَّقُوا النَّارَ الَّتِي وَقُودُهَا النَّاسُ وَالْحِجَارَةُ ۖ أُعِدَّتْ لِلْكَافِرِينَ ﴿٢٤﴾ وَبَشِّرِ الَّذِينَ آمَنُوا وَعَمِلُوا الصَّالِحَاتِ أَنَّ لَهُمْ جَنَّاتٍ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا الْأَنْهَارُ)

ትርጉሙም


***23-<< በባሪያችን (ሙሀመድ) ላይ ባወረድነው (በዚህ ቁርአን) ቅንጣት ጥርጣሬ ካለባችሁ እርሱን የሚመስል አንዲት <<ሱራ>> (ምዕራፍ) እንኳ አምጡ ። ከአሏህ ውጭ ረዳቶቻችሁን ጥሩ ፤ (ጥርጣሪያችሁ) እውነትን ያዘለ ከሆነ>> ።***

***24-<< (ይህን) መፈፀም ከተሳናችሁ ወደፊትም መፈፀም አትችሉም፤መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች የሆኑችን ለከሓዲያን የተዘጋጀች እሳት ፍሩ >> ።***

***25-<<(ሙሀመድ ሆይ!) ለነዚያ ላመኑትና ጽድቅ ተግባራትን ለሚያከናውኑት (ጥንቁቆች) ብስራት ንገራቸው ። ወንዞች የሚፈሱባት ገነት ተዘጋጅቶላቸዋል >> ።***

ካለፉት አሥራ አራት ክፍለ ዘመን በፊት ወህይ (ተአምር) ቁርአንን ይዞ ከወረደበት ጊዜ ጀምሮ አቀራረቡ ያማረ፥አንደበተ ርቱዕነቱ፥በአስደናቂነቱ፥የህግጋት ጥበቡ፥የመረጃ እውነታነቱ፥ ትንቢተ እውነታነቱና ሌሎችንም የሙሉነት ባህርያቶች ያሟላ ። አንድም ሰው አንዲትን የቁርአን ሱራ( ምዕራፍ) ማምጣት አልቻለም ።

ለግንዛቤ ያህል በቁርአን ውስጥ በጣም ትንሿ ምዕራፍ (ሱረቱ አል-ከውሰር ቁጥር 108 ነው) ።




ይህች ትንሽ ምዕራፍ የተቀናበረችው ከአሥር ቃላቶች ብቻ ነው ። ያም ሆኖ በፍጹም አንድም ሰው በድሮ ዘመንም ሆነ አሁንም ይህን (ፉክክር )ውድድር መጋፈጥ አልቻለም ።[32]

አንዳንድ ያላመኑ አረቦች እነዚያ ለነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ጠላት የነበሩት ይህንን ውድድር ለመጋፈጥ ሞከሩ እንዲሁም ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እውነተኛ ነቢይ አይደለም በሚል ማስረጃ ለማምጣት ሞከሩ ። ነገር ግን ሳይሳካላቸው ቀረ ። ይህም ሳይሳካላቸው የቀረው ቁርአን በቋንቋቸውና በአነጋገር ዘይቢያቸው ከመውረዱም ጋር ነበር ። ምንም እንኳ በነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ዘመን አረቦች በጣም አንደበተ ርቱዕ ቢሆኑም (አልተሳካላቸውም)።
ግጥምን ባማረ ሁኔታ ይገጥሙም ነበር ። እስካሁንም ይህ ግጥም ይነበባል ። አንባቢውንም ያስገርማል ።

32 አል-ቡርሃን ፊ ኡሉም አል-ቁርአን አል-ዘርከሺ ፤ ቮልዩም 2 ገጽ 224

# 3-ስለ እስላሙ ነቢይ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ተልዕኮ የመጽሀፍ ቅዱስ ትንቢቶች

**የመጸሀፍ ቅዱስ ትንቢቶች ስለ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ተልዕኮ (መናገራቸው) የእስልምናን እውነታነት የሚያስረዱ ናቸው ።**
**ያ በመጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምኑ ምሳሌ ነው ።**




**ይህን አስመልክቶ ነቢዩላሂ ሙሳ (ሙሴ) በኦሪት ዘዳግም በምዕራፍ 18 ከአንቀጽ 18-19 እንዲህ ይላል ፦**

***<<እግዚአብሔርም አለኝ ፦ የተናገሩት መልካም ነው ፤ ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ፤ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፤ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል፤በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ ።>>***

**ከነዚህ አንቀጾች በመነሳት ያ ነቢይ በዚህ ትንቢት በሚከተሉት ሶስት ባህሪዎች የግድ መሰየም አለበት ስንል እንቋጫለን ፦**
**1-እርሱ እንደ ሙሴ/ ሙሳ/ ይሆናል ።**
**2-ያ እርሱ ከእስራኤል ወንድሞች በኩል ማለትም ከኢስማኤል ልጆች ይመጣል ።**

3-አሏህ/ሱ.ወ/ ቃሉን በዚህ ነቢይ የሚያደርግና እርሱም አሏህ ያዘዘውን የሚያውጅ ነው ፡፡
እነዚህን ሶስት ባህሪዎችን በጣም ጥልቅ በሆነ መንገድ እንመርምር ፡፡

## ሀ. እንደ ሙሴ አይነት ነቢይ ፡-

እንደ ነቢዩ ሙሴና ነቢዩ ሙሀመድ(አለይሂማ አስ-ሰላም) የሚመስሉ ሁለት ነቢያቶችን ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ነው ፡፡ ሁለቱም የተሰጣቸው አጠቃላይ ህግና የህይወት ሥርአት ነው ፡፡ ሁለቱም ጠላቶቻቸውን ተጋፍጠው በተአምር መልኩ አሸንፈዋቸዋል ፡፡ ሁለቱም (በህዝባቸው ዘንድ) እንደ ነቢይና አስተዳደር ተቀባይነትን አግኝተዋል ፡፡ ሁለቱም ጠላቶቻቸው ሊገድሏቸው ሲያሴሩ ተሰደዋል ፡፡ ነገር ግን በነቢዩ ሙሴና ሙሀመድ(አለይሂማ አስ-ሰላም) መካከል ያለው መመሳሰል ከላይኛው የመመሳሰል ነጥቦችና ከሌሎችም የውሳኔ ነጥቦች ጋር አይስማማም ፡፡ ለምሳሌ ተፈጥሯዊ ልደት ፥ቤተሰባዊ ኑሮ፥ እንዲሁም የሙሴ(ሙሳ) ና የሙሀመድ(አለይሂማ አስ-ሰላም) ሞት የመሳሰሉት ናቸው ፡፡ ነገር ግን ኢሳ(ኢየሱስ) /አለይሂ አስ-ሰላም/ አልሞተም ፡፡

ከዚህም በላይ የነቢዩላሂ ኢሳ(ኢየሱስ ) /አለይሂ አሰላም/ ተከታዮች ኢሳ እንደ ሙሳና ሙሀመድ (አለይሂማ አስ-ሰላም) ከአሏህ ዘንድ የተላከ ነቢይ ሳይሆን የአሏህ ልጅ ነው ብለው ያምናሉ ፡፡ ሙስሊሞች ግን ኢሳ /ዐ.ሰ/ ነቢይ እንደሆነ ያምናሉ ፡፡

ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት ነቢዩ ሙሀመድን እንጂ ኢሳን አይጠቅስም ፡፡ ምክንያቱም ነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከኢሳ ይልቅ ነቢዩ ሙሳን ይመስላል ፡፡ በሌላ በኩል በዮሐንስ ወንጌል ይሁዶች ሶስት የተለያዩ ትንቢቶችን መረጋገጥ ይጠብቁ እንደ ነበር ይስተዋላል ፡፡

1- የኢየሱስ(ኢሳ) መምጣት 2- የኤሊያስ/ኢልያስ/ መምጣት
3- የነቢዩ መምጣት ፡፡
እነዚህ በዮሐንስ ላይ የቀረቡ ሶስት ጥያቄዎች ግልጽ ናቸው ፡፡ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ /1/ ከ19-21 እንዲህ ይላል፡-

<<አይሁዳም፡- አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት ዘንድ ከኢየሩ ሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት ጊዜ የዩሐንስ ምስክርነት ህ ነው ። መሰከረም አልካደምም እኔ ክርስቶስ አይደለሁም ብሎ መሰከረ እንኪያስ ማን ነህ? ኤሊያስ ነህን? ብለው ጠየቁት አይደለሁም አለ ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም ብሎ መለሰ ።

በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ የመሸጋገሪያ ጥቅሶችን ያየን እንደሆነ በመሸጋገሪያው በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ /1/ በአንቀጽ 21 ላይ <<ነቢይ>> የሚሉትን ቃላቶች እናገኛለን እነዚህ ከትንቢት ጋር የተገናኙ ቃላቶች በኦሪት ዘዳግም በምዕራፍ /18/ በአንቀጽ /15/ እንዲሁም በምዕራፍ /18/ በአንቀጽ /18/ ላይ ተጠቅሰዋል ። ከዚህም በመነሳት በኦሪት ዘዳግም በምዕራፍ /18/ በአንቀጽ /18/ ላይ የተጠቀሰው የኢየሱስ ክርስቶስን ነብይነት የሚገልጽ አይደለም ስንል እንቋጫለን ።

## ለ. ከኢስራኤል ወንድሞች

ለኢብራሂም (አብርሃም) ሁለት ልጆች ነበሩት፡- ኢስማኤልና ይስሃቅ (ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ21) ኢስማኤል የአረብ ህዝቦች አያት ሆነ ። ይስሃቅ ደግሞ የይሁድ ህዝቦች አያት ሆነ ። በትንቢቱ የተነገረለት ነቢይ ከይሁዶች ራሳቸው ሊመጣ አይችልም ። ነገር ግን በወንድሞቻቸው መካከል ማለትም ከኢስማኢል ነው ። ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ የኢስማኢል ዘር ነው ። እርሱ በርግጥ ይህ ነቢይ ነው ።

በትንቢተ ኢሳያስ በምዕራፍ 42 ከአንቀጽ1-13 ደግሞ ስለ አኂህ <<ምርጥ>> ባሪያ ያ የመረጠውና ወደፊት ህግን ይዞ የሚመጣ <<መልዕክተኛ>> ይናገራል ። በትንቢተ ኢሳያስ በምዕራፍ 42 በአንቀጽ 4 ላይ ፡- <<በምድርም ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ ያበራል እንጂ አይጠፋም ...>> አሥራ አንደኛው አንቀጽ የሚገልጸው ከቄዳር የዘር ግንድ የሚጠበቀውን መልዕክተኛ ነው ። ቄዳር የኢስማኤል ሁለተኛ ልጁና ለሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ቅድመ አያት ነው ። (ኦሪት ዘፍትረት ምዕራፍ 25 አንቀጽ 13)

## ሐ. አሏህ ቃሉን በዚህ ነቢይ አፍ ያደርጋል፡-

በርግጥ አሏህ ቃሉን አስቀምጧል (እርሱም ቁርአን አል-ከሪም ነው) በውነቱ በሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ አፍ ላይ አድርጓል ። ለሙሀመድ ቃሉን እንዲያስተምረው አሏህ ጂብሪልን ላከው ከዚያም ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ከጂብሪል እንደሰማው ሰዎችን ያጽፋቸዋል ። ስለዚህ የቁርአን ቃላቶች የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ቃል አይደሉም ። ከራሱ ሀሳብ የፈለቀ አይደለም ። ነገር ግን በመልአኩ ጂብሪል አማካኝነት ነው ። ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ በህይወት እያለና በቁጥጥሩ ሥር ሆኖ ባልደረቦቹ (ሶሃባዎቹ) እነዚህን ቃላት በቃላቸው አንብበው ይዛሉ ። በተጨማሪም ይጽፉ ነበር ።

***በኦሪት ዘዳግም በምዕራፍ 18 በአንቀጽ 19 ላይ ያለውን ማስተዋል ይቻላል ፡- <<በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ ።>>*** ይህ ነቢይ እርሱ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ነው ።

(ስለ ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጨማሪ መረጃ የፈለገ ይህንን ዌብ ሳይት ይጎብኝ፡- (www.islam-guide.com/mib)

## 4. የወደፊት ክስተቶችን የሚጠቅሱ የቁርአን አንቀጾችና ከዚያም ቆይተው የተሳኩ

ቁርአን ከተነበያቸው ክስተቶች ውስጥ አንዱ ምሳሌ፡- ሮማዎች በፐርሺያዎች ከተሸነፉ በኋላ ከሶስት እስከ ዘጠኝ አመት ባለ ጊዜ ውስጥ ማሸነፋቸው ነው ። ይህንንም አስመልክቶ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አር-ሩም ከአንቀጽ 2-4 እንዲህ ይላል ፡-

(غُلِبَتِ ٱلرُّومُ ۝٢ فِيٓ أَدۡنَى ٱلۡأَرۡضِ وَهُم مِّنۢ بَعۡدِ غَلَبِهِمۡ سَيَغۡلِبُونَ ۝٣ فِي بِضۡعِ سِنِينَۗ )

ትርጉሙ

***2- <<ሮማ ተሸነፈች***
***3- (ከዐረቢያ) ቅርብ በሆነችው ምድር /ግዛት/ ውስጥ እነርሱ ከተሸነፉ በኋላ (መልሰው) ያሸንፋሉ ።***
***4- በጥቂት አመታት ጊዜ ውስጥ ።>>***

እስኪ ስለነዚህ ጦርነቶች ታሪክ ምን እንደሚነግረን እንይ ። ርዕሱ History of the Byzantine State ፡ በሚለው መጽሐፍ ላይ ፡- የሮም ወታደር በአንጺኪያ (Antioch) በ 613 በሐይል ተሸነፈ ። በዚያም ውጤት ፐርሺያዎች በሁሉም አቅጣጫ በፍጥነት ጫና አደረጉ ። በዚያን ጊዜ ሮማዎች ፐርሺያዎችን ያሸንፋሉ የሚል እምነት አንድም ሰው አልነበረውም ። ነገር ግን ቁርአን ከሶስት እስከ ዘጠኝ አመታት ባለው ጊዜ ውስጥ ድልን እንደሚቀዳጁ ተናግሯል ። በ 622 እ.ኤ.አ ሮማዎች ከተሸነፉ ከዘጠኝ አመት በኋላ ሁለቱ ሀይሎች (ሮማዎችና ፐርሺያዎች) በአርሚኒያ ምድር ላይ ተገናኙ ። ውጤቱም ሮማዎች በፐርሺያዎች ቆራጥ ድልን ተቀዳጁ ። (ያም ) ሮማዎች ያሸነፉት በ613 እ.ኤ.አ ከተሸነፉ በሗላ ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር ። በዚህ መልኩ ነበር  አኗህ በቁርአኑ የተናገረው ትንቢት ሙሉ በሙሉ የተረጋገጠው ።

እንዲሁም ሌሎች የወደፊት ክስቶችን የሚጠቅሱና ከዚያም በተግባር የተረጋገጡ አያሌ የቁርአን አንቀጾችና የነቢዩ ሙሀመድ (ሰ.ዐ.ወ) ሀዲሶች ይኖራሉ ።

## 5- በነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እጅ የተከሰቱ ተአምራቶች

በርግጥም በአኗህ ፈቃድ ተአምራቶች በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ተከስተዋል ። እነዚህን ተአምራቶች በብዙ የሚቆጠሩ ሰዎች ተመልክተውታል ። ለምሳሌ ያህል፡-

* ሙሽሪኮች መካ ውስጥ ነቢዩ ሙሀመድን /ሰ.ዐ.ወ/ ተአምር እንዲያመጡ ሲጠየቋቸው የጨረቃ መሰንጠቅን አሳዩዋቸው ። (ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል)
* ሌላው ተአምር በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ጣቶች መካከል ውሃ መፍሰስ ነበር ። (በዚያን ጊዜ የነቢዩ ባልደረቦች/ሶሃቦች/ ውሃ ተጠምተው ነበር ) ። በዕቃው ጥቅት ውሃ በስተቀር የለም ። (ሶሃቦችም) ወደ ነቢዩ ሙሀመድ በመምጣት በዕቃው ላይ ያለው ሲቀር ውዱዕ ለማድረግም ሆነ ለመጠጥ የሚሆን ምንም ውሃ እንደሌለ ነገሯቸውና ነቢዩ ሙሀመድም /ሰ.ዐ.ወ/ እጃቸውን በዕቃው ውስጥ አስገቡ ። ከዚያም በጣቶቻቸው መካከል ውሃው መጉረፍ ጀመረ ። ከዚያም እነርሱ (ውሃውን) ጠጡት ውዱዕም(ለፀሎት) አደረጉ ። (የዚያን ጊዜ) እነርሱ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሶሃቦች ነበሩ ። (ቡኻሪይ ዘግበውታል)
ሌሎችም ብዙ ተአምራቶች በነቢዩ ሙሀመድ ተከስተዋል ።

## 6- የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ የኑሮ ህይወት ቀላልነት

የነቢዩ ሙሀመድን/ሰ.ዐ.ወ/ ህይወት ወይም ኑሮ ወደ ነቢይነት ከመላካቸው በፊትና እንደ ነብዩ መልዕክታቸውን ከጀመሩ በኋላ ያለውን ስናነፃጽር ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ ነቢይ የነበረው ቁሳቁስን፥ ትልቅነትን ወይም ሥልጣንን ለማትረፍ ነው የሚለውን አባባል አእምሯችን ሊገምተው የማይችል መሆኑን እንረዳለን ።

ነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ እንደ ነቢይ ከመካከላቸው በፊት ምንም የፋይናንስ ችግር አልነበረባቸውም ። እንደ ስኬታማና ዝነኛ ነጋዴ ጥሩ ገቢ ያስገቡ ነበር ። ለነቢይነት ከተላኩ በኋላ ቁሳቁሳቸው እየቀነሰ መጣ ። ያንንም የበለጠ ግልጽ ለማድረግ እነዚህን ስለ ነቢዩ ሙሀመድ / ሰ.ዐ.ወ/ የተነገሩትን ነገሮች እናቅርብ፡-

* የነቢዩ ሙሀመድ / ሰ.ዐ.ወ/ ባለቤት አኢሻ/ረ.ዐ/ ለእህቷ ልጅ ኡርዋ <<የእህቴ ልጅ ሆይ ! በነቢዩ ሙሀመድ / ሰ.ዐ.ወ/ ቤቶች ውስጥ (ለምግብ ማብሰያ) እሳት ሳይነድ በሁለት ወር ውስጥ ሶስት /አዳዲስ / ጨረቃዎችን እናያለን ፡፡>> አለች ፡፡ የእህቷ ልጅም <<አክስቴ ሆይ ! ምንድን ነው የሚያኖራችሁ ?>> አልኩኝ ፡፡ እሷም <<ሁለቱ ጥቁር ነገሮች ፤ቴምርና ውሃ ናቸው ፡፡ ነገር ግን ከአንሷር የሆኑ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጎረቤቶች ነበሩ ፡፡ (እነዚህ ጎረቤቶች) ወተት የሚሰጡ ግመሎች ነበራቸው እነርሱም ለነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ ከወተታቸው ይሰጧቸው ነበር፡፡ከዚያም ለኛ ያጠጡን ነበር ፡፡>> አለች ፡፡ (ቡኻሪይ ዘግበውታል) ፡፡

* አነስ ቢኑ ማሊክ/ረ.ዐ/ እንዲህ አለ፡- ነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ ህይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ ከጥሩ ዱቄት የተጋገረ ዳቦን አላዩም ፡፡

* የነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ ባለቤት እንዲህ አለች፡- ነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ የሚተኙበት ማቴሪያል ከቴምር ዛፍ ቅርንጫፍ የተሞላ የቆዳ ፍራሽ ላይ ነበር የሚተኙት ፡፡( አህመድ ዘግበውታል)

* ከአምር ኢብን አል-ሃሪስ ከነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ ባልደረቦች ከአንዱ ባወራው ሀዲስ ላይ እንዲህ ይላል፡- ነቢዩ ሙሀመድ/ ሰ.ዐ.ወ/ ገንዘብም ሆነ ሌሎች ነገሮችን አልተውም ፡፡ ነጭ የሚጋልቧት በቅሏቸው ፤የጦር መሣሪያቸውና ለበጎ አድራጎት የተውት ቁራጭ መሬታቸው ሲቀር ፡፡ (ነሳኢ ዘግበውታል) ፡፡

ምንም እንኳ የሙስሊሞች ግምጃ ቤት በትዕዛዛቸው ቢሆንም መልዕክተኛው ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እነዚህን አስከፊ ህይወቶች እስኪሞቱ ድረስ (ችለው) አሳልፈዋል ፡፡ አብዛኛዎቹ የአረብ ደሴት ነዋሪዎች የነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ህይወት ከማለፉ በፊት ወደ

እስልምና ገብተው ነበር ። ወደ ነቢይነት ከተላኩ ከ18 አመት በኋላ ሙስሊሞች ድልን ተቀዳጅተዋል ።

መልዕክተኛው/ሰ.ዐ.ወ/ ነቢይነታቸውን ያወጁት ትልቅነትን (ክብርን) ወይም ሥልጣንን ለማግኘት ሊሆን ይችላልን? ብዙን ጊዜ ደስታና ሥልጣን ጥሩ ከመመገብ ፣እጅግ ያማረ ልብስ ከመልበስ ፣ ድንቅ ቤተ መንግስትና ጋርዶች ጋር የተያያዘ ነው ።ከዚህ ነገሮች አንዱም በነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ተግባራዊ ይሆናልን ?

ለጥያቄው መልስ እንዲሆን የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ የህይወት ታሪክ በጥቅቱ ለመግለጽ እንሞክራለን ፡-

የነቢይነት ሀላፊነታቸው ፣አስተማሪነታቸው፣ አስተዳዳሪነታቸውና ዳኝነታቸው እንዳለ ሆኖ እያለ ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ፍየላቸውን ያልቡ ነበር ፣ልብሳቸውን ይሰፉ ነበር፣ጫማቸውን ይወለውሉ ነበር፣በቤት ውስጥ ቤተሰባቸውን ያግዙ ነበር፤ ድሃዎችና በሽተኛዎችን ይጠይቁ ነበር ። እንዲሁም ባልደረቦቻቸውን የምሽግ ቦይ በመቆፈርና አሸዋን ከነርሱ በማጓጓዝ (በማንቀሳቀስ) አግዘዋል ። የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ህይወት የቀላልነትና ትሁት ሞዴል ነበር ። (ዘገባው የሙስነድ አህመድና ሶሂህ አል-ቡኻሪይ ነው ) ።

የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ተከታዮች /ሶሃባዎች/ ይወዷቸው፣ ያከብሯቸው እንዲሁም እስከሚያስገርም ድረስ ይተማመኑባቸው ነበር ። ነገር ግን ሁል ጊዜ መልዕክተኛው/ሰ.ዐ.ወ/ መለኮታዊነት ለአሏህ ብቻ እንጂ ለእሳቸው እንዳልሆነ አጠንክረው ያስተምሩ ነበር ።

ከነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ባልደረቦች አንዱ የሆነው አነስ ኢብን ማሊክ /ረ.ዐ/ እንዲህ አለ፡- የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ባልደረቦች ከእሳቸው የበለጠ አንድም ሰው አልወደዱም ።ነገር ግን መልዕክተኛው ወደ ሶሃባዎቹ በሚመጡ ጊዜ (ከመቀመጫቸው) አይነሱላቸውም ነበር ሌሎች ህዝቦች ለታላቆቻቸው እንደሚያደርጉት ። (ሀዲሱ የተወራው ከሙስነድ አህመድ ነው) ።

እስላም እዚህ ክንዋኔ ከመድረሱ በፊት ለረጅም ዘመናት በነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እና በባልደረቦቻቸው ስቃይና ስደት ደርሶባቸዋል ።

ከሙሽሪክ ሹማምንቶች (በኩል) (ኡትባ) መልዕክተኛ ሆኖ መጣ እንዲህም አላቸው ፦ <<ገንዘብ የምትፈልግ ከሆነ በቂ ገንዘብን እንሰበስብልሃለን ። ከዚያም ከኛ የበለጠ ሀብታም ትሆናለህ ። መሪነትን(ሥልጣንን) የምትፈልግ ከሆነ መሪ እናደርግሃለን ። ያለ አንተ ውሳኔን አንወስንም ። ንግሥናን የምትፈልግ ከሆነ ንጉሥ እናደርግሃለን ።>>

ለዚህ ሁሉ መልስ ከነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ የሚጠበቅ የነበረው አንድ ነገር ነበር ይህም ሰዎችን ወደ እስልምና መጥራታቸውንና ከአሏህ ውጭ ሌላ አጋር አድርገው እንዳይገዙ የሚያስተላልፉትን ጥሪ ማቆም(መተው) ነበር ። ይህን ስጦታ ማቅረብ አንድ አለማዊ ትቅምን ለሚከተል መፈታተን አይሆንምን? ለነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ይህ ስጦታ ከሙሽሪኮች ሲቀርብላቸው ተከራክረዋልን? ነቢዩ/ሰ.ዐ.ወ/ ይህንን ስጦታ ያልተቀበሉት ትልቅ ጥቅምን ለማግኘት የድርድር በሩን ክፍት ለማድረግ የተጠቀሙት እስትራቴጂያዊ ዕቅድ ነውን? በፍፁም እንዲያውም መልሳቸው፦ (በአሏህ ስም እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው) እናም ለኡትባ ሱረቱ አል-ፉሲለት ከአንቀጽ 2-4 ያለውን አነበቡለት እነዚህ አንቀጾች እንደሚከተሉት ናቸው፦

( تَنزِيلٌ مِّنَ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿٢﴾ كِتَٰبٌ فُصِّلَتۡ ءَايَٰتُهُۥ قُرۡءَانًا عَرَبِيًّا لِّقَوۡمٍ يَعۡلَمُونَ ﴿٣﴾ بَشِيرًا وَنَذِيرًا فَأَعۡرَضَ أَكۡثَرُهُمۡ فَهُمۡ لَا يَسۡمَعُونَ ﴿٤﴾ )

<u>ትርጉሙ</u>

***2- << (ቁርአን) እጅግ በጣም ርህሩህና አዛኝ ከሆነው (አምላክ) የተወረደ መልዕክት ነው >> ።***

***3- <<አንቀጾቹ ግልጽ የተደረጉና የተብራሩ የሆነ መጽሐፍ ነው ። በዐረቢኛ ቋንቋ (የወረደ) ቁርአን ነው ። ለሚያውቁ ሰዎች >> ።***
***4- <<አብሳሪና አስፈራሪም ነው ። ይሁንና አብዛኞቹ (መልዕክቱን) ከማስተንተንና ከመተግበር ሸሸተዋል ። እነርሱም ፈጽሞ አይሰሙም>> ።***

በሌላ ጊዜ አጎትየው ወደ እስልምና ሰዎችን መስበካቸውን እንዲያቆሙ ሲጠይቋቸው መልስ ሲሰጡ የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ መልስ ቆራጥ ነበር ፦ <<አጎቴ ሆይ! ወሏሂ ፀሐይን በቀኝ እጄ ጨረቃን ደግሞ በግራ እጄ ቢያስቀምጡልኝ አሏህ ድልን እስከሚነሳ ድረስ ወይም ለርሱ በመከላከል እስክሞት ድረስ ይህን ጉዳይ (ሰዎችን ወደ እስልምና መጥራት) አልተውም አሉ ።[33]

ሙሀመድን/ሰ.ዐ.ወ/ ና ባልደረቦቻቸውን ለአሥራ ሶስት አመት ማሰቃየትና ማሳደድ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ሙሽሪኮች ብዙ ጊዜ ነቢዩ ሙሀመድን/ሰ.ዐ.ወ/ ለመግደል ሙከራ አድርገዋል ። አንድ ጊዜ ትልቅ ቋጥኝ በራሳቸው በመጣል ለመግደል ሙከራ አድርገዋል ። በሌላ ጊዜ ምግባቸውን በመርዝ በመበረዝ ለመግደል ሙከራ አድርገዋል ።[34] ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እነዚህን የህይወት ስቃይና መሰዋዕት የተቋቋሙበት ምክንያት ምንድን ነው? ከዚህም በላይ ትሑትነታቸውና መሳፍንትነታቸው ያ በታላቅ ክብራቸው ጊዜ ያሳዩት በምን ሊገለጽ ይችላል? (ታዲያ) ስኬታቸውን (ያገኙት)በብልህነታቸው ሳይሆን በአሏህ ዕርዳታ ብቻ እንደሆነ ጽኑ እምነት ነበራቸው ። ሥልጣን ለጠማውና እኔ እኔ ለሚል ሰው (ክብርን ለሚወድ ሰው) እነዚህ ባህሪዎች ሊሆኑ ይችላሉን?

---

[33] አል-ሲረቱ አል-ነበዊያህ ኢብን ሂሻም ቮልዩም 1
[34] አል-ሲረቱ አል-ነበዊያህ ኢብን ሂሻም ቮልዩም 1

## 7-እስልምና እየተስፋፋ መምጣት

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ የእስልምናን እውነተኛነት የሚያመለክቱ ነገሮችን መግለጽ አስፈላጊ ምክንያት ነው ፡፡ እስልምና በተባበሩት አሜሪካና በአለም አጠቃላይ በመስፋፋት ፈጣን ሀይማኖት እንደሆነ በደንብ ይታወቃል ፡፡ ሚከተሉት አንዳንድ ነጥቦች የእስልምናን ሀይማኖት መስፋፋት የሚያመለክቱ ናቸው ፡፡

* <<ኢስላም በአሜሪካ ውስጥ ካሉ ሀይማኖቶች በፍጥነት የሚስፋፉ ሀይማኖት ነው ፡፡ለብዙ ህዝቦች መሪና ዐምደ ጽኑ ሆኗል (Hillary Rodham Clinton)…>> ሎስ አንጀለስ ታይምስ ጋዜጣ…[35]

* << ሙስሊሞች በአለም ላይ በፍጥነት የሚስፋፉ (Growing) ግሩፖች ናቸው ፡፡>> (The population Reference Bureau, USA today)[36]

* <<...እስልምና በዚህ ሀገር በፍጥነት ከሚስፋፉ ሀይማኖቶች ነው ፡፡ >> (Geraldine Baum, Newsday Religion Writer, Newsday)[37]

* <<እስልምና በአሜሪካ ውስጥ በፍጥነት የተስፋፋ ሀይማኖት ነው ፡፡>> … (Aril. Goldman)…ኒዮርክ ታይምስ ጋዜጣ…[38]

---

35 Larry B.Stammer, times Religion Writer, <<First lady Breaks Ground with Muslims>> Los Angeles times, home Edition part B May 31, 1996, p3

36 Timothy Kenny <<Elsewhere in the world, >> USA today, Final Edition, News section February 17, 1989, p 4a

37 Geraldine Baum <<For love of Allah>> Newsday, Nassau and Suffolk Edition, March 7, 1989 p, 4

38 Aril. Goldman, <<Main stream Islam rapidly Embranced by Black Americans, >> New York Times, Late city Final Edition February 21, 1989, p.1

ይህ የእስልምና በይፋ መስፋፋት የሚያመለክተው እስልምና በእውነቱ ከአሏህ ዘንድ የመጣ መሆኑ ነው ፡፡ እነዚህ በብዙ የሚቆጠሩ አሜሪካዎችና የሌሎች የተለያዩ ሀገር ህዝቦች ወደ እስልምና ሀይማኖት የገቡት እስልምና ትክክለኛ መሆኑን ጠንቅቀው ሳያስቡና በጥልቅ ሳያሰላስሉ ነው ብሎ መገመት የማይመስል ነው ፡፡ እነዚህ እምነቱን የተቀበሉ የተለያየ ሀገር ህዝቦች ሳይንትስቶች ፣ፕሮፌሰሮች፣ፈላስፋዎች፣ጋዜጠኞች፣ አክተሮችና አትሌቶች ናቸው ፡፡

በዚህ ምዕራፍ የተገለፁ እውነታዎች ቁርአን የአሏህ ቃል መሆኑና ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ በእውነት ከአሏህ ዘንድ የተላኩ መልዕክተኛ ፤ እንዲሁም እስልምና ፍጹም ከአሏህ የሆነ ሀይማኖት መሆኑን የሚገልፁልን አንዳንድ ማስረጃዎች ናቸው ፡፡

# ክፍል ሁለት

## አንዳንድ የእስላም ትሩፋቶች

እስልምና ለግለሰብና ህብረተሰቡ ብዙ ረድኤቶችን ይሰጣል ፡፡ ይህ ምዕራፍ በእስልምና አማካኝነት ግለሰቡ የሚጠቀማቸውን ጥቅሞች እንደ ሚከተለው ይገልጻል ፡-

## 1- ዘላለማዊ የጀነት በር

አላህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-በቀራህ በአንቀጽ 25 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(وَبَشِّرِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أَنَّ لَهُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۖ)

ትርጉሙ

***25- « (ሙሐመድ ሆይ!) ለነዚያ ላመኑትና ጽድቅ ተግባራትን ለሚያከናውኑት (ጥንቁቆች) ብስራት ንገራቸ ወንዞች የሚፈሱባት ገነት ተዘጋጅቶላቸዋል» ፡፡***

እንዲሁም አላህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ሀዲድ በአንቀጽ 21 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(سَابِقُوٓاْ إِلَىٰ مَغۡفِرَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ وَجَنَّةٍ عَرۡضُهَا كَعَرۡضِ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ أُعِدَّتۡ لِلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ)...

ትርጉሙም

***21- «የጌታቻሁን ምህረትና ስፋቷ እንደ ሰማይና ምድር ስፋት የሆነውን ገነት ለመጎናፀፍ ተሽቀዳደሙ ፡፡***

***ለነዚያ በአሏህና በመልዕክተኛው ላመኑት ተዘጋጅታለች ።»***

መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ አሉን ፦«እኔ ከገሀነም የሚወጡትን የመጨረሻ የገሀነም ሰዎችን አውቃለሁ ። አንድ ሰው ከገሀነም በአፍጥሙ ተገልብጦ ይወጣል ። (ይህን ሰው) አሏህ /ሱ.ወ/ እንዲህ ይለዋል፦ ሂድ ወደ ገነት ግባ፤ወደ ገነት ይመጣና የሞላች ትመስለውና ይመለሳል ። እንዲህም ይላል፦ ጌታዬ ሆይ (ገነቷ) ሞልታ አገኘኋት ፤አሏህም ሂድ ወደ ገነት ግባ ይለዋል ወደ ገነቷ ይመጣና የሞላች ትመስለውና ይመለሳል ። እንዲህም ይላል፦ ጌታዬ ሆይ ! ሞልታ አገኘኋት (ሲል) ሂድ ወደ ገነት ግባ ላንተ የአዱንያን አሥር የሚሆኑ ገነቶች አሉልህ ይለዋል ።» (ሐዲሱን ቡኻሪይ ዘግበውታል)

መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ ይላሉ፦ «በአሏህ መንገድ ጂሃድ ጠዋት ወይም ማታ መውጣት ከአዱንያና በውስጧ ካሉ ነገሮች (ሁሉ )የተሻለ ነው ። ከናንተ የአንዳችሁ ቀስት ክፍተት ወይም በገነት ውስጥ የአንድ እግር ቦታ ከአዱንያና በውስጧ ካሉ ነገሮች ሁሉ የተሻለ ነው ። » (ሀዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል) ።

አሁንም እንዲህ ይላሉ፦ አሏህ /ሱ.ወ/ እንዲህ አለ፦ «ለመልካም ባሪያዎቼ አይን አይታ የማታውቀውን ጆሮ ሰምቶ የማያውቀውን በሰው ልጅ አእምሮ ታስቦ የማይታወቀውን አዘጋጅቼለታለሁ ። » (ሀዲሱን ቡኻሪይ ዘግበውታል) ።

መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ ከገነት ሰዎች አንዱ በአለም ላይ በጣም ችግረኛ ሰው ሆኖ ያመጡትና በገነት ውስጥ (የአሏህን ፀጋ) ያስነኩታል ። እንዲህም ይባላል፦ «አንተ የአደም ልጅ ሆይ ! ችግር አጋጥሞህ ያውቃል? መከራን አሳልፈህ ታውቃለህ ? እርሱም ወሏሂ(በአሏህ እምላለሁ) ጌታዬ ሆይ ! ችግር ደርሶብኝ አያውቅም ። መከራም አጋጥሞኝ አያውቅም ። » (ሀዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል) ።

ወደ ገነት ስትገባ ያለ ህመም ወይም ያለ ሀዘን ወይም ያለ ሞት በጣም ደስተኛ ሆነህ ትኖራለህ ። ዘላለማዊ ኑሮ ትኖራለህ ።

**ይህን አስመልክቶ አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኒሳእ በአንቀጽ 57 ላይ እንዲህ ይላል፡-**

(وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ سَنُدۡخِلُهُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ لَّهُمۡ فِيهَآ أَزۡوَٰجٞ مُّطَهَّرَةٞۖ وَنُدۡخِلُهُمۡ ظِلّٗا ظَلِيلًا ۝٥٧ )

ትርጉሙ

***57- ‹‹እነዚያን ያመኑትንና መልካም ተግባራትን የፈፀሙትንም ከሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በእርግጥ እናስገባቸዋለን ።ከውስጣቸውም ዝንተ አለም ይኖራሉ ። ለነርሱ ከውስጣቸው ንጹሓን ሚስቶች ይኖራቸዋል ። ዘውትር የሚጠለሉበት ጥላ ውስጥም እናስገባቸዋለን ።***

**ስለ ጀነት ወይም ከሞት በኋላ ስላለው ህይወት የበለጠ መረጃ እባክዎ ይህንን ቬብ ሳይት ይጎብኙ፡-**
**www.islam-guide.com/herafter**

## 2- ከገሀነም እሳት መዳን

አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኢምራን በአንቀጽ 91 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَمَاتُواْ وَهُمۡ كُفَّارٞ فَلَن يُقۡبَلَ مِنۡ أَحَدِهِم مِّلۡءُ ٱلۡأَرۡضِ ذَهَبٗا وَلَوِ ٱفۡتَدَىٰ بِهِۦٓۗ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ﴿٩١﴾ )

<u>ትርጉሙ</u>

***91- <<እነዚያ የካዱትና ክህደት ውስጥ እንዳሉ የሞቱት ከነርሱ አንዳቸው (ራሱን ከቅጣት ለማዳን) ምድርን የሚሞላ ወርቅ ቤዛ ቢያቀርብ ተቀባይነት የለውም ። (ከአሏህ ቅጣት የሚያድናቸው አንድም) ረዳት አያገኙም ።***

ስለዚህ ገነትን ለመግባትና ከገሀነም ለመዳን አንድ ዕድል ነው ። ምክንያቱም አንድ ሰው ከሀዲ ሆኖ ከሞተ እንደገና ለማመንና ወደዚህ አለም ለመመለስ ሌላ ዕድል የለውም ። አሏህ/ሱ.ወ/ ይህን አስመልክቶ በቁርአን ውስጥ የትንሳኤ ቀን ለከሀዲዎች ምን እንደሚከሰትባቸው በሱረቱ አል-አንዓም በአንቀጽ 27ላይ እንዲህ በማለት ጠቅሶታል ፡-

وَلَوۡ تَرَىٰٓ إِذۡ وُقِفُواْ عَلَى ٱلنَّارِ فَقَالُواْ يَٰلَيۡتَنَا نُرَدُّ وَلَا نُكَذِّبَ بِـَٔايَٰتِ رَبِّنَا وَنَكُونَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٢٧﴾

<u>ትርጉሙም</u>

***27- <<ከእሳት ላይ እንዲቆሙ በተደረጉ ጊዜ (ሁኔታቸውን) ብታይ ኖሮ (ትዕይንቱ በጣም ይዘገንንህ ነበር)***

*(ወደ ምድረ ዓለም) ብንመልስ (እንዴት መልካም ነው) የጌታችንን አናቅጽ አናስተባብልም ፤በአማኞችም እንሆን ነበር ።›› ይላሉ ።*

*ለአንድም ሰው ንሳህ እንዲገባ ሁለተኛ ዕድል አይሰጠውም ።*

የአሏህ መልዕክተኛ /ሰ.ዐ.ወ/ ‹‹የትንሳኤ ቀን ከገሀነም ሰዎች አንዱን በአለም ላይ ደስተኛ የነበረ ሰውን ያመጡትና አንድ ጊዜ በገሀነም ውስጥ ያስነኩትና ከዚያም የአደም ልጅ ሆይ ! መልካም ነገርን አይተህ ታውቃለህ ን? መልካም ፀጋን አሳልፌህ ታውቃለህን ? ይባላል ። እርሱም ጌታዬ ሆይ ! በፍጹም አላውቅም ።›› ይላል ። (ሀዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል) ።

## 3-እውነተኛ ደስታና ውስጣዊ ሰላም

ቀጣይ ለሆነውና ለዚህ ዓለም ፈጣሪ በመሸነፍ እውነተኛ ደስታና መንፈሳዊ ሰላምን ማግኘት ይቻላል ። ይህን አስመልክቶ አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አር-ራዕድ በአንቀጽ 28 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ﴿٢٨﴾ )

ትርጉሙ

***28- ‹‹እነዚያ ያመኑትን፤ልቦቻቸውም አለህን በማስታወስ የሚረኩትን (ይመራል) ። አዋጅ ልቦች አላህን በማስታወስ ይረካሉ ።››***



በሌላ በኩል ከቁርአን የምርቅ ሰው በዚህ አለም ላይ ችግረኛ ሆኖ ይኖራል ። ለዚህም ማስረጃ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አጥ-ጧሀ በአንቀጽ 124 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِى فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ أَعْمَىٰ ﴿١٢٤﴾)

ትርጉሙም

**124- «ግና ከመልዕክቴ ያፈገፈገ ህይወቱ ጭንቅ የበዛበት ይሆናል ። በትንሳኤ ቀንም እውር አድርገን እንቀሰቅሰዋለን ።»**

ይህም አንዳንድ ሰዎች ምን ያህል ራሳቸውን እንደሚያጠፉ ነው የሚገልፀው ። ምንም እንኳ ማቴርያል ተመቻችቶላቸው ቢሆንም ። ለምሳሌ ፡ Cat Stevens ተመልከት (ይህ ሰው) (በአሁኑ ጊዜ ሰልሞ ስሙ ዩሱፍ አል-ኢስላም ሆኗል) ። ከዚህ ቀደም ታዋቂ የፖፕ ዘፋኝ ነበር ። አንዳንድ ጊዜ በአንድ ሌሊት ውስጥ ከ150,000 ዶላር በላይ ያገኝ ነበር ። እስልምናን ከተቀበለ በኋላ በማቴሪያል ክንውን ያላገኘውን እውነተኛ ደስታና ሰላምን አገኘ ። ወደ እስልምና የገቡ ሰዎችን ታሪክ ለማንበብ ከፈለክ የሚከተለውን ዌብ ሳይት ጎብኝ ወይም «ለምን እስልምና ብቻ የኛ ምርጫ ሆነ» www.islam-guide.com/stories

(Why Islam our only choice) በዚህ ዌብ ሳይት ይህን መጽሐፍ ስለነዚያ ሰዎች ሀሳብና ስሜት ታነባለህ ። እነዚያ የተለያዩ ሀገር ሰዎች የተለያየ አስተዳደግና የትምህርት ደረጃ ያላቸው ናቸው ።

## 4- ወደ አላህ ንሰሀ በመግባት ያለፉትን ወንጀሎችን በሙሉ መማር

አንድ ሰው እስልምናን ከተቀበለ አላህ/ሱ.ወ/ ያለፈውን ወንጀልና መጥፎ ተግባር ይምረዋል ።

አንድ አምር ኢብኑል-ዓስ /ረ.ዐ/ የሚባል ሶሃባ ወደ ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ መጣና ቀኝ እጅን ዘርጉልኝ ቃል ኪዳንን እገባሎታለሁ አላቸው ። ቀኝ እጃቸውን ሲዘረጉ እጄን ወደኋላ አደረኩኝ (ከመጨበጥ ተቆጠብኩኝ) ። ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ (አምሩ ሆይ! ምን ሆንክ?) አሉት ። እርሱም (ከመጨበጤ በፊት) ቅድመ ግዴታ ለማድረግ ፈልጌ ነው አለ ። ነቢዩ ሙሀመድም/ሰ.ዐ.ወ/ (በምን ቅድመ ግዴታ ታደርጋለህ?) አሉት ። አምርም ማርታ እንዲደረግልኝ ነው አለ ። ነቢዩ ሙሀመድም እስልምና የበፊት ወንጀልን እንደሚሰርዝ አታውቅምን? አሉት ። (ሀዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል) ።

# ክፍል ሶስት

## ስለ እስልምና አጠቃላይ ዕውቀት

### * እስላም ምንድን ነው?

የእስልምና ሀይማኖት ሲባል በመጨረሻው ነቢይ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ላይ የወረደውን ወህይ አምኖ መቀበል ማለት ነው ።

### * መሠረታዊ እምነት በእስላም

**1- በአሏህ ማመን**

ሙስሊም በአሏህ አንድነትና ብቸኝነት ያምናል ። ያ ልጅና አጋር የሌለው የሆነ ከርሱ በስተቀር ለማንም እንዲመለክ መብት የለውም ። እርሱ እውነተኛ አምላክ ነው ። ሌሎች አምላካዊ ጠባዮች በሙሉ ስህተቶች ናቸው ። ለአሏህ /ሱ.ወ/ መልካም ስሞችና ፍጹም የተሟሉ ባህሪዎች አሉት ። ማንም በአምልኮትም ሆነ በባህሪ አይጋራውም ። ይህን አስመልክቶ አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኢኽላስ ራሱን እንዲህ በማለት ይገልጻል ፦

(قُلْ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ۝١ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ۝٢ لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ ۝٣ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدٌۢ ۝٤ )

ትርጉሙ

***1- በል፦<< እርሱ አሏህ ዘንድ ነው ። >>***
***2- <<አላህ (የፍጡራን) የበላይ ገዢና መጠጊያ ነው። >>***
***3- << አልወለደም ፤አልተወለደምም ።>>***
***4- <<አንድም ቢጤ የለውም ።>>***

ማንም እርዳታ መጠየቅ ፣መተናነስና ለርሱ መጸለይ የሚገባው ወገን የለም ። ነገር ግን ያ ሁሉ ለአሏህ ነው ።




ፍጹም ሀይል ያለው አሏህ ብቻ ነው ። ፈጣሪ፣ንጉስና በአለም ውስጥ ባለ ነገር ላይ ሁሉ ቋሚ ነው ። እርሱ ነገሮችን ሁሉ ይቆጣጠራል ። እርሱ ከፍጡራኖች ከአንዱም አይፈልግም ። ፍጡራኖች ሁሉ ለሚፈልጉት ነገር የሚመኩት በርሱ ነው ። እርሱ ሰሚ፣ተመልካችና አዋቂ ነው ። ዕውቀቱ ሁሉንም ነገሮች ያካበበ ነው ። በግልጽም ሆነ በድብቅ፣ህዝባዊም ሆነ ግላዊ፣ እርሱ የላቀው(ጌታ) የተከሰተውንም ሆነ ወደፊት የሚከሰተውን እንዲሁም እንዴት እንደሚከሰት ያውቃል ። በአለም ላይ ያለ ነገር ሁሉ ከርሱ ፈቃድ ውጭ አይከሰትም ። አሏህ የፈቀደው ይሆናል ያልፈቀደው አይሆንም ። የርሱ ፍላጎት ከፍጡራኖች ፍላጎት በሙሉ የበለጠ ነው ። እርሱ ከሁሉም ነገሮች የበለጠ ሀይል አለው ። እርሱ በሁሉም ነገር ቻይ ነው ። እጅግ በጣም ርህሩህ በጣም አዛኝና ጠቃሚ ነው ። ከነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲስ አንዱ እንደሚገልፀው አሏህ/ሱ.ወ/ ለፍጡራኖቹ እናት ለልጇ ከምታዝነው በላይ አዛኝ የሆነ ጌታ ነው ። (ሀዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል) ።

አሏህ/ሰ.ዐ.ወ/ ከብደላና ጭካኔ የራቀ ነው ። በሥራውና በትእዛዙ ጥበበኛ ነው ። አንድ ሰው አንድን ነገር ከአሏህ ከፈለገ ማንንም ከርሱ ጋር እንዲያማልደው ሳይጠይቅ በቀጥታ አሏህን መጠየቅ ይችላል ።

አሏህ እየሱስ አይደለም እየሱስ ደግሞ አሏህ አይደለም ። [39]እንዲያውም እየሱስ ራሱ ይህን አባባል ተቃውሞታል ። ይህን አስመልክቶ አሏህ/ሱ.ወ/ በሱረቱ አል-ማኢዳ በአንቀጽ 72 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(لَقَدْ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْمَسِيحُ ٱبْنُ مَرْيَمَ ۖ وَقَالَ ٱلْمَسِيحُ يَٰبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ ٱعْبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّى وَرَبَّكُمْ ۖ إِنَّهُۥ مَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِ ٱلْجَنَّةَ وَمَأْوَىٰهُ ٱلنَّارُ ۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾ )

ትርጉሙም

***72- <<አሏህ የመርየም ልጅ አልመሲህ ነው ።>> ያሉ በእርግጥም ካዱ ። አል-መሲህ ፡- <<የእስራኤል ልጆች ሆይ! ጌታዬንና ጌታችሁን (በብቸኝነት) አምልኩ ። እነሆ! በአሏህ የሚያጋራ አሏህ ገነትን እርም አድርጎበታል መኖሪያው እሳት ነው ። በዳዮችም ረዳቶች የሏቸውም ። >> ብሏል ።***

አሏህ ሥላሴ አይደለም ። ለዚህም ማስረጃ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ማኢዳ ከ73- 75 እንዲህ ይላል፡-

---

[39] የለንደኑ አሶሼትድ ፕሬስ በጁን 25- 1984(እንዲህ በማለት አስታወቀ) አብዛኛ የወንጌል ጳጳሶች ፡-<<ክርስትያኖች እየሱስን ጌታ ነው ብለው ማመናቸው የግድ አይደለም ።>> አሉ ። የጳጳሶች ቁጥራቸው እንጊሊዝ ውስጥ ከሚገኙ 39 ጳጳሶች 31 ነበሩ ። ከ31 ጳጳሶች 19 እየሱስ <<የአሏህ ከፍተኛ ወኪል >> ነው ብሎ ማመን ይበቃል ብለዋል ።

(لَّقَدۡ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ ثَالِثُ ثَلَٰثَةٖۘ وَمَا مِنۡ إِلَٰهٍ إِلَّآ
إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۚ وَإِن لَّمۡ يَنتَهُواْ عَمَّا يَقُولُونَ لَيَمَسَّنَّ ٱلَّذِينَ
كَفَرُواْ مِنۡهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٌ ٧٣ أَفَلَا يَتُوبُونَ إِلَى ٱللَّهِ
وَيَسۡتَغۡفِرُونَهُۥۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٧٤ مَّا ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ مَرۡيَمَ
إِلَّا رَسُولٞ قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهِ ٱلرُّسُلُ وَأُمُّهُۥ صِدِّيقَةٞۖ كَانَا
يَأۡكُلَانِ ٱلطَّعَامَۗ ٱنظُرۡ كَيۡفَ نُبَيِّنُ لَهُمُ ٱلۡأٓيَٰتِ ثُمَّ ٱنظُرۡ
أَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ٧٥ )

ትርጉሙ

***73- « አላህ የሦሥት አንድ ሦስተኛ ነው ።» ያሉም በእርግጥ ካዱ ። ከአንድ አምላክ ውጭ ሌላ አምላክ የለም ። ከሚሉት ነገር ባይታቀቡ ከመካከላቸው እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት ያገኛቸዋል ።»***

***74- « ወደ አላህ በንስሐ አይመለሱምና ምህረትን አይጠይቁትምን? አላህ መሓሪ አዛኝ ነው ።»***

***75- « የመርየም ልጅ አልመሲሕ ከርሱ በፊት እንዳለፉት (ሌሎች) መልዕክተኞች እርሱም መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አልነበረም ። እናቱ እውነተኛ ሴት ናት ። ሁለቱም ምግብ ይመገቡ ነበር ። አንቀጾችን እንዴት***

***እንደምናብራራላቸው አስተውል ። (ከእውነት) እንዴት እንደሚሸሹም አስተውል ።»***

አሏህ ፍጡራንን ከፈጠረ በሰባተኛው ቀን ላይ አረፈ፣ ያ እርሱ ከመልአኮች ከአንዱ ጋር ታገለ፣እርሱ በሰው ዘር ላይ የሚያሴር ምቀኛ ነው የሚባሉትን አባባሎች እስላም (አጥብቆ) ይቃወማል ። እንዲሁም ማንኛውንም የሰው ፎርም ለአሏህ ስያሜ አድርጎ መስጠት እስልምና ይቃወማል ። ይህ ሁሉ ክህደት ሆኖ ይታሰባል ። አሏህ የበላይ ነው ። የላቀው አሏህ ከጎደሎ ነገሮች ሁሉ የራቀ ነው ። የጠራው( አሏህ) አያንገላጀውም አይተኛምም ።

በአረቢኛ (አሏህ) የሚለው ቃል ፦ አምላክ(አንድና እውነተኛ ጌታ አለምን ሁሉ የፈጠረ ነው ) ። ይህ (አሏህ) የሚለው ቃል ለጌታ(አምላክ) ስሙ ነው ። የአረቢኛ ተናጋሪዎች የሚጠቀሙት ነው ። የአረብ ሙስሊሞችም ሆነ ክርስቲያኖች ። ይህ ቃል አንዱን ፈጣሪ ጌታ በስተቀር ሌላ ነገርን ለመግለጽ አይጠቀሙበትም ። ይህ ቃል በቁርአን ውጥ ከ2150 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል ። በአራማይክ(Aramaic) ይህ ከአረቢኛ ቋንቋ ጋር ግንኙነት አለው ። ነቢዩላሂ ኢሳ(ኢየሱስ) /ዐ.ሰ/ በንግግራቸው የሚጠቀሙት ቋንቋ ነበር ።[40] ጌታ የሚለው ቃል አሏህ የሚለውን ይጠቅሳል ።

## 2- በመልአኮች ማመን

ሙስሊሞች በመልአኮች ያምናሉ ። እነርሱ የተከበሩ ፍጡራንና አሏህን ብቻ የሚገዛና ከርሱ ትዕዛዝ ውጭ የማይሰሩ መሆናቸውን ያምናሉ ። ከመልአኮች አንዱ ጂብሪል(ገብሪኤል) ነው ። ያ ቁርአንን ለነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያወረደ ነው ።

[40] NIV Compact Dictionary of the Bible , Douglas p.42

## 3- ከሰማይ በወረዱ መጽሐፍቶች ማመን

ሙስሊሞች አሏህ በመጽሐፍቶች ራዕይን ወደ መልዕክተኞዎች ለሰው ልጅ እንደ ማስረጃና እንደ ስጦታ አድርጎ ልኳል ብለው ያምናሉ ። ከነዚህ መጽሐፍቶች ውስጥ ለነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያወረደው ቁርአን ነው ። አሏህ /ሱ.ወ/ ቁርአንን ከማዛባትም ሆነ ከመሰረዝ ከመደለዝ እንደሚጠብቀው ዋስተና ገብቶለታል ። አሏህ /ሱ.ወ/ በሱረቱ አል-ሂጅር በአንቀጽ 9 ላይ እንዲህ ይላል ፡-

(إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٩ )

ትርጉሙ

***9- <<መልዕክቱን ያወረድነው እኛ ነን ። (ከመበከልም) በእርግጥ እንጠብቀዋለን ።>>***

## 4- በነቢያቶችና መልዕክተኞች ማመን

ሙስሊሞች በነቢያቶችና በመልዕክተኞች ከአደም ጀምሮ ኑህን ኢብራሂምን፣ኢስማኢልን፣ኢስሐቅን፣ያዕቁብና ኢሳን ጨምሮ (አሏህ ሰላም በነርሱ ላይ ያውርድና ) በሁሉም ያምናሉ ። ነገር ግን ከነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ወደ ሰዎች የተላከው የመጨረሻው የአሏህ መልዕክት ዘላለማዊ መልዕክትን የሚያረጋግጥ ነው ። ሙስሊሞች ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ መጨረሻ የላካቸው ነቢይ መሆናቸውን ያምናሉ ። አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-አህዛብ በአንቀጽ 40 ላይ እንደሚከተለው ይገልጽልናል ።

(مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمۡ وَلَٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمًا ٤٠ )

ትርጉሙ

**40- «ሙሀመድ ከወንዶቻችሁ መካከል የአንዱም አባት አይደለም ። ግና (እርሱ) የአሏህ መልዕክተኛና የነቢያት መቋጫ ነው ። አላህ ሁሉንም ነገር ዐዋቂ ነውና ።**

ሙስሊሞች ነቢያቶች በሙሉ ፍጡራን ሰዎች እንደሆኑ ያምናሉ ። እንዲሁም ከነዚያ ነቢያቶች አንዳቸውም ከአሏህ ባህሪዎች የመለኮታዊ ባህሪነት የለባቸውም ።

## 5- በመጨረሻው ቀን ማመን

ሙስሊሞች በመጨረሻው ቀን (ሰዎች ከቀብር የሚቀሰቀሱበት ቀን) ያምናሉ ። የዚያን ቀን ሰዎች በሙሉ ይቆማሉ ። አሏህ በእምነታቸውና በሥራቸው መሰረት ይመረምራቸዋል ።

## 6- በቀድር ማመን

ሙስሊሞች በቀድር ያምናሉ ። ነገር ግን ይህ በቀድር ማመን ሲባል ለሰው ልጆች የፍላጎት ነፃነት የላቸውም ማለት አይደለም ። እንዲያውም ሙስሊሞች አሏህ ለሰው ልጅ የፍላጎት ነፃነት እንደሰጠው አረጋግጠው ያምናሉ ። ያ ማለት ትክክለኛውን ወይም ስህተቱን የመምረጥ መብት አላቸው ። ነገር ግን እነርሱ በመረጡት ነገር ሀላፊነቱን ይወስዳሉ ። በቀድር ማመን አራት ነገሮችን ያካትታል ፡-

1- አሏህ/ሱ.ወ/ ሁሉን ነገር ያውቃል ። ማለትም የተከሰተውንም ሆነ ወደፊት የሚከሰተውን ሁሉ ያውቃል ።
2- አሏህ ሁሉን ነገር የተከሰተውንም ሆነ ወደ ፊት የሚከሰተውን መዝግቧል ።
3- አሏህ ያለው ይሆናል ያላለው ነገር አይሆንም ።
4- አሏህ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው ።
(ለበለጠ መረጃ ስለ መሰረታዊ እምነት በእስላም እባኮ! ዌብ ሳይቱን ይጎብኙ፡- www.islamg-uide.com/beliefs

## * ለእስልምና ከቁርአን ውጭ ሌላ የተቀደሰ ምንጭ አለውን?

አዎ እርሱም የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሱና ነው ። (ንግግራቸው ፥ሥራቸው፥ያጸደቁት) ይህ የነቢዩ ሱና ለእስልምና ሁለተኛ ምንጭ ነው ። ሱናው ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ያሉትን ፥የሰሩትንና ያፀደቁትን ሐዲሶች ከሶሃባዎች በታማኝነት የተላለፈውን ያካትታል ። በሱና ማመን በእስላም መሠረታዊ እምነት ነው ።

### አንዳንድ የነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሐዲሶች

* የምዕመናን ምሳሌ በመዋደዳቸው፥በምህረታቸውና በርህራሄነታቸው እንደ አንድ አካል ናቸው ። (ከአካሎች) አንዱ ቢታመም ሁሉም አካሎች እንቅልፍ ሳይተኙ በማሳለፍና በትኩሳት ይካፈላሉ ።[41]

* በእምነቱ ሙሉ በሙሉ ያመኑ ምዕመናን በግብረ ገብነት የበለጡ ሰዎች ናቸው ። እንዲሁም ከናንተ መካከል በላጭ የሆኑት እነዚያ ለባለቤቶቻቸው መልካም ግብረገብነት ያላቸው ናቸው ።[42]

* ከናንተ አንዳችሁ ለራሱ የወደደውን ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ አላመነም ።[43]

* ማርታ ለሚየደርጉት አል-ራህማን ማርታ ያደርግላቸዋል ። በምድር ላሉት ምህረትን አድርጉ በሰማይ ያለው (ጌታ) ማርታ ያደርግላችኋል ።[44]

---

41 ሀዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል ።

42 ሀዲሱን አህመድና ቲርሚዚይ ዘግበውታል ።

43 ሀዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል ።
44 ሀዲሱን ትርሚዚይ ዘግበውታል ።

* ለወንድምህ ፈገግ ማለት ከበጎ አድራጎት ነው ።[45]

* መልካም ቃል (ንግግር) ከበጎ አድራጎት ነው ።[46]

* በአሏህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን ሰው ለጎረቤቱ መልካም ይስራ ።[47]

* አሏህ /ሱ.ወ/ ወደ አካላችሁም ሆነ ወደ ገጽታችሁ አይመለከትም ነገር ግን ወደ ልቦቻችሁና ሥራዎቻችሁ ይመለከታል ።[48]

* ለሰራተኛ የሰራበትን ዋጋ ክፈሉት ላቡ ሳይደርቅ በፊት ። ሀዲሱን ኢብን ማጃ ዘግበውታል ።

* (አንድ ሰው መንገድን እየተጓዘ እያለ በጣም ተጠማ ። (ይህ ሰው ) የውሃ ጉድጓድን አገኘና ወደርሱ በመውረድ ጠጣና ወጣ ። ከዚያም ውሻ ከጥማት የተነሳ አለክልኮ ጥሙን ለመቁረጥ ጭቃን እየላሰ ያየዋል ። እንዲህም አለ፡- እኔ የተጠማሁትን ያክል ይህ ውሻ ተጠምቷል (በማለት) ወደ ውሃ ጉድጓዱ ወረደና ጫማውን ውሃ ሞላውና ውሻውን አጠጣው ። አሏህም (ይህን ሰው) አመሰገነውና ወንጀሉን ማረው ) ። (ባልደረቦቻቸውም) የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ! ለእንስሳዎች ርህራሄ ማድረግ ምንዳ እናገኛለን ? ብለው ሲጠይቋቸው እርሳቸውም (ህይወት ላለው እንስሳ ሁሉ ርህራሄ ማድረግ ምንዳ አለው) ብለዋል ። (ሀዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል) ።

---

45 ሀዲሱን ትርሚዚይ ዘግበውታል ።

46 ሀዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል ።

47 ሀዲሱን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበውታል ።

48 ሀዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል ።

# ስለ ትንሳኤው ቀን እስላም ምን ይላል?

ሙስሊሞች የዚህች አለም ህይወት ለመጨረሻው አለም ህይወት (የትንሳኤ ቀን) የሙከራ ዝግጅት መሆኑን ያምናሉ ። የዚህች አለም ህይወት ለእያንዳንዱ ግለሰብ ከሞት በኋላ ላለው ህይወት ሙከራ ነው ። ይህ የመጨረሻው ቀን ይመጣና አለም በሙሉ ያበቃል ። የሞቱ ሰዎች ከቀብር ይቀሰቀሱና አላህ ፊት ለፍትህ ይቀርባሉ ። ይህ ቀን የህይወት የመጀመሪያና ዘላለማዊ ነው ። ይህ የትንሳኤ ቀን ነው ። ሰዎች በአጠቃላይ እንደ እምነታቸውና ሥራቸው ከአላህ ምንዳ ያገኛሉ ። እነዚያ **«ከአላህ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው ።»** ብለው አምነው የሞቱና ሙስሊሞች የሆኑ ምንዳቸውን ያገኛሉ ። እንዲሁም ዘላለማዊ ገነትን ይገባሉ ። ለዚህም ማስረጃ አላህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-በቀራህ በአንቀጽ 82 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٨٢ )

ትርጉሙም

***82- «እነዚያ ያመኑትና መልካምንም ሥራ የሠሩት እነርሱ የገነት ሰዎች ናቸው ዝንተ ዓለም ከውስጧ ይኖራሉ ። »***

ነገር ግን እነዚያ «ከአንድ አላህ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም ሙሀመድ የአላህ መልዕክተኛ ነው» ብለው አምነው ያልሞቱና ሙስሊሞችም ያልሆኑት እስከ ዘላለም ገነትን አያገኙም የገሀነም

እሳትም ይገባሉ ። ይህን አስመልክቶ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኢምራን በአንቀጽ 85 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ ٱلْإِسْلَٰمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٨٥﴾ )

ትርጉሙ

***85- <<ከኢስላም ውጭ ሌላን ዲን የሚሻ ሰው ከርሱ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም ። እርሱ በመጭው ዓለም ከከሳሪዎች ነው ።>>***

አሁንም አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኢምራን በአንቀጽ 91 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَمَاتُوا۟ وَهُمْ كُفَّارٌ فَلَن يُقْبَلَ مِنْ أَحَدِهِم مِّلْءُ ٱلْأَرْضِ ذَهَبًا وَلَوِ ٱفْتَدَىٰ بِهِۦٓ ۗ أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ﴿٩١﴾ )

ትርጉሙ

***91- <<እነዚያ የካዱትና ክህደት ውስጥ እንዳሉ የሞቱት ከነርሱ አንዳቸው (ራሱን ከቅጣት ለማዳን) ምድርን የሚሞላ ወርቅ ቤዛ ቢያቀርብ ተቀባይነት የለውም ። እነዚያ ለነርሱ አሳማሚ ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል ። (ከአላህ ቅጣት የሚያድናቸው አንድም) ረዳት አያገኙም ።***

ምናልባት አንድ ሰው ጥያቄ ልጠይቅ ይችላል ፡-እስልምና ጥሩ ሀይማኖት ይመስለኛል ። ነገር ግን እስልምናን ከተቀበልኩ ቤተሰቦቼና ጓደኞቼ ሌሎችም ሰዎች ያሳድዱኛል እንዲሁም በኔ ላይ ያሾፋሉ ። እስልምናን ብቀበል ወደ ገነት እገባለሁ ከእሳት ገሀነም እድናለሁን?

መልሱን በባለፈው የቁርአን አንቀጽ አሏህ /ሱ.ወ/ ያለውን እናገኛለን ፡- ***<<ከኢስላም ውጭ ሌላን ዲን የሚሻ ሰው ከርሱ ፈጽሞ ተቀባይነት የለውም ። እርሱ በመጭው ዓለም ከከሳሪዎች ነው ።>>***

አሏህ/ሱ.ወ/ ነቢዩ ሙሀመድን/ሰ.ዐ.ወ/ ወደ እስልምና እንዲጠሩ ከላከ በኋላ እርሱ ከእስልምና ውጭ ሌላን ሀይማኖት ቢከተል ተቀባይነት የለውም ። አሏህ እርሱ ፈጣሪያችንና ረዳታችን ነው ። በምድር ላይ ሁሉን ነገር ፈጥሮልናል ። እኛ ዘንድ ያሉ ፀጋዎችና መልካም ነገሮች ሁሉ ከላቀው እርሱ ዘንድ ነው ። ከዚህ ሁሉ በኋላ አንድ ሰው በአሏህና በመልዕክተኛው ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እና በእስልምና ሀይማኖት ማመንን እምቢ የሚል ሰው የትንሳኤ ቀን መቀጣቱ ፍትሃዊ ነው ። በእውነቱ የተፈጠርንበት ዋና አላማ አሏህን አንድ አድርገን እንድንገዛ ነው ። ይህን አስመልክቶ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አዝ-ዛሪያት በአንቀጽ 56 ላይ እንዲህ በማለት ይገልጻል፡-

(وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾)

ትርጉሙ

***56- <<አጋንንትንም ሰዎችንም ሊያመልኩኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም ።>>***

አሁን እኛ ዛሬ የምንኖረው ህይወት አጭር ህይወት ነው ። ከሃዲዎች የትንሳኤ ቀን በምድር ላይ የኖሩት ህይወት አንድ ቀን ወይም ግማሽ ቀን ይመስላቸዋል ። ለዚህም ማስረጃ አሏህ/ሱ.ወ/

በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ሙእሚኑን ከአንቀጽ 112-113 እንዲህ ይላል፡-

(قَٰلَ كَمۡ لَبِثۡتُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ عَدَدَ سِنِينَ ﴿١١٢﴾ قَالُواْ لَبِثۡنَا يَوۡمًا أَوۡ بَعۡضَ يَوۡمٖ فَسۡـَٔلِ ٱلۡعَآدِّينَ ﴿١١٣﴾ )

ትርጉሙም

***112- <<ምድር ላይ ምን ያህል ዓመታት ቆያችሁ ፡፡>> ሲልም ይጠይቃቸዋል ፡፡***
***113- <<የቆየነው አንድ ቀን ወይም ከቀኑ የተወሰነ ክፍል ነው ፡፡ ግና ስሌት አዋቂዎችን ጠይቅ ፡፡>> ይላሉ ፡፡***

አሁንም አሏህ/ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ሙእሚኑን ከአንቀጽ 115-116 እንዲህ ይላል፡-

(أَفَحَسِبۡتُمۡ أَنَّمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ عَبَثٗا وَأَنَّكُمۡ إِلَيۡنَا لَا تُرۡجَعُونَ ﴿١١٥﴾ فَتَعَٰلَى ٱللَّهُ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡحَقُّۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ رَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡكَرِيمِ ﴿١١٦﴾ )

ትርጉሙ

***115- <<የፈጠራችሁ ለቀልድ እንደሆነና እናንተም ወደኛ እንደማትመለሱ ገመታችሁን? >>***
***116- <<እውነተኛውን ንጉሥ አላህ (ከእንዲህ ዓይነቱ አድራጎት) ከፍ አለ ፡፡ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም ፡፡ (እርሱ) የተከበረው ዐርሽ ጌታ ነው ፡፡>> (ይላቸዋልም) ፡፡***

እውነተኛ ህይወት ማለት የወደፊት ህይወት ነው ፡፡ ያ ህይወት መንፈሳዊ ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ፊዚካላዊ ህይወትም ጭምር ነው ፡፡ እዚያ በአካላችንም ሆነ በመንፈሳችን እንኖራለን ፡፡ ነቢያችን/ሰ.ዐ.ወ/ የአዱንያ ህይወትን ከአኼራ (የመጨረሻው)

ህይወት ጋር ሲያነጻጽሩ እንዲህ ይላሉ፡- <<ወሏሂ የዚህ ዓለም (አዱንያ) ቫልዩ ከሚመጣው ዓለም (አኼራ) ሲነጻጸር አንዳችሁ ጣቱን ባህር ውስጥ ነክሮ ከዘዚያም ምን ያህል ውሃ ይዞ እንደሚወጣው አይነት ነው ። (ሀዲሱን አህመድና ሙስሊም ዘግበውታል) ።
የዚህ ዓለም ኑሮ ቫልዩ ከሚመጣው ዓለም ቫልዩ ጋር ሲነጻጸር እንደ ጠብታ ውሃ ነው ከባህር ጋር ሲነጻጸር ።

## አንድ ሰው እንዴት ሙስሊም መሆን ይችላል ?

በቀላሉ <<ላኢላሀ ኢለሏህ ሙሀመዱን ረሱሉሏህ>> ከአሏህ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም ሙሀመድ የአሏህ መልዕክተኛ ነው በማለቱ ብቻ ወደ እስልምና ይለወጣል ። ብሎም ሙስሊም ይሆናል ።

የመጀመሪያው ክፍል <<ከአሏህ በስተቀር እውነተኛ ጌታ የለም ።>> ማለትም ከአንድ አሏህ በስተቀር ለማንም እንዲመለክ መብት የለውም ። እንዲሁም ለአሏህ አጋርም ሆነ ልጅ የለውም ። አንድ ሰው ሙስሊም እንዲሆን የሚከተሉትን ነጥቦች መፈፀም አለበት ፡-

* ቁርአን አል-ከሪም ፊደል በፊደል ከአሏህ ዘንድ የወረደ ቃል ነው ።

* በትንሳኤው ቀን (የሰው ልጅ ከሞት በሚቀሰቀስበት ቀን) ማመን አለበት ። የትንሳኤው ቀን አሏህ በቁርአን ውስጥ ቃል ኪዳን እንደገባው መምጣቱ የማይቀር ነው ።

* እስልምና ሀይማኖቴ ነው ብሎ መቀበል አለበት ።

* ከአንድ አምላክ በስተቀር ምንም ነገር ወይም አንድም ነገር መገዛት የለበትም ። የአሏህ መልዕክተኛ /ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ ይላሉ ፡- <<አሏህ በባሪያው ንሰሀ በጣም ተደሰተ ። ከናንተ አንዳችሁ በንሰሀ ወደርሱ በተመለሰ ጊዜ። እርሱ በምድረበዳ ግመሉ ላይ ነበር ። ከዚያም (ግመሉ) አምልጣው ሮጠች ምግቡንና መጠጡንም ተሸክማለች ። ስለዚህ ተመልሳ ትመጣለች የሚለውን ተስፋ ሙሉ በሙሉ ቆረጠና ወደ ዛፉ በመምጣት በጥላው

ተጋደመ(ከግመሉ ተስፋ ቆረጠ) ግመሉን የመፈለጉን ተስፋ ሙሉ በሙሉ ቆርጦ እያለ በድንገት ከፊቱ ቆማ ሲያገኛት ሉጋሟን ለቀም አድርጎ ያዘና ከዚያም ከደስታ ብዛት እንዲህ አለ፡-
ጌታዬ ሆይ! አንተ ባሪያዬ ነህ እኔ ጌታህ ነኝ ። በጣም ከመደሰቱ የተነሳ ተሳሳተ ። (ሀዲሱን ሙስሊም ዘግበውታል) ።



<<ከአንድ አሏህ በስተቀር ሌላ በእውነት የሚገዙት አምላክ የለም ሙሀመድ የአሏህ መልዕክተኛ ነው ።>> የሚለው ጥቅስ በላይኛው ግንብ መግቢያ ተጽፏል ።

## ቁርአን የሚናገረው ስለ ምንድን ነው?

ቁርአን አል-ከሪም ከአሏህ የወረደ የመጨረሻ የተአምር ቃል ነው ። እሱም የሙስሊም እምነትና የአጠቃላይ ተግባሩ የመጀመሪያ ምንጭ.

ነው ። የሰው ልጅን የሚመለከቱ ርዕሶችን ሁሉ ይዳስሳል ። ጥበብ፥ የሀይማኖት ትምህርት ፥አምልኮት፥ መገበያየት፥ ህግና ሌሎችም...



ነገር ግን ዋናው የቁርአን ርዕስ በአሏህና በባሪያው መካከል ያለው ግኑኙነት ነው ። በዚያው ጊዜ የመመሪያ መስመር ያዘጋጃል ። እንዲሁም ለፍትሃዊ ማህበረሰብ አስተምህሮቱን ይተነትናል ። ብሎም ተገቢ የሰብአዊ ጠባይና ፍትሃዊ የሆነ የኢኮኖሚ ሥርአትን ያዘጋጃል ።

**ማስታወሻ፡-** በነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ላይ የወረደው ቁርአን አል-ከሪም በአረቢኛ ቋንቋ ብቻ ነው ። ታዲያ ማንኛውም የቁርአን ትርጉም በእንግሊዘኛም ሆነ በሌሎች በማንኛቸውም ቋንቋዎች የሚተረጎመው ቁርአን አይደለም ። ከቁርአን ንባቦች እንኳ አይደለም ። ነገር ግን የቁርአን የትርጉም ፍች ነው ። ቁርአን በአረቢኛ ቋንቋ ብቻ ወርዶ የተገኘ ተአምር ነው ።

## ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ማን ነው?

**ነቢዩ ሙሀመድ**/ሰ.ዐ.ወ/ በ570 እ.ኤ.አ በመካ ተወለዱ ። አባትየው እርሳቸው ከመወለዳቸው በፊት ከዚህ አለም በሞት ተለዩ ። እናትየው ደግሞ ከተወለዱ ከትንሽ ጊዜ በኋላ በሞት ተለዩ ። ከዚያም ከተከበረ የቁረይሽ ጎሳ የነበሩት አጎታቸው አሳደጓቸው ። ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ኡምይ ሆነው አደጉ ። መፃፍ ማንበብ አይችሉም ነበር ። ህይወታቸው እስኪያልፍ ድረስ በዚህ ሁኔታ ላይ ነበሩ ። ወደነቢይነት ከመላካቸው በፊት ህዝባቸው ሳይንስን አያውቁም ነበር ። ከነርሱ ውስጥ ብዞቻቸው የማይጽፉ የማያነቡ ነበሩ ። ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ትልቅ ሲሆኑ በእውነተኝነታቸውና በታማኝነታቸው የሚተማመኑባቸው መሆኑ ፣ በለጋሥነታቸውና በልባዊነታቸው ይታወቁ ነበር ። የታማኝነታቸው ልክ አልፎ እስከ «አል-አሚን »(ታማኙ) የሚል ሥያሜ እንዲዙ አድርጓቸዋል ።

መልዕክተኛው ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በጣም ሀይማኖታዊ ነበሩ ፡፡ የህብረተሰባቸውን ኋላቀርነትና ጣኦት አምልኮትን አጥብቀው ይጸየፉ ነበር ፡፡ አርባ አመት ሲሞላቸው ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ የመጀመሪያ ራዕይን በጅብሪል አማካኝነት ተቀበሉ ፡፡ ይህ ራዕይ ቁርአን አል-ከሪም እስኪሟላ ድረስ ሀያ ሶስት አመት ፈጀ ፡፡ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ቁርአን ማንበብና ወደ እስልምና (ወደ እውነተኛው መንገድ) ጥሪ ማድረግ ሲጀምሩ እርሳቸውና የርሳቸው ጥቅት ጓደኞች ካላመኑት በኩል (ሙሽሪኮች) ለሥቃይና ስደት ተዳረጉ ፡፡ ጭቆናው በሀይል እየበዛ ሄደ ፡፡ አሏህ /ሱ.ወ/ በ622 እ.ኤ.አ (ስደት) እስከሚያዛቸው ድረስ ፡፡ ይህ ከመካ ወደ መዲና ከተማ ነበር ፡፡ ያም (በ260 ማይል በስተሰሜን) ይገኛል ፡፡ የተደረገው ስደት የሙስሊም ካላንደር ምልክት መጀመሪያ ነበር ፡፡ ከብዙ አመታት በኋላ መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ እና ተከታዮቻቸው ወደ መካ ለመመለስ ቻሉ ፡፡ እነርሱም ለጣላቶቻቸው ይቅርታ አደረጉ ፡፡ ከዚህ አለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በስድሳ ሶስት አመታቸው አብዛኛው የአረብ ደሴት ሰዎች እስልምናን ተቀበሉ ፡፡ ህይወታቸው ካለፈ በአንድ ክፍለ ዘመን ውስጥ እስልምና በስተ ምዕራብ እስከ እስፔን በስተ ምስራቅ እስከ ቻይና ተስፋፋ ፡፡ ይህ ፈጣንና ሰላማዊ የሆነ የእስልምና መስፋፋት ምክንያት የሆነው በእውነታዊና በግልጻዊ የሀይማኖት ትምህርት ልዩነት ባህሪ ነበር ፡፡ እስልምና የሚጣራው በአንድ ጌታ የማመን እንጂ ሌላ አይደለም ፡፡ እርሱ ብቻ ነው መገዛት የሚገባው ፡፡

መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ ለታማኝነት ፣ ለፍትህ፣ ለምህረት ፣ ለርህራሄ ፣ለእውነትነትና ለጀግንነት መልካም አርአያ ተምሳሌት ነበሩ ፡፡ ምንም እንኳ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ የሰው ልጅ ቢሆኑም ከተንኮል ባህሪዎች በሙሉ የራቁ ነበር ፡፡ ትግላቸው በአንዱ አሏህ መንገድ ብቻና የአኼራን (የሚመጣው አለምን) ምንዳ በመፈለግ ነበር ፡፡ ከዚህም በላይ በሁሉም ተግባራቸውና አድራጎታቸው አሏህን ይፈሩ ነበር ፡፡

ስለ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ተጨማሪ ዕውቀት እባኮ! ዌብ ሳይቱን ይጎብኙ ፡ www.islam-guide.com/muhammad



የነቢዩ ሙሀመድ መስጂድ

## የእስልምና መስፋፋት የሳይንስ ሥልጣኔን እንዴት አገዘ?

እስልምና የሰው ልጆች የአእምሮ ሀይላቸውንና አስተውሏቸውን እንዲጠቀሙ ያዛል ።




እስልምና ከተስፋፋ በጥቅት አመታት ውስጥ ከፍተኛ ሥልጣኔና ዩኒቨርሲቲዎች ተስፋፉ ።
የምስራቃዊና የምዕራባዊ አስተሳሰብ ተያያዥነት ያለው ስርአት ሆኗል ። አዲሱ አስተሳሰብ ከቀድሞ አስተሳሰብ ከፍተኛ ሥልጣኔን አምጥቷል ። ለምሳሌ በህክምና በማቲማቲክስ ፥በፊዚክስ፥ በአስትሮኖሚ፥ በጂኦግራፊ ፥ በህንፃ ጥበብበሥነ ጽሁፍና በታሪክ ናቸው ። ከዚያም በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከእስላሙ አለም ወደ ኢሮፕ ብዙ መሰረታዊ ሥርአቶች ተሸጋገሩ ። እንደ አል- ጀብራ ፥ የአረቢኛ ቁጥሮችና የዜሮ ሀሳብ (ለማቲማቲክስ መሻሻል

ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው) ። ሙስሊሞች ዘመናዊ መሳሪያዎችን በማሻሻል ኢሮፕያዊያኖች ለምርምር እንዲጠቀሙ አስችሏቸዋል ።
ለምሳሌ ያክል ፦ የከፍታ መለኪያ መሳሪያ (Astrolabe)፣ አቅጣጫን መለያ (መጠቆሚያ) ካርታና ሌሎችም ነገሮች የበለጸጉት በሙስሊሞች ነው ።



(Astrolabe) አንዱ በጣም አስፈላጊ
የሳይንስ መሳሪያ ነው ። ይህም በሙስሊሞች
የተፈለሰፈና በምዕራቡ አለም እስካሁን
በሰፊው ይጠቀሙበታል ።



ከዚህ በታች በሥዕሉ ላይ እንደምንመለከተው የሙስሊም ሀኪሞች (physicians) ብዙ የቀዶ ጥገና መሣሪያዎችን በማስፋፋት ለቀዶ ጥገና ትልቅ ትኩረት ሰጥተዋል ፡፡ የቀድሞ የብራና መጽሀፍ እንደሚያሳየው ፡፡

## ሙስሊሞች በኢሳ/ዐ.ሰ/ እንዴት ያምናሉ?

ሙስሊሞች ኢየሱስ ክርስቶስን በጣም ያከብሯቸዋል ፡፡ ወደ ሰው ልጅ ከተላኩ ታላላቅ ነቢያቶች አንዱ እንደሆኑ ያምናሉ ፡፡ ትውልዳቸውም ከድንግሏ መርየም (ማሪያም) መሆኑንና በቁርአን ውስጥ ስሟ መርየም የሚል ሱራ ይገኛል ፡፡ ቁርአን የኢሳን ትውልድ በሱረቱ አል-ኢምራን ከአንቀጽ 45-47 እንደሚከተለው ይገልጻል ፡-

(إِذْ قَالَتِ ٱلْمَلَـٰٓئِكَةُ يَـٰمَرْيَمُ إِنَّ ٱللَّهَ يُبَشِّرُكِ بِكَلِمَةٍ مِّنْهُ ٱسْمُهُ ٱلْمَسِيحُ عِيسَى ٱبْنُ مَرْيَمَ وَجِيهًا فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْـَٔاخِرَةِ وَمِنَ ٱلْمُقَرَّبِينَ ﴿٤٥﴾ وَيُكَلِّمُ ٱلنَّاسَ فِى ٱلْمَهْدِ وَكَهْلًا وَمِنَ ٱلصَّـٰلِحِينَ ﴿٤٦﴾ قَالَتْ رَبِّ أَنَّىٰ يَكُونُ لِى وَلَدٌ وَلَمْ يَمْسَسْنِى بَشَرٌ ۖ قَالَ كَذَٰلِكِ ٱللَّهُ يَخْلُقُ مَا يَشَآءُ ۚ إِذَا قَضَىٰٓ أَمْرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٤٧﴾ )

ትርጉሙም

***45- መላእክት እንዲህ ባሉ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ) ፡- «መርየም ሆይ! አላህ ከርሱ በሆነ በቃል (ያለ አባት በሚወለድን) ልጅ ያበስርሻል ፡፡ (ልጅሽ) የመርየም ልጅ አልመሲህ ዒሳ በሚል ስያሜ ይጠራል ፡፡ በዚህችም በቀጣዩ አለም የተከበረ ፣ (ከአለህ) የቅርብ ባለሟሎች አንዱም ይሆናል ፡፡»***

***46- «ገና ከአንቀልባ ውስጥ እያለና ካደገም በኋላ ሰዎችን (ወደ ተውሂድ) ይጠራል ፡፡ ከደጋግ የአሏህ አገልጋዮችም ይሆናል ፡፡»***

***47- (መርየም) ፡- «ጌታዬ ሆይ! አንድም ሰው ሳይነካኝ (ከአንድም ወንድ ጋር ሳልገናኝ) እንዴት ልጅ ሊኖረኝ ይችላል ?» አለች ፡፡ «ነገሩ እንዲህ ነው አለህ (የሚሳነው የለም)፣ የሚሻውን ይፈጥራል ፡፡ አንድ ነገር በወሰነ ጊዜ ሁን ይለዋል፣(ወዲያውም)ተፈጻሚ ይሆናል ፡፡» አላት ፡፡***

የነቢዩላሂ ኢሳ (አለይሂ አስ-ሰላም) አወላለድ እንዲህ ነበር ፡፡ ከአሏህ የሆነ ተአምራዊ ትእዛዝ አሏህ አደምን ያለ አባት እንደፈጠረ ሁሉ ኢሳንም ፈጥሯል ፡፡ ይህን አስመልክቶ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኢምራን በአንቀጽ 59 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(إِنَّ مَثَلَ عِيسَىٰ عِندَ ٱللَّهِ كَمَثَلِ ءَادَمَ ۖ خَلَقَهُۥ مِن تُرَابٍ ثُمَّ قَالَ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٥٩﴾)

ትርጉሙ

***59- <<ከአላህ ዘንድ ዒሳ እንደ አደም አምሳያ ነው ፡፡ (አላህ አደምን) ከአፈር ፈጠረው ፡፡ <<ሁን>> አለው፤ሆነ ፡፡>>***

ነቢዩላሂ ዒሳ/ዐ.ሰ/ በነቢይነት ጊዚያቸው ብዙ ተአምራቶችን አሳይተዋል ፡፡ ለዚሁ ማስረጃ የተባረከው አሏህ በቁርአን ውስጥ ነቢዩላሂ ኢሳ ያሉትን በማመላከት በሱረቱ አል-ኢምራን በአንቀጽ 49 እንዲህ ይላል ፡-

(وَرَسُولاً إِلَىٰ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ أَنِّي قَدۡ جِئۡتُكُم بِـَٔايَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ ۖ أَنِّيٓ أَخۡلُقُ لَكُم مِّنَ ٱلطِّينِ كَهَيۡـَٔةِ ٱلطَّيۡرِ فَأَنفُخُ فِيهِ فَيَكُونُ طَيۡرَۢا بِإِذۡنِ ٱللَّهِ ۖ وَأُبۡرِئُ ٱلۡأَكۡمَهَ وَٱلۡأَبۡرَصَ وَأُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰ بِإِذۡنِ ٱللَّهِ ۖ وَأُنَبِّئُكُم بِمَا تَأۡكُلُونَ وَمَا تَدَّخِرُونَ فِي بُيُوتِكُمۡ ۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لَّكُمۡ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ﴿٤٩﴾)

ትርጉሙ

***49- ለእስራኤል ልጆች መልዕክተኛ ያደርገዋልም ፡፡ (እንዲህ የሚል መልዕክትም ያደርስላቸዋል) ፡- <<ከጌታችሁ ዘንድ የተሰጠኝን ተአምር ይዤ ወደናንተ መጣሁ ፡፡ ከጭቃ የወፍ አይነት ቅርጽ ያለውን ነገር እፈጥራለሁ ፡፡ ከውስጡም እነፋበታለሁ ፡፡ በአላህ ፈቃድ ወፍ ይሆናል ፡፡ እውር ሆኖ የተወለደንም ፤ለምጻምንም (በአላህ ፈቃድ) እፈውሳለሁ ፤ የሞተንም -በአላህ ፈቃድ- ሕያው አደርጋለሁ ፡፡ የምትመገቡትንም ፤ከቤታችሁ***

***ውስጥ የምታከማቹሁትንም እነግራችኋለሁ ፡፡ የምታምኑ ከሆናችሁ ይህ ለናንተ በውስጡ በቂ ተአምርን ይዟል ፡፡>>***

ሙስሊሞች ነቢዩላሂ ኢሳ /ዐ.ሰ/ እንዳልተሰቀሉ ያምናሉ ፡፡ እነዚያ የኢሳ /ዐ.ሰ/ ጠላቶች እርሳቸውን ለመስቀል ያቀዱት ነበር ፡፡ ነገር ግን አሏህ አድናቸው ሲያበቃ ወደርሱ አሳረጋቸው ፡፡ እናም ሌላን ሰው በኢሳ ቦታ በማስቀመጥ አመሳሰለባቸው ፡፡ የኢሳ ጠላቶች ይህን ሰው እርሱ ኢሳ ነው በማለት ወስደው ሰቀሉት ፡፡ ይህን አስመልክቶ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኒሳእ በአንቀጽ 157 ላይ እንዲህ ይላል፡-

(وَقَوۡلِهِمۡ إِنَّا قَتَلۡنَا ٱلۡمَسِيحَ عِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ رَسُولَ ٱللَّهِ وَمَا قَتَلُوهُ وَمَا صَلَبُوهُ وَلَٰكِن شُبِّهَ لَهُمۡۚ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ لَفِي شَكّٖ مِّنۡهُۚ مَا لَهُم بِهِۦ مِنۡ عِلۡمٍ إِلَّا ٱتِّبَاعَ ٱلظَّنِّۚ وَمَا قَتَلُوهُ يَقِينَۢا ﴿١٥٧﴾)

ትርጉሙ

***157- <<እኛ የአላህ መልዕክተኛ የሆነውን የመርየምን ልጅ አል መሲሕ ዒሳን ገደልን ፡፡ በማለታቸውም ሰበብ (ተረገሙ) ፡፡ አልገደሉትም ፡፡ አልሰቀሉትምም ፡፡ ግና ተመሳሰለባቸው ፡፡ እነዚያ በዚህ ጉዳይ ላይ የተወዛገቡት ጥርጣሬ ውስጥ ናቸው ፡፡ በዚህ ላይ ቅንጣት እውቀት የላቸውም ፡፡ ጥርጣሬን ከመከተል በቀር ፡፡ በእርግጥም አልገደሉትም ፡፡>>***

መልዕክተኛውም ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሆነ ኢሳ /ዐ.ሰ/ በአሏህ አንድነት እምነት መሠረታዊ ለውጥን ለማምጣት አልመጡም ፡፡

እነዚያ የመጀመሪያዎቹ ነቢያቶች የመጡበት መንገድ ይህን እምነት የበላይ ለማድረግና እንደ አዲስ ለማስፋፋት ነው ፡፡[49]



ቅዱስ የሚገኘው አል-መስጂድ አል አቅሳ

ስለ ኢሳ /ዐ.ሰ/ ለበለጠ መረጃ እባኮ! ዌብ ሳይታችንን ይጎብኙ፡-

www.islam-guide.com/jesus

[49] ሙስሊሞች አሏህ/ሱ.ወ/ በነቢዩላሂ ኢሳ /ዐ.ሰ/ ላይ ወንጌልን እንዳወረደና ያ የዚህ ወንጌል ከፊል ፓርቶቹ እስካሁንም እንዳለ ያምናሉ ፡፡ ነገር ግን ያ ማለት ሙስሊሞች አሁን ባለው ወንጌል ያምናሉ ማለት አይደለም ፡፡ ምክንያቱም ያ አላህ በነቢዩ ኢሳ /ዐ.ሰ/ ላይ እንዳወረደው ኦሪጂናል መጽሀፍ ቅዱስ አልሆነም ብዙ ክፍሎቹ ተቀይሯል ፤ ተጨምሯል እንዲሁም ተገድፏል ፡፡ ይህን የተናገሩት መጽሀፍ ቅዱስን ክለሳ ለማድረግ የተዋቀሩ ኮሚቴዎች ነበሩ ፡፡ እነዚህ ኮሚቴዎች 32 ጥናት አድራጊዎችና 50 ከሚሆኑ የተለያዩ የሀይማኖት ተወካዮች መካሪነት የተዋቀረ ነበር ፡፡ በመጽሀፍ ቅዱስ መግቢያ ላይ ኮሚቴዎቹ ክለሳ ሲያደርጉ እንዲህ በማለት ገልፀዋል ፡- ‹‹ወንጌል ለብዙ ለውጦች ተዳርጓል ፡፡ እንዲሁም ትክክለኛ እትሙ አይገኝም ፡፡ ስለዚህ ለኦሪጂናሉ መጽሀፍ ቅዱስ ቅርብ የሆነውን ጥናት መከተል ይገባናል ፡፡ እባኮ ዌብ ሳይቱን ይጎብኙ

## የእስልምና ሀይማኖት ስለ አሸባሪነት ምን ይላል ?

**እስልምና የምህረት ሀይማኖት ነው ። አሸባሪነትን አይፈቅድም ። ይህን አስመልክቶ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ሙምተሂና በአንቀጽ 8 ላይ እንዲህ ይላል፡-**

(لَّا يَنْهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ لَمْ يُقَـٰتِلُوكُمْ فِى ٱلدِّينِ وَلَمْ يُخْرِجُوكُم مِّن دِيَـٰرِكُمْ أَن تَبَرُّوهُمْ وَتُقْسِطُوٓا۟ إِلَيْهِمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُقْسِطِينَ ﴿٨﴾)

ትርጉሙም

***8- <<ለነዚያ በእምነታቸው ሰበብ ላልተዋጓችሁና ከቤቶቻችሁም ላላስወጧችሁ (ከሐዲያን) መልካም ልትውሉላቸው ፍትሃዊ ልትሆኑላቸውም አላህ አይከለክላችሁም ። አላህ ፍትሃዊያንን ይወዳልና ። >>***

***ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ ሴቶችና ህፃናትን ወታደሮች እንዳይገድሏቸው ይከለክሉ ነበር ።[50] ከዚህም በላይ እንዳይከዱ፣ ከልክ በላይ እንዳይገድሉና አዲስ የተወለደ ህፃን ልጅ እንዳይገድሉ ይመክሯቸው ነበር ።[51] በተጨማሪም ማንም ከሙስሊሞች ጋር ከተስማማ*** በኋላ አንድን ሰው የገደለ የጀነትን ሽታ አያሸትም (የጀነቷ) ሽታ አርባ አመት የሚያስኬድ ርቀት የሚገኝ ሆኖ እያለ ።[52]

ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ በእሳት መቅጣትን ይከለክሉ ነበር ።[53]

---

[50] *ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 1744 እና ሶሂህል ቡኻሪይ 3015 ላይ ዘግበውታል ።*

[51] *ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 1731 እና ቲርሚዚይ 1408 ላይ ዘግበውታል ።*

[52] ሀዲሱን ሶሂሂል ቡኻሪይ 3166 እና ኢብን ማጃ 2686 ላይ ዘግበውታል ።

[53] ሀዲሱን 67አቡዳውድ 2675 ላይ ዘግበውታል ።

የግድያ ወንጀል እንደ ሁለተኛ ትላልቅ ወንጀሎች ተደርጎ ተቀምጧል ፡፡[54] እንዲያውም ስለ ትንሳኤው ቅጣት እንዲህ በማት ያስጠንቅቁ ነበር ፡-(የትንሳኤው ቀን በሰዎች መካከል የሚፈረደው የመጀመሪያው ፍርድ እነዚያ ደምን የሚያፈሱ ሰዎች ናቸው /ያ ማለት መግደልና መደብደብ ማለት ነው / ) ፡፡[55] ከዚህም በላይ ሙስሊሞች ለእንስሳዎች ምህረት እንዲያደርጉ ገፋፍቷቸዋል ፡፡ እንዲሁም መጉዳትን ከልክሏል ፡፡ አንድ ጊዜ ነቢዩ ሙሀመድ እንዲህ አሉ፡- {አንዲት ሴት ድመቷን እስክትሞት ድረስ በማሰሯ ምክንያት ተቀጣች ፡፡ እሳትንም ገባች ፡፡ አላበላቻትም ፤ አላጠጣቻትም (ሌላው ቀርቶ) በምድር ላይ ያሉትን ተባዮች እንዳትበላ አሰረቻት} ፡፡[56] በተጨማሪም ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ ይላሉ ፡- {አንድ ሰው መንገድ ላይ እየተጓዘ እያለ በጣም ተጠማ ፡፡ (ይህ ሰው) የውሃ ጉድጓድን አገኘና ወደርሱ በመውረድ ጠጣና ወጣ ፡፡ ከዚያም ውሻ ከጥማት የተነሳ አለክልኮ ጥሙን ለመቁረጥ ጭቃን እየላሰ ያየዋል ፡፡ እንዲህም አለ፡- እኔ የተጠማሁትን ያክል ይህ ውሻ ተጠምቷል በማለት ወደ ውሃ ጉድጓዱ ወረደና ጫማውን ውሃ ሞላውና ውሻውን አጠጣው ፡፡ አሏህም አመሰገነውና ወንጀሉን ማረው} ፡፡ (ባልደረቦቻቸውም) የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ ! ለእንስሳዎች ርህራሄ በማድረጋችን ምንዳ እናገኛለን? ብለው ሲጠይቋቸው እርሳቸውም {ህይወት ላለው እንስሳ ሁሉ ርህራሄ ማድረግ ምንዳ አለው} ብለዋል ፡፡ [57]በሌላም በኩል ነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ አሉ፡- እንስሳ ለምግብነት ማረድ ሲያስፈልግ ሙስሊሞች ለሚታረደው እንስሳ ፍራቻና ህመም በጣም ሳይሰማው እንዲያርዱ አዘዋል ፡፡

---

[54] ሀዲሱን ሶሂሂል ሙስሊም 88 እና ሶሂሂል ቡኻሪይ 6871 ላይ ዘግበውታል ፡፡
[55] ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 1678 እና ሶሂሂል ቡኻሪይ 6533 ላይ ዘግበውታል ፡፡
[56] ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 2422 እና ሶሂሂል ቡኻሪይ 2365 ላይ ዘግበውታል ፡፡

[57] ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 2244 እና ሶሂሂል ቡኻሪይ 2466 ላይ ዘግበውታል ፡፡

አሏህ /ሱ.ወ/ በሁሉም ነገር ላይ መልካም ነገርን ደንግጓል ፡፡
እንስሳን ስታርዱ አሳምራችሁ እረዱ ከናንተ አንዳችሁ ቢለዋውን ይሳለውና የእንስሳውን ስቃይ ይቀንስ ፡፡[58]
ከነዚህና ከሌሎችም እስላማዊ ጥቅሶች በመነሳት በሰላማዊ ሰዎች ልብ ተጽኖ የሚያሳድረውን ተግባር መፈፀም፣ግንባታንና ንብረትን ለማፍረስ ምክንያት መሆን ፣ቦንብን በመወርወር ንፁሓንን ወንዶችን፣ሴቶችንና ህፃናትን አካለ ስንኩላን ማድረግ ፣ እነዚህ ሁሉ ክልክል የሆኑ ተግባሮች ናቸው ፡፡ በእስላምና በሙስሊሞችም የተጠላ ነው ፡፡ እስልምና የሰላም፣የምህረትና የእዝነት ሀይማኖት ነው ፡፡ አብዛኛ ሙስሊሞች በሙስሊም ስም ለሚደረጉ ክስተቶችና ፍንዳታዎች በምንም ነገር ግኑኙነት የላቸውም ፡፡ ከሙስሊሞች አንድ ግለሰብ አሸባሪ ተግባርን ቢፈጽም ይህ ሰው በእስላም ህግ (ሸሪአ) ይወገዛል ፡፡

## ሰብኣዊ መብትና ፍትህ በእስላም

እስልምና ብዙ ሰብአዊ መብቶችን ለእያንዳንዱ ግለሰብ ይሰጣል ፡፡ ከዚህ በታች አንዳንድ እስላም የሚከለክላቸው ሰብአዊ መብቶች ናቸው ፡-
የሰው ልጅ ህይወትና ንብረት በእስላም ቅዱሳዊ ሆኖ ይገለፃል ፡፡ ግለሰቡ ሙስሊም ቢሆንም ባይሆንም ፡፡ በተጨማሪም እስላም የሰው ክብርን ይጠብቃል ፡፡ ስለዚህም እስላም ሌላን መስደብ ወይም በሱ ማሾፍ ይከለክላል ፡፡ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ ይላሉ ፡- (ደማችሁ ገንዘባችሁ (ንብረታችሁ) ና ክብራችሁ በናንተ ላይ ክልክል ነው) ፡፡[59]
ዘረኝነት በእስላም አይፈቀድም ፡፡ ቁርአን የሰው ልጅን እኩልነት በዚህ ጠንካራ ንግግር በሱረቱ አል-ሁጁራት በአንቀጽ 13 ላይ እንዲህ በማለት ያረጋግጣል ፡-

---

[58] ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 1955 እና አት-ቲርሚዝይ 1409 ላይ ዘግበውታል ፡፡
[59] ሀዲሱን ሶሂህ አል-ቡኻሪይ 1739 ዘግበውታል ፡፡



شبكة الألوكة - قسم الكتب

(يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ١٣)

ትርጉሙ

***13- <<እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እኛ ከሴትና ከወንድ ፈጠርናችሁ ፡፡ ትተዋወቁ ዘንድም ጎሣዎችና ነገዶችም አደረግናችሁ ፡፡ ከመካከላችሁ ከአላህ ዘንድ በላጩ አላህን የበለጠ የሚፈራ ነው ፡፡ አላህ (ሁሉንም ነገር) ዐዋቂ ፤ (የውስጥ ሚስጥራትን ሳይቀር) ጠንቅቆ የሚያውቅ (አምላክ ) ነው ፡፡***

እስልምና አንዳንድ ሰዎችን ወይም ቡድኖችን በሀብታቸው ወይም በሥልጣናቸው ወይም በዘራቸው ምክንያት ልዩነት ያደርጋል የሚለውን አባባል አይቀበለውም ፡፡ አሏህ/ሱ.ወ/ የሰው ልጆችን የፈጠረው በእኩልነት ነው ፡፡ በግለሰቦች መካከል ያለው ልዩነት የሚሆነው በእምነትና አሏህን በመፍራት ብቻ ነው ፡፡ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ <<እናንተ ሰዎች ሆይ! ጌታችሁ አንድ ነው ፡፡ አባታችሁ (አደም) አንድ ነው ፡፡ አረቦች አረብ ካልሆኑት አይበልጡም ፡፡ አረብ ያልሆኑትም ከአረቦች አይበልጡም ፡፡ ቀዮችም ጥቁሮችን አይበልጡም ፡፡ ጥቁሮችም ቀዮችን አይበልጡም አሏህን በመፍራት ቢሆን እንጂ) ፡፡[60]

[60] ሀዲሱ በሙስነድ አህመድ 22978 ተዘግቧል ፡፡



ዛሬ የሰው ልጅ የሚጋፈጠው አንዱ ዋና ችግር ዘረኝነት ነው ፡፡ የሰለጠነው አለም ሰውን ወደ መንኮራኮር (ጨረቃ) መላክ ይችላል ነገር ግን አንድ ሰው ወንድሙን እንዳይጠላ ወይም እንዳይገድል ማድረግ አይችልም ፡፡ ከነቢዩ ሙሀመድ ዘመን ጀምሮ እስልምና ዘረኝነትን ለማጥፋት እውን ምሳሌ ሆኗል ፡፡ ወደ ሳውዲ አረቢያ (መካ) የሚደረገው አመታዊ የሀጅ ጉዞ እውነታዊ የሙስሊም ወንድማማችነትን በሁሉም ዘሮችና ህዝቦች መካከል ይተገብራል ፡፡ ያም ከ2 ሚሊዮን በላይ ሙስሊሞች በአለም አጠቃላይ ሀጅን ለማድረግ ይመጣሉ ፡፡ እስልምና የፍትህ ሀይማኖት ነው ፡፡ ለዚህም ማስረጃ አኋህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኒሳእ በአንቀጽ 58 ላይ እንዲህ ይላል፡-

۞ إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُكُمۡ أَن تُؤَدُّواْ ٱلۡأَمَٰنَٰتِ إِلَىٰٓ أَهۡلِهَا وَإِذَا حَكَمۡتُم بَيۡنَ ٱلنَّاسِ أَن تَحۡكُمُواْ بِٱلۡعَدۡلِ

ትርጉሙ

***58- <<አላህ አደራን ለባለቤቱ እንድታደርሱ በሰዎች መካከል ፍርድ በምትሰጡበት ወቅት በፍትህ እንድትፈርዱ ያዛችኋል ።>>***

(وَأَقْسِطُوٓاْ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُقْسِطِينَ )

ትርጉሙ

***9- <<አላህ ፍትሃዊያንን ይወዳልና ።***

**ከዚህም በላይ ሙስሊም ከሚጠላቸው ሰዎች እንኳ ቢሆን የግድ ፍትሃዊ መሆን አለበት ። ለዚህም ማስረጃ አሏህ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ማኢዳ በአንቀጽ 8 ላይ እንዲህ ይላል፡-**

(وَلَا يَجْرِمَنَّكُمْ شَنَـَٔانُ قَوْمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعْدِلُواْ ۚ ٱعْدِلُواْ هُوَ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ )

ትርጉሙ

***8- <<ለሰዎች ያላችሁ ጥላቻ ፍትሃዊ ከመሆን አያግዳችሁ ። ፍትሃዊ ሁኑ ። እርሱ አላህን ለመፍራት (ባህሪ) ቀረብ ያለ ነው ።***

**ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ሌላ ወገንን ማሳደድ፣ መበደልና እንዲሁም መጥፎ አኗኗርን መኖር አስጠንቅቋል ። እንዲህም ይላሉ፡-**

**(መበደልን ፍሩ ። መበደል የትንሳኤው ቀን ብዙ ጨለማዎች ሆነው ይቀርባሉ) ።[61] እነዚያ በዚች አለም መብታቸውን (የሚገባቸውን መብት) ያላገኙ የትንሳኤ ቀን ይወስዳሉ ። ነቢዩ ሙሀመድ**

---

[61] ሀዲሱ በሙስነድ አህመድ 5798እና በሶሂሂል ቡኻሪይ2447 ተዘግቧል ።

/ሰ.ዐ.ወ/ እንዲህ ይላሉ፤ የፍርዱ ቀን እነዚያ የተበደሉት ሰዎች ይካሳሉ ። (መብታቸው ይሰጣቸዋል ) ።[62]

## ሴት ልጅ በእስላም ያላት ቦታ ምንድን ነው ?

እስላም ሴትን ልጅ ያገባችም ብትሆን ያላገባች እንደ ሰው ልጅ ሙሉ መብት ያላት መሆኑን ያሰምርበታል ። ባለ ንብረት የመሆንና ንብረቷን ያለ ምንም ቁጥጥር እንደፈለገች የማድረግ መብት አላት ። የመግዛትና የመሸጥ መብት አላት ። ለመልካም ነገር ስጦታ መስጠት ፤ገንዘቧን እንደፈለገች ማውጣት ትችላለች ። የሙሽራው ጥሎሽ ለሙሽርነት የሚሰጠው እንደፈለገች እንድታደርግ ነው ። እንዲሁም ስላገባች በባሏ ስም አትጠራም በቤተሰቦቿ ስም ነው የምትጠራው ። እስልምና ወንድ ከባለቤቱ ጋር ጥሩ አኗኗር እንዲኖር ያዛል ። ይህን አስመልክቶ መልዕክተኛው /ሰ.ዐ.ወ/ (ከምእመናን የተሟላ እምነት ያለው ሥነ ምግባሩ ጥሩ የሆነ ነው ። ከናንተ የተሻሉት ለሚስቶቻቸው መልካም የሚሆኑ ናቸው ።[63]እናቶች በእስልምና በጣም ክብር አለቸው ። እስልምና እናቶችን መልካም እንዲዋልላቸው ያዛል ። አንድ ሰውዬ ወደ አሏህ መልዕክተኛ /ሰ.ዐ.ወ/ መጣና እንዲህ አላቸው ፡- የአሏህ መልዕክተኛ ሆይ! ማንን ነው መልካም ተጓዳኝ አድርጌ መያዝ የሚገባኝ ? አለ ። እርሳቸውም እናትህን አሉት ። ከዚያስ ማንን? አለ ።እናትህን አሉት ። ከዚያስ ማንን ? አላቸው ። እርሳቸውም አባትህን አሉት ።[64]

ስለ ሴት ልጅ ያላት ቦታ በእስላም ለማወቅ እባኮ ! ዌብሳይቱን ይጎብኙ ።

---

[62] ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 2582 እና ሙስነድ አህመድ 7163 ላይ ዘግበውታል ።

[63] ሀዲሱን አህመድና ቲርሚዝይ ዘግበውታል ።

[64] ሀዲሱን ሶሂህ ሙስሊም 2548 እና ሶሂህ ቡኻሪይ 5971 ላይ ዘግበውታል ።



## ቤተሰብ በእስላም

ቤተሰብ በሰው ልጅ ሥልጣኔ መሠረታዊ አንድነት አለው ። ቤተሰብ ዛሬ መበታተንና ያለ መስማማት እየታየበት ይገኛል ። ቤተሰባዊ የእስላም ሥርአት የባልን፥ የሚስትን ፥ የህጻናትና የዝምድናን መብት በሚዛናዊ ሁኔታ ይጠብቃል ። በደንብ የተደራጀ ቤተሰባዊ ሥርአት በመመሥረት ራስን ያለ መውደድ ፀባይ ፥ልግስናና ፍቅርን ይመግባል ። የተደላደለ የቤተሰብ አንድነት ለመመስረት ሰላምና ደህንነት ማግኘት በጣም አስፈላጊ ነው ። ይህንን እስላም በያንዳንዱ ቤተሰብ መካከል ለመንፈሳዊ እድገት አስፈላጊ ሆኖ ያየዋል ።

## ሙስሊሞች የዕድሜ ባለ ፀጋዎችን እንዴት ይንከባከባሉ?

በሙስሊሙ አለም የዕድሜ ባለ ፀጋዎችን ቤት ማግኘት በጣም ጥቅት ነው ። በዚህ አስቸጋሪ የህይወት ጊዜ ደካማ ወላጆችን መሸከም ክብርና በረከት እንዲሁም ለትልቅ መንፈሳዊ እድገት ምቹ ሆኖ ይታሰባል ። በእስልምና ለወላጆቻችን ፀሎት ማድረግ ብቻ በቂ አይደለም ። ነገር ግን ከልክ በላይ በእዝነት ከነርሱ ጋር አብረን በመኗኗርና ህፃን ሆነን እያለ ከራሳቸው በላይ እኛን ያበልጡ እንደነበር ማስታወስ ይገባናል ። ስለዚህም ነው የእናቶች ክብር ከፍ ብሎ የምናገኘው ። የሙስሊም ወላጆች ለዕድሜ ባለ ፀጋነት



شبكة الألوكة - قسم الكتب

ሲደርሱ በምህረትና በርህራሄነት ይያዛሉ ፡፡ በእስላም ከአሏህ በኋላ ወላጆችን ማገልገል ወይም መልካም መሆን የግድ ነው ፡፡ አንድ ሙስሊም ወላጆቹ ሲያረጁ በቁጣ መንፈስ መናገር ክልክል ነው ፡፡ ለዚህም ማስረጃ አሏህ /ሱ.ወ/ በቁርአን ውስጥ በሱረቱ አል-ኢስራእ ከአንቀጽ 23-24 እንዲህ ይላል፡-

(﴿ وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوٓاْ إِلَّآ إِيَّاهُ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَٰنًا ۚ إِمَّا يَبْلُغَنَّ عِندَكَ ٱلْكِبَرَ أَحَدُهُمَآ أَوْ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل لَّهُمَآ أُفٍّ وَلَا تَنْهَرْهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوْلًا كَرِيمًا ﴿٢٣﴾ وَٱخْفِضْ لَهُمَا جَنَاحَ ٱلذُّلِّ مِنَ ٱلرَّحْمَةِ وَقُل رَّبِّ ٱرْحَمْهُمَا كَمَا رَبَّيَانِى صَغِيرًا ﴿٢٤﴾)

ትርጉሙ

*23- <<ጌታህም እርሱን እንጂ እንዳታመልኩ ደንግጓል ፡፡ ለወላጆቻችሁም መልካም እንድትውሉ (ወስኗል) ፡፡ በተለይም አንዳቸው ወይም ሁለቱ ከናንተ ዘንድ ሆነው እርጅና ከተጫጫናቸው <<ኡፍ>> አትበሏቸው ፡፡ አትገላምጧቸውም ፡፡ መልካምን ቃል ብቻ ተናገሯቸው ፡፡ >>*

*24- <<ከእዝነት የመነጨን የትህትና ክንፍ ዝቅ አድርግላቸው ፡፡ ጌታዬ ሆይ! በልጅነቴ ተንከባክበው እንዳሳደጉኝ እዘንላቸው ፡፡>> በልም ፡፡*

# አምስቱ የእስልምና መሰረቶች ምንድን ናቸው ?

አምስቱ የእስልምና መሰረቶች የሙስሊም ህይወት ፍሬም ወርክ ናቸው ፡፡ እነርሱም በአሏህ አንድነትና በነቢዩ ሙሀመድ/ሰ.ዐ.ወ/ መልዕክተኝነት መመስከር ፤በቀን አምስት ጊዜ ፀሎት ማድረግ ፤ ለድሃዎች ዘካ(ምጽዋት) መስጠት፤ጾምን መጾምና የቻለ ሰው ሐጅ (ወደ መካ መጓዝ) ናቸው ፡፡

## 1- ሸሃደቱ አል-ላኢላሀ ኢል-ለሏህ

<<ላኢላሀ ኢል-ለሏህ ሙሀመዱን ረሱሉሏህ ፡፡>> ማለት ከአሏህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት ሌላ አምላክ የለም ፡፡ ሙሀመድ የአሏህ መልዕክተኛ ነው ፡፡ የመጀመሪያው ክፍል <<ከአንድ አሏህ በስተቀር በእውነት የሚገዙት ጌታ የለም ፡፡ >> ማለትም ከአንድ አሏህ በስተቀር ለመገዛት መብት ያለው ሌላ አምላክ የለም ፡፡ ለአሏህ አጋር የለውም ልጅም የለውም ፡፡ ይህ የእምነት ምስክር ሸሃዳ ተብሎ ይጠራል ፡፡ እስልምናን ሲቀበል በሙሉ እምነት መባል ያለበት ቀላል ፎርሙላ ነው ፡፡ የእምነት ምስክር (ሸሃዳ) ለአምስቱ የእስልምና መሰረቶች በጣም አስፈላጊ ናቸው ፡፡

## 2-ሶላት መስገድ

ሙስሊም በቀን አምስት ጊዜ ሶላት ይሰግዳል (ፀሎት ያደርጋል) ፡፡ እያንዳንዱ ሶላት ከጥቂት ደቂቃዎች በላይ አይወስዱም ፡፡ ፀሎት በእስላም በአሏህና ፀሎት በሚያደርገው ሰውዬ መካከል በቀጥታ አገናኝ ናት ፡፡ በአሏህና በባሪያው መካከል አማላጅ አያስፈልግም ፡፡ ሰውየው በሚሰግድበት ጊዜ ውስጣዊ ደስታ ፤ሰላምና እረፍት የማግኘት ስሜት ይሰማዋል ፡፡ አሏህም በርሱ ይደሰታል ፡፡ ነቢዩ ሙሀመድ /ሰ.ዐ.ወ/ ስለ ሶላት (ፀሎት) ለቢላል እንዲህ ይሉታል ፡- (ቢላል ሆይ ! (ሰዎችን) ለሶላት ጥሪ አድርግና በሶላቷ እፎይታ

እናግኝ (እንደሰት) ፡፡[65] ቢላል ከነቢዩ ሙሀመድ ባልደረቦች አንዱ ነበር ፡፡ እርሱ ነበር ለሶላት አዛን (ጥሪ) እንዲያደርግ የታዘዘው ፡፡ ሶላቶች የሚፈፀሙት ንጋት ላይ ፥ቀትር ላይ ፥ከሰአት በኋላ ፥ፀሃይ ስትጠልቅና ማታ ናቸው ፡፡ እነዚህን ሶላቶች ሙስሊም የትም ቦታ ሊሰግዳቸው ይችላል ፡፡ እንደ ሜዳ ፥ቢሮ ፋብሪካና ዩኒቨርሲቲ የመሳሰሉት ቦታዎች መስገድ ይችላል ፡፡
ስለ ፀሎት የበለጠ መረጃ እባኮ ዌብ ሳይቱን ይጎብኙ ፡-
www.islam-guide.com/praYer

## 3-ዘካ (ምጽዋት ለድሃዎች) መስጠት ፡፡

ሁሉም ነገር ንብረትነቱ ለአሏህ ነው ፡፡ ደግሞም በሰው ልጅ ያለው ገንዘብ አሏህ ዘንድ አደራ ነው ፡፡ (ዘካ) ለሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉም ማጥራትና ዕድገት ማለት ነው ፡፡ ያሰጣጡ ሁኔታ ፡- ካለ ነገር በተወሰነ ልክ ለድሃ መስጠት ያስፈልጋል ፡፡ የሚሰጠው ከወርቅ፥ከብርና ከተሰበሰበ ጥሬ ገንዘብ ሲሆን ልኩ 85 ግራም ወርቅ ይገመታል ፡፡ ይህ በግለሰቡ እጅ (ሳይቀንስ) አንድ አመት መቆየት አለበት ፡፡



ከንብረታችን ትንሽ ድርሻ ለድሃዎች በመስጠት ገንዘባችንን እናጠራለን ፡፡ ያም አትክልትን እንደ መቀፍቀፍ ነው ፡፡ (ይህ አትክልትን) የመቀፍቀፉ ሂደት እንደገና እንደ አዲስ እንዲያድግ ይገፋፋዋል ፡፡ ልክ እንደዚሁ ሰውም ምጽዋት በመስጠትና መልካም ሥራን በማብዛት መደሰት ይችላል ፡፡

[65] ሀዲሱን አቡ-ዳውድ 4985 እና ሙስነድ አህመድ 22578 ዘግበውታል ፡፡

## 4-የረመዷንን ወር መጾም

ሙስሊሞች የረመዷንን ወር በየአመቱ ከንጋት ጀምሮ ፀሐይ እስክትገባ ድረስ ። ምግብና መጠጥ እንዲሁም ግብረ ሥጋ ግኑኝነትን መቆጠብ ነው ። በተጨማሪም ጾም ለጤንነት ይጠቅማል ። ያም መንፈስን ለማጥራት (ለማንጻት) ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ። የሰው ልጅ ለጥቅት ጊዜም ቢሆን አለማዊ ድሎትን በመቁረጥ ፤ ጾመኛ ከተራቡ ሰዎች ጋር በመሳተፍ እውነተኛ ርህራሄን ያተርፋል ። ከዚህም በላይ መንፈሳዊ ህይወት ያድጋል ።




## 5- ወደ መካ ጉዞ

አመታዊ የመካ ጉዞ በህይወት አንድ ጊዜ አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ችሎታ ያለው የግድ ማድረግ አለበት ። በየአመቱ ወደ ሶስት ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ወደ መካ ይሄዳሉ ። እነዚህ ሰዎች ከአለም በአጠቃላይ ይመጣሉ ። ምንም እንኳ ሁል ጊዜ መካ በጎብኚዎች የተጨናነቀ ቢሆንም ሐጅ (ጉብኝቱ) የሚደረገው በአረቢኛው ዙልሂጃ ወር ነው ። ሐጅ የሚያደርገው ሰውዬ የሚለብሰው ልብስ ቀላል ነው ። በተለይ ማንኛውንም ደረጃ ወይም የባህል ልዩነት ይከለክላል ። ስለዚህ ሰዎች አሏህ ፊት እኩል ሆነው ይቆማሉ ።

የሐጅ ሥነ ስርአት ሰባት ጊዜ ካእባን መዞር፤በሶፍ-ፋና መርዋ መካከል ሰባት ጊዜ መሄድ (መሮጥ) / የነቢዩ ኢብራሂም ባለ ቤት/ ሃጀር ውሃን ፈልጋ እንዳደረገችው ። ከዚያም የሐጅ ተግባርን

የሚፈጽሙ ሁሉ በአንድ ላይ አረፋት ላይ ይቆማሉ ፡፡[66] አሏህን የሚፈልጉትን ሁሉ ይጠይቃሉ ፡፡ ይቅርታን ይጠይቁታል ፡፡ የትንሳኤ ቀንን እንድናስታውስ ያደርገናል ፡፡

የሐጅ ሥነ ስርአቱ የሚያበቃው በኢድ አል-አድሃ በአል ነው ፡፡ ያም የሚከበረው በሶላት ነው ፡፡ ይህ በአልና የኢድ አል-ፊጥር በአል ያ በረመዷን ጾም መጨረሻ የሚመጣው ነው ፡፡ እነዚያ ሁለቱ በአሎች በሙስሊም ካላንደር የሰፈሩ ናቸው ፡፡



ይህ ሥዕል የሚያሳየው መካ ውስጥ የሚገኘውን መስጂደል ሐራም ሐጃጆች ሲጎበኙት ነው ፡፡ በዚህ መስጂድ ውስጥ ሙስሊሞች ሶላት ሲሰግዱ ፊታቸውን የሚያዞሩበት ካዕባ ይገኛል ፡፡ ካዕባ አሏህ ኢብራሂም (አብርሃም ) ና እስማኢል እንዲገነቡት ያዘዛቸው የማምለኪያ ቦታ ነው ፡፡

[66] ከመካ ወደ 15 ማይል የምትርቅ አካባቢ ናት ፡፡

ስለ አምስቱ የእስልምና መሰረቶች የበለጠ መረጃ እባኮ ! ዌብ ሳይቱን ይጎብኙ ፡-
www.islam-guide.com/pillars

ስለ እስልምና የበለጠ መረጃ የፈለገ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እና በአረቢኛ ቋንቋ የተተረጎመውን በዌብ ሳይቱ ማግኘት ይችላል ።
www.islam-guide.com

ስለዚህ መጽሐፍ አስተያየት ያለው ፡- ዶራሲ I.A. Ebrahim በሚከተለው አድራሻ ማግኘት ይችላል፡-

ኢሜል ፡ - ib@i-g.org
ስልክ ቁጥር ፡ - 0096614541065
ፋክስ ፡- 0096614536842
ፖስታ ፡- 21679 አል-ሪያድ 11458 ሳውዲ አረቢያ

ስለ እስልምና የበለጠ ለማንበብ

* እውነተኛ ሀይማኖት ፡- ቢላል ፊሊፕስ
* እውነታው ይህ ነው ፡- ሙአስ-ሰሰቱል ሐረመይን አል-ኢስላሚያህ ።
* ቁርአንና ኢልመል-ሐዲስ ፡- ሞሪስ ቦካይ
* እስልምናን ለመረዳት ፡- አቡል-አላ አል-ሞዱዲ
* ህይወት ከሞት በኋላ ፡- (ኪቲብ) ጀምኢየቱ ሸባቡ አል-ሙስሊሚን አል-ኣለሚያህ ።
* የሙስሊም ዐቂዳ ፡- ሙሀመድ አል-ኡሰይሚን ትርጉም ዶክተር ማኒሕ አል-ጀውሃኒ
* የቁርአን አል-ከሪም ትርጉም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ፣ ዶክተር ሙሂድ አል-ሂላሊና ዶክተር ሙሀመድ ኻን

ከነዚህ መጽሀፍቶች ማንኛውንም ማግኘት የፈለገ እባኮ ! ዌብ ሳይቱን ይጎብኙ ፡-

www.islam-guide.com

## ዋቢ መጽሐፍት

የእንጊለዘኛው ትርጉም ፡Abrief Illustrated Guide to understanding Islam

የረቢኛው ትርጉም ፡ደሊሉን ሙሰወር ሊ ፋህሚል ኢስላም

በነጃሺ የተተረጎመው የአማሪኛው ተፍሲር

የአማሪኛው የመጽሀፍ ቅዱስ ትርጉምና ሌሎችም ክዚህ በታች የተጠቀሱ ማስረጃዎች ናቸው።


Ahrens, C. Donald. 1988. *Meteorology Today*. 3rd ed. St. Paul: West Publishing Company.

Anderson, Ralph K.; and others. 1978. *The Use of Satellite Pictures in Weather Analysis and Forecasting*. Geneva: Secretarial of the World Meteorological Organization.

Anthes, Richard A.; John J. Cahir; Alistair B. Fraser; and Hans A. Panofsky. 1981. *The Atmosphere*. 3rd ed. Columbus: Charles E. Merrill Publishing Company.

Barker, Kenneth; and others. 1985. *The NIV Study Bible, New International Version*. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House.

Bodin, Svante. 1978. *Weather and Climate*. Poole, Dorest: Blandford Press Ltd.

Cailleux, Andre'. 1968. *Anatomy of the Earth*. London: World University Library.

Couper, Heather; and Nigel Henbest. 1995. *The Space Atlas*. London: Dorling Kindersley Limited.

Davis, Richard A., Jr. 1972. *Principles of Oceanography*. Don Mills, Ontario: Addison-Wesley Publishing Company.

Douglas, J. D.; and Merrill C. Tenney. 1989. *NIV Compact Dictionary of the Bible*. Grand Rapids, Michigan: Zondervan Publishing House.

Elder, Danny; and John Pernetta. 1991. *Oceans*. London: Mitchell Beazley Publishers.

Famighetti, Robert. 1996. *The World Almanac and Book of Facts 1996*. Mahwah, New Jersey: World Almanac Books.

Gross, M. Grant. 1993. *Oceanography, a View of Earth*. 6th ed. Englewood Cliffs: Prentice-Hall, Inc.

Hickman, Cleveland P.; and others. 1979. *Integrated Principles of Zoology*. 6th ed. St. Louis: The C. V. Mosby Company.

Al-Hilali, Muhammad T.; and Muhammad M. Khan. 1994. *Interpretation of the Meanings of The Noble*

www.alukah.net
شبكة الألوكة

*Quran in the English Language*. 4th revised ed. Riyadh: Maktaba Dar-us-Salam.

*The Holy Bible, Containing the Old and New Testaments (Revised Standard Version)*. 1971. New York: William Collins Sons & Co., Ltd.

Ibn Hesham, Abdul-Malek. *Al-Serah Al-Nabaweyyah*. Beirut: Dar El-Marefah.

The Islamic Affairs Department, The Embassy of Saudi Arabia, Washington, DC. 1989. *Understanding Islam and the Muslims*. Washington, DC: The Islamic Affairs Department, The Embassy of Saudi Arabia.

Kuenen, H. 1960. *Marine Geology*. New York: John Wiley & Sons, Inc.

Leeson, C. R.; and T. S. Leeson. 1981. *Histology*. 4th ed. Philadelphia: W. B. Saunders Company.

Ludlam, F. H. 1980. *Clouds and Storms*. London: The Pennsylvania State University Press.

Makky, Ahmad A.; and others. 1993. *Ee'jaz al-Quran al-Kareem fee Wasf Anwa' al-Riyah, al-Sohob, al-Matar*. Makkah: Commission on Scientific Signs of the Quran and Sunnah.



شبكة الألوكة - قسم الكتب

Miller, Albert; and Jack C. Thompson. 1975. *Elements of Meteorology*. 2nd ed. Columbus: Charles E. Merrill Publishing Company.

Moore, Keith L.; E. Marshall Johnson; T. V. N. Persaud; Gerald C. Goeringer; Abdul-Majeed A. Zindani; and Mustafa A. Ahmed. 1992. *Human Development as Described in the Quran and Sunnah*. Makkah: Commission on Scientific Signs of the Quran and Sunnah.

Moore, Keith L.; A. A. Zindani; and others. 1987. *Al-E'jaz al-Elmy fee al-Naseyah* (The scientific Miracles in the Front of the Head). Makkah: Commission on Scientific Signs of the Quran and Sunnah.

Moore, Keith L. 1983. *The Developing Human, Clinically Oriented Embryology, With Islamic Additions*. 3rd ed. Jeddah: Dar Al-Qiblah.

Moore, Keith L.; and T. V. N. Persaud. 1993. *The Developing Human, Clinically Oriented Embryology*. 5th ed. Philadelphia: W. B. Saunders Company.

El-Naggar, Z. R. 1991. *The Geological Concept of Mountains in the Quran*. 1st ed. Herndon: International Institute of Islamic Thought.

Neufeldt, V. 1994. *Webster's New World Dictionary*. Third College Edition. New York: Prentice Hall.

*The New Encyclopaedia Britannica*. 1981. 15th ed. Chicago: Encyclopaedia Britannica, Inc.

Noback, Charles R.; N. L. Strominger; and R. J. Demarest. 1991. *The Human Nervous System, Introduction and Review*. 4th ed. Philadelphia: Lea & Febiger.

Ostrogorsky, George. 1969. *History of the Byzantine State*. Translated from the German by Joan Hussey. Revised ed. New Brunswick: Rutgers University Press.

Press, Frank; and Raymond Siever. 1982. *Earth*. 3rd ed. San Francisco: W. H. Freeman and Company.

Ross, W. D.; and others. 1963. *The Works of Aristotle Translated into English: Meteorologica*. vol. 3. London: Oxford University Press.

Scorer, Richard; and Harry Wexler. 1963. *A Colour Guide to Clouds*. Robert Maxwell.

Seeds, Michael A. 1981. *Horizons, Exploring the Universe*. Belmont: Wadsworth Publishing Company.

Seeley, Rod R.; Trent D. Stephens; and Philip Tate. 1996. *Essentials of Anatomy & Physiology*. 2nd ed. St. Louis: Mosby-Year Book, Inc.

Sykes, Percy. 1963. *History of Persia*. 3rd ed. London: Macmillan & CO Ltd.

Tarbuck, Edward J.; and Frederick K. Lutgens. 1982. *Earth Science*. 3rd ed. Columbus: Charles E. Merrill Publishing Company.

Thurman, Harold V. 1988. *Introductory Oceanography*. 5th ed. Columbus: Merrill Publishing Company.

Weinberg, Steven. 1984. *The First Three Minutes, a Modern View of the Origin of the Universe*. 5th printing. New York: Bantam Books.

Al-Zarkashy, Badr Al-Deen. 1990. *Al-Borhan fee Oloom Al-Quran*. 1st ed. Beirut: Dar El-Marefah.

Zindani, A. A. *This is the Truth* (video tape). Makkah: Commission on Scientific Signs of the Quran and Sunnah.

## The Numbering of *Hadeeths*:

The numbering of *Hadeeths*[1] in this book is based on the following:

- *Saheeh Muslim*: according to the numbering of Muhammad F. Abdul-Baqy.
- *Saheeh Al-Bukhari*: according to the numbering of *Fath Al-Bari*.
- *Al-Tirmizi*: according to the numbering of Ahmad Shaker.
- *Mosnad Ahmad*: according to the numbering of Dar Ehya' Al-Torath Al-Araby, Beirut.
- *Mowatta*' *Malek*: according to the numbering of *Mowatta*' *Malek*.
- *Abu-Dawood*: according to the numbering of Muhammad Muhyi Al-Deen Abdul-Hameed.
- *Ibn Majah*: according to the numbering of Muhammad F. Abdul-Baqy.
- *Al-Daremey*: according to the numbering of Khalid Al-Saba Al-Alamy and Fawwaz Ahmad Zamarly.

## ምስጋና

አህመድ አወል ሀሰን

አብዱል ጀሊል ሩቤ

ሱልጣን ቶሬ

ዳኛቸው ተፈሪ

ሳራ አብደሏህ

በተለይ ለውድ ባለ ቤቴ

ለራህማ አደም አሊ

هذا الكتاب منشور في

شبكة الألوكة

www.alukah.net